

የአፄ ቴዎድሮስ ኒሻን

*ይህ ኒሻን ከፊት ለፊቱ የሚቀጥለው ፅሁፍ አለበት*

*"የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው"*

*በጀርባው*

*"ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ"*



*ደጃዝማች ካሳ ሀይሉ*

"በስመ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ ቅዱስ፡ አሀዱ አምላክ፡
የእግዚአብሔር ፍጥረት፡ ባርያው ቴዎድሮስ..."

ከአፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤ መግቢያ

*ሀገራቸውንና ህዝብን በቅንነት ለማገልገል ለተሰለፉና ላለፉ ዜጎች መታሰቢያ*

# መቅደላ

## የቴዎድሮስ ዕጣ

ኩማሲና መቅደላ
በሔንሪ ሞርተን ስታንሊ

የመቅደላ ትርጉም
ዶ/ር ገበየሁ ተፈሪ

*መቅደላ! የቴዎድሮስ ዕጣ*

*በእንግሊዝኛ "ኮማሲና መቅደላ፣ ሁለት የእንግሊዞች ዘመቻዎች በአፍሪቃ" ተብሎ በአሜሪካዊው የኒውዮርክ ሔራልድ ጋዜጠኛ በሄንሪ ሞርተን ስታንሊ እኤአ 1874 ከፃፈው መፅሐፍ የተተረጎመ::*

*Coomassie and Magdala*
*The Story of Two British Campaigns in Africa (1874)*
*Henry Morton Stanley*
*Translation of the Magdala part*

*ከመፅሐፉ፣ የሁለተኛው ክፍል፣ የመቅደላ ትርጉም*
*የመጀመሪያ ህትመት (2010)*
*First edition 2017*

*የግርጌ ማስታወሻዎችና ተጨማሪ ምስሎች በገበየሁ ተፈሪ*
*የሽፋን ዲዛይን በገበየሁ ተፈሪ*

*የተርጓሚው ቀደምት ሥራ*
*የተደበቀው ማስታወሻ*
*በገበየሁ ተፈሪና ደሳለኝ እለሙ*

*ሙሉ መብት የተጠበቀ፣ ያለ ፈቃድ ማባዛትም ሆነ ማሳተም ወይም በተለያዩ መገናኛዎች መፅሐፉን ማካፈል ሆነ መተረክ ክልክል ነው::*
*ገበየሁ ተፈሪ*

*Copy right © 2017 by Gebeyehu Teferi*
*All rights reserved including the right to reproduce this book or portions thereof in any form whatsoever*

*ISBN 9780692922033*

*Printed in the USA*
*Signature Book Printing, www.sbpbooks.com*



ይህን ሥራ እንድሠራ ላበረታቱኝ በሙሉ ከልብ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ተጨማሪ ፎቶዎችን ወይም ምስሎችን በአሜሪካ ላይብረሪ ኦፍ ኮንግሬስ የሥራ ቦታቸው በማዘጋጀት ስረዱኝ ለላይብራሪ ኦፍ ኮንግሬስ ባልደረባ ለአቶ ፋንታሁን ጥሩነህ ጥልቅ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ርዕስ ማውጫ


መግቢያ ....................i

ምዕራፍ አንድ ....................1

የእንግሊዞች ካምፕ፣በአለም ምርጥ ሰው፣ ለትልቅ ሰው የሚያስፈልጉ ነገሮች፣ መግቢያ1

የምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች ....................33

ምዕራፍ ሁለት ....................57

አነስሲ ወሽመጥ - ኮሎኔል መርዌዘር

የምዕራፍ ሁለት ማስታወሻዎች ....................79

ምዕራፍ ሶስት ....................81

አስገራሚ የማታ ጉዞ፣ የአቢሲኒያ ሸንጎ፣ የተወላጆች ዲስኩር

ምዕራፍ አራት ....................86

የአለት አምባ፣ እንግዳ የሆነ ተፈጥሮ፣ ስመልፈንገስ በፎቃዳ፣ የአቢሲኒያ ቤተክርስቲያንና የቀብር ስነ ሥርአት

ምዕራፍ አምስት ....................104

የናፒየር አዋጅ፣ ዲፕሎማሲ፣ ሜጀር ግራንት፣ የናፒየርና የመስፍኑ ካሳ ግንኙነት፣ የወዳጅነት ዕይታዎች

የምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች ....................119

ምዕራፍ ስድስት ....................122

እንጣሎ - የገበያ አይነት

ምዕራፍ ሰባት ....................149

ስመልፈንገስና እኔ ተለያዩን፣ የእንግሊዝ ጋዜጦች፣ ሃላፊነት የጎደለው ትንበያቸው፣ የእንግሊዝና ህንድ ሠራዊት መከፋት፣ የተከፉት ቴዎድሮስ፣ አሳዛኝ ምርኮኞች፣ የፖለቲካ መረጃ ሥራዎች፣ የስር ሮበርት አመራርና የዲፕሎማሲ ችሎታ፣ ስለ እንቅስቃሴው ማዝግም ማብራሪያ፣ የእሰያ ዝሆኖች በአቢሲኒያ፣ የማጓጓዣው መስመር

የምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች ....................174

ምዕራፍ  ስምንት ....................178

የአቢሲኒያ ዕይታዎች፣ በተራሮች የታቀፈው የአሸንጌ ሀይቅ፣ የአልኮል መጠጣችን እንዲቀር መደረጉ

ምዕራፍ ዘጠኝ ........ 209

የፖለቲካ መረጃ ሥራ፣ መቅደላ - የድራማው የፍፃሜ ትዕይንት፣ ቴዎድሮስ ተኩስ ከፈቱ፣ የአቢሲኒያኖች ማጥቃት፣ የኮሎኔል ፔን የመጨረሻ ሰላምታ፣ ጅቦች ተኩላዎችና ሥራቸው

ምዕራፍ አስር........ 239

በውጊያው የተጎዱ ሰዎች፣ ጥሩ የለበሰ ምርኮኛ፣ የቴዎድሮስ ተስፋ መቁረጥ፣ ራሳም፣ ያልተጠበቀው እስረኞችን መቀበል፣ የመጨረሻው የእጅ ስጥ ጥሪ

የምዕራፍ አስር ማስታወሻዎች........ 254

ምዕራፍ አስራ አንድ........ 256

ለፍፃሜው ዝግጅት፣ የቴዎድሮስ የመጨረሻ 30ሺ ተፋላሚዎች፣ ከባድ መሳሪያ ድብደባ፣ መቅደላ መግቢያ በር ላይ፣ መቅደላ ላይ የንጉስ ነገሥቱ ራሳቸውን ማጥፋት

የምዕራፍ 11 ማስታወሻዎች ........ 277

ምዕራፍ አስራ ሁለት........ 278

የንጉስ ነገሥቱ ቤት ዘረፋ፣ ጥቁር ኮት ለባሾች፣ ሚቹ ቻሸ

የምዕራፍ 12 ማስታወሻዎች ........ 290

ምዕራፍ አስራ ሶስት ........ 295

የቴዎድሮስ ቀብር፣ ባላንጣ ንግሥቶች፣ የመቅደላ ስንብት፣ የጄኔራል ናፒየር ትዛዝ፣ የተዘረፉ ዕቃዎች ጨረታ፣ አፊሻል ሪፖርት

የምዕራፍ 13 ማስታወሻዎች ........ 318

ምዕራፍ አስራ አራት ........ 320

ወደ መጣንበት - ወደ ተከዜ ጉዞ፣ የሌተናንት ሞርጋን ሞትና ቀብር፣ የቄሶች የምስጋና ቅዳሴ፣ ከመቅደላ ስደተኞች ጋር መለያየት፣ የንግሥት ቪክቶርያ ለክሩሴዱ ጦር እንኳን ደስ ያላችሁ መልክት፣ የእቴጌዋ ሞትና ቀብር፣ ልዑል አለማየሁ፣ የካሳ ሽልማትና ከናፒየር ጋር ስንብት፣ በሶሮ ማለፊያ ትልቅ ጎርፍ

የምዕራፍ 14 ማስታወሻዎች........ 345

ዋቢ መፃሕፍት ........ 347

መቅደላ!........ 348

መዝጊያ ........ 349

## የምሥል ማውጫ

የዙላ ወደብ ዕይታ ........ 2

የዙላ ካምፕ በከፊል ........ 3

የጥንታዊው የአዱሊስ ከተማ ፈርስራሽ በዙላ አጠገብ........ 5

የአርምስተሮንግ መድፎች ሲጫኑ ........ 9

የተራራ ከባድ መሳሪያዎች ሲጫኑ ........ 9

ሎርድ ጆን ራሰል........ 19

ባሻ ፈለቀ ከናፒየር ጋር(በቀኝ በኩል በጥግ የሚታየው ግዙፍ ሰው)........ 25

የአውሮፓ እስረኞች ........ 25

ሆርሙዝ ራሳም ........ 26

ፀሀፊው ሄንሪ ሞርተን ስታንሊ........ 32

በዙላ የውሀ ማጠጫ ገንዳዎች........ 60

ኮሎኔል መርዌዘር ........ 62

የባቡር ሀዲድ በቁማይሌ........ 66

ውሀ ማጠጫ በቁማይሌ........ 67

የሶሮ ማለፊያ (የዲያብሎስ ደረጃ) ........ 72

በቁማይሌ ማለፊያ ፡ አንደል ዌልስ ........ 74

ጉና ጉና በማይ ሙና ሸለቆ........ 83

በማይ ዋሂዝና በአዳ አባጋ መካከል የሚገኝ ግምብ ቤት ........ 93

የእንግሊዞች ካምፕ በአዲግራት ........ 95

የደጃዝማች ካሳ መልክተኛና ተከታዮች........ 107

የእንግሊዞች ካምፕ በአድ አባጋ........ 109

የደጃች ካሳና የሮበርት ናፒየር ግንኙነት ........ 111

ደጃዝማች ካሳ ምርጫ ........ 113

ሌፍተናንት ጀኔራል ሮበርት ናፒየር ........ 115

ደጃች ካሳ የሮኬቶች ተኩስ ልምምድ ሲመለከቱ ........ 118

የአንጣሎ ገበያ........ 124

በአንጣሎ የሚገኝ መንደር........ 125

የበሎቺዎች ሬጅመንት ........ 133

ማርያ ተሬዛ፣ (ማር ተሬዛ)ጠገራ ብር ........ 141

የእስረኞቹ ጎጆዎች በመቅደላ........ 155

የእስረኞቹ መኖሪያ በመቅደላ (ካርታ) ራሳም፤ ........ 155

ሴባስቶፖል ወደ መቅደላ ሲጎተት! ........ 159

ሚር አከበር አሊ ........ 162

የአፄሎ ካምፐ .......... 167
አምባላጌ (የወልደየሱስ አምባ) .......... 169
የአቢሲኒያ መልከተኞች በእንግሊዞች ካምፕ .......... 173
በአሸንጌ ሀይቅ አጠገብ ጉዞ .......... 180
የአርምስትሮንግ ከባድ መሳሪያዎች በተከዜ ሸለቆ ሲጓጓዙ .......... 189
ሜጀር ጄኔራል ቻርለስ ስታቬሊ .......... 198
ካፒቴን ስፒዲ (ባሻ ፈለቀ) .......... 200
የከባድ መሳሪያ ጉዞ መስመር .......... 207
ወደ መቅደላ የሚወስደው መንገድ .......... 211
ከደላንታ አፋፍ፣ የመቅደላና የአካባቢው ዕይታ .......... 212
ፑንጃቦቹ ሳንጃ ወድረው አቢሲኒያውያንን ሲያጠቁ .......... 231
የእንግሊዞች ሮኬት ተኳሾች ብርጌድ .......... 234
የአሮጌ ውጊያ .......... 236
የተለቀቁት እስረኞች ከቤተሰብና ሠራተኞቻቸው ጋር .......... 251
የአፄ ቴዎድሮስ ቀሪ ሠራዊት ከመቅደላ ሲወጣ .......... 260
የእንግሊዝ ጦር እንቅስቃሴ ወደ መቅደላ .......... 261
የእንግሊዝ ጦር መቅደላን ጥሶ ሲገባ .......... 270
የአፄ ቴዎድሮስ ፍፃሜ .......... 272
ኮኪት በር በእንግሊዝ ወታደሮች ሲጠበቅ .......... 274
ካፒቴን ስፒዲ (ባሻ ፈለቀ) ከልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስ ጋር .......... 280
የአፄ ቴዎድሮስ ማህተም .......... 283
በመቅደላ የንጉሡ ቤት ዕይታ .......... 284
የአፄ ቴዎድሮስ ዘውድ .......... 285
ከወርቅ የተሠራው የአቡኑ ዘውድ .......... 285
የአፄ ቴዎድሮስ መስቀል .......... 294
ንግሥት መስታውት ከልጇ ጋር .......... 298
የመቅደላ ቃጠሎ .......... 300
ቄሶች ለሮበርት ናፒየር ሲያሸበሽቡ .......... 323
የአቴጌ ጥሩ ወርቅ የቀብር ሥነ ሥርአት .......... 329
ወላጅ አልባ የቀረው ልዑል አለማየሁ .......... 330
የንግሥቷን ልደት በማክበር በሰናፌ የተደረገ ሠልፍ .......... 333

# መግቢያ

ስለ አፄ ቴዎድሮስ ከዚህ ቀደም በተለያዩ ፀሀፊዎች ሥራዎች ታትመው የቀረቡ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህን ሥራ ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው፣ የአፄ ቴዎድሮስ የመጨረሻዎቹ ቀናትና ሰአታት እንዴት እንደነበሩ በዝርዝር ስለሚያቀርብ ነው፡፡ ፀሐፊው ሄንሪ ሞርተን ስታንሊ፣ የአሜሪካው የኒውዮርክ ሄራልድ ጋዜጣ ዘጋቢ ነበር፡፡ ከእንግሊዝ ጦር ጋር ከዙላ ተነስቶ መቅደላ ድረስ በመጓዝ ያየውንና የሰማውን በዝርዝር ዘግቧል፡፡ አንባቢያን እንደሚረዱት፣ በመቅደላ የእንግሊዞች ዘመቻና በተያያዙ ነገሮች ብዙ የምናውቃቸውን ድርጊቶች በዝርዝር ያቀረበ ሲሆን፣ ሌሎችም በብዛት የማይታወቁ ሁኔታዎችን ዘግቧል፡፡ በሰውዬው ፅሁፍ ላይ መተኮር የሚገባው ራሱ በአካል ተገኝቶ ያየውንና የሰማውን የዘገበውን ክፍል ነው፡፡ ስለ አፄ ቴዎድሮስ የሚያትተው የሰውየው ፅሁፍ፣ ምናልባትም ከሚታወቀው ትንሽ ለየት ያለ ቢመስልም የሰውየን ፅሁፍ እንዳለ አስቀምጫለሁ፡፡ ሆኖም ፀሐፊው ስለ ካሳ ወይም አፄ ቴዎድሮስ በመጠኑም ቢሆን የፃፋቸው አረፍተ ነገሮችንም ሆነ አንቀፆችን የበለጠ ማብራራትና ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

ይህ መፅሐፍ መኖሩን ያወቅሁት፣ ከዚህ ቀደም፣ "የተደበቀው ማስታወሻ" በሚል ርዕስ ለአንባቢ የቀረበ የትርጉም ሥራ በምሠራበት ጊዜ ነበር፡፡ ያም በ2007 አ.ም ነበር፡፡ በአጋጣሚ ነበር፡፡ ከዚህ በፊት እንዳደረግሁት ሁሉ፣ መተርጎም ብቻ ሳይሆን፣ ፀሐፊው ያተታቸው ከስተቶችን ለማመሳከር ሌሎች አያሌ መፅሐፍትን ማገላበጥ ነበረብኝ፡፡ ፀሐፊው፣ ጋዜጠኛም እንደመሆኑ፣ በተጨማሪም አሜሪካዊ በመሆኑ፣ ከእንግሊዞቹ ፀሐፊዎች ተለይቶ ወገናዊነት የጎደለው ይሆናል የሚል ተስፋም ነበረኝ፤ እናም፣ ከሌሎች ጋር ሲነፃፀር፣ በርግጥም ሚዛናዊ ለመሆን ሞክሯል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን፣ በቦታው የነበረ የአይን ምስክር በመሆኑ፣ ታሪኩን የበለጠ ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡

ከዚህ ቀደም በርከት ያሉ ፀሀፊዎች ስለ አፄ ቴዎድሮስ ብዙ ያካፈሉ ስለሆነ ታሪኩን ለመድገም ሳይሆን፣ አንባቢያን፣ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ስለ ንጉሡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው፣ ስለ አፄ ቴዎድሮስ የሚታወቁና የማይታወቁ ተጨማሪ መረጃዎችን በግርጌ ማስታወሻዎች አካፍያለሁ፡፡ በዚህ ሥራ ብዙ ፅሁፎችን በመመልከት፣ በተለይም ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር በቅርብ፣ በአካልም ያዩዋቸውና የተመለከቷቸው ያነጋገሯቸውን ፀሀፊዎችን ሥራዎች

በመመርመር ስለ ንጉሡ ምኞት፣ ባሕሪ፣ ቁመናና ሌሎችም ሁኔታዎች ለአንባቢያን እቅርቤያለሁ::

ለግርጌ ማስታወሻዎች ዋቢ የሆኑ ሥራዎችን በየማስታወሻው መግለፁ በጣም ተደራራቢ ስለሆነ፣ ሁሉም በመፅሐፉ መጨረሻ ገፅ በዝርዝር ተቀምጠዋል:: በእንግሊዝኛው ፅሁፍ የተጠቀመጡትን ቀናት እንዳለ በመጠበቅ፣ ካልተጠቀሰ በስተቀር ቀናቶች በሙሉ እንደ አውሮፓውያን እቆጣጠር ናቸው:: በተጨማሪም፣ የግርጌ ማስታወሻዎች ሰፋ ያሉና ብዛትም ያላቸው ስለሆኑ፣ በየገፁ ከማስቀመጥ ይልቅ በየምዕራፎች መጨረሻ ጠቅለል አድርጎ ማቅረቡ ለንባብ ይረዳል በሚል ግምት በዚህ መልክ ተቀምጠዋል::

በትርጉም ሥራው፣ ፀሐፊው፣ ጥንታዊ የሆኑ የእንግሊዝኛ ቃላትና ምሳሌዎችን ስለተጠቀመ፣ አስቸጋሪና አድካሚ፣ ጊዜም የሚወስድ ሆኖ ነው ያገኘሁት:: ብርታት የሠጠኝ ነገር ቢኖር፣ ይህንን ታሪክ ለሌሎች አንባብያን ማቅረብ የዜግነት ግዴታ አድርጌ ስለወሰድኩ ነበር:: ሌላው አምነቴ ደግሞ፣ ዛሬን የምንተረጉመው ትናንትናን ተመርኩዘን ከሆነ፤ ትናንትና ምን እንደነበር፣ ከፉውም ደጉም ሙሉ በሙሉ መገለፅ አለበት የሚል አምነት ስላለኝ ነው:: ፀሀፊዎች፣ ምናልባትም በበጎ መንፈስ፣ አንዳንዱን ታሪክ ለህዝብ ባይነገር ይሻላል በሚል አመለካከት ነጥለው ሊተዉት ይችላሉ:: በኔ እስተያየት ግን፣ ህዝቡ ራሱ በየዘመኑ ብዙ ፈተናዎችን ያየና ራሱም ምስክር ስለሆነ፣ ያለፈ ታሪክን በትክክል ማወቁ ይጠቅመዋል እንጂ አይጎዳውም:: የነገሮችን አመጣጥ በመገንዘብ ከታሪክ መጥፎው እንዳይደገም ይጥራል ባይ ነኝ:: ታሪክ ሙሉ በሙሉ ካልተነገረ፣ በሚፈጠረው ክፍተት በአብዛኛው በጎ ላልሆኑ ሀሳቦች መንደርደሪያ ሊሆን ስለሚችል፣ በተቻለ መጠን፣ የሆነው፣ የተደረገው ሁሉ እንዳለ ይቅረብ በሚል መንፈስ፣ እነሆ ይህንን ፅሁፍ ለአንባብያን ለማቅረብ በመቻሌ ለፈጣሪ ምሥጋና አቀርባለሁ::

ይህንንም ሳቀርብ ታሪኩ ሊጎረብጣቸው የሚችሉ ሰዎች ይኖሩ ይሆን ብዬ ማሰቤን አልከድም:: ነገር ግን መልሼ ደግሞ፣ ለምንስ ይሆን ሰዎች በታሪክ ቅር ሊሰኙ የሚችሉት በማለት ራሴን መልሼ ጠየቅሁ:: ለአንባቢም ተመሳሳይ ጥያቄ ለማቅረብ አወዳለሁ:: ያለፈውን ወደኋላ ተመልሶ መሟገት ለምንስ ይበጃል? ካለፈው ለመማር ካልሆነ በስተቀር፤ በተለይም አሁን ሌላ ታሪክ መሥራት በሚቻልበት ወቅት:: ሰዎች አዲስ ታሪክ መሥራት ከፈለጉ ደግሞ ወደኋላ ሄደው እንደዚህ ስለነበረ ነው ማለት አያስፈልጋቸውም:: ወደኋላ ከተመለሱ ግን፣ ከታሪክ፣ ከመሀል ምዕራፍ ብቻ ተነስተውም መሆን የለበትም:: በተጨማሪም፣ በዚያን ጊዜ ለተፈፀመው ድርጊት፣ በጊዜው ወይም በዘመኑ ከነበረው ሁኔታ ጋር ነው መታየት የሚኖርበት:: እዚህ ላይ፣ የካቶሊኩ ርዕሰ ጳጳስ ፍራንሲስ፣ ለአሜሪካ ምክር ቤት ተወካዮች ካደረጉት



ንግግር ለመጥቀስ፣ "አሁን ባለ መመዘኛ ያለፈውን መዳኘት ከባድ ነው::" ብለው ነበር:: በእርግጥ፣ ታሪክ እየተነጠለና እየተመረጠ እየተነገራቸው ያደጉ ትውልዶች ካሉ፣ በነሱ ላይ መፍረድ አስቸጋሪ ይሆናል::

ወደ መፅሐፉ ለመመለስ፣ ለኔ፣ ደጋግሞ በአእምሮዬ የሚመላለሰው ትልቁ ጥያቄ፣ እንዴት? ወይም ለምን? የሚለው ነበር::

በቅን መንፈስ፣ በህዝቡ ላይ የነበረውን የመሳፍንት ዘመን ቀንበር ያስወገዱ ጎልማሳ፤ ለራሳቸው ምቾት ሳይፈልጉ በየድንኳኑ ሲንከራተቱ የኖሩ ሰው፤ ለህዝቡም ቢሆን፣ እንዳይበደል፣ ወደፊት ተስፋ እንዲኖረው ያሰቡ ሰው፤ በሀያላን መሳፍንቶች በየቦታው ተቆራርሳ፣ ዙሪያዋን ሊቀራመቷት ከተዘጋጁ ጠላቶች መንጋጋ ያዳኑ ሰው፤ በተቻላቸው መጠን ዘመናዊ ሥርአትን ሊመሰርቱ የታገሉ ሰው፤ እንዴት ሆኖ ነው ወይስ በምን ምክንያት፣ ህዝቡ ወይም ገበሬው የራሱን ጥቅም እሳልፎ በየቦታው አልመች ያለና ግፉ ሲል ንጉሡን ሊወጋ የነበረው:: ከሁሉም በላይ የአፄ ቴዎድሮስን መራራ ስሜት የፈጠረው፣ ይህ ደግ ያሰቡለት ህዝብ ቅን አለመሆን ነበር:: እዚህ ላይ መስተዋል ያለበት፣ ነገሩን የሚጭሩትና፣ እንድ ጠቅለል ያለ ሀገር መኖሩም ያልታያቸው፣ በየቦታው የነበሩት ባላባቶችና መሳፍንቶች ነበሩ:: ገበሬው፣ በመሳፍንቱ ወይም በባላባቱ ስር የተሻለ ኑሮ እግኝቶ እልነበረም የሚያምፁ ወይም የሚሸፍቱ ባላባቶችን ተከትሎ ሲሄድ የነበረው:: ቴዎድሮስ ደግ ላደረጉለትና ደግ ላሰቡለት ህዝብ መሸፈት ምክንያት በየቦታው የነበሩ በትውልድ ከነሱ ጋር የተሳሰሩ ሰዎቻቸው ነበሩ:: እነዚህ ባላባቶቻቸው ያሰቡት ለራሳቸው እንደነበር ግልፅ ነው:: አፄ ቴዎድሮስን፣ የንግሥና ዘር የለውም፤ እናቱ ኮሶ ሻጭ ነች እያሉ፣ ዝቅ ዝቅ ማድረግና ማከፋቱም የመጣው ከነዚህ ተሰፈኛ ባላባቶች ነበር:: ባላባቶቹ የሥርአት ለውጥ ፈላጊዎች አልነበሩም:: የታገሉት፣ ለነበረው በተለይም እነሱ ተጠቃሚ የሆኑበት ሥርአት እንዲቆይ ነበር:: ያንን ለማስፈፀም ግን ተከታዮችን በዘር፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት፣ በአካባቢ፣ በባላባትነት ትውልድ ማሰለፍ ነበረባቸው::

ሌላው ለአፄ ቴዎድሮስ ዕንቅፋት የነበሩት ደግሞ ካህናቱና መነኮሳቱ ነበሩ:: ንጉሡ አምነታቸውን ከድተውም አልነበረም ከካህናቱና መነኮሳቱ ጋር ጠብ የመጣው:: በሀይማኖት ከመጣ፣ ቴዎድሮስ፣ ራሳቸውን "የክርስቶስ ባሪያ" ብለው የሚጠሩ ሰው ነበሩ:: ፈሪሀ እግዚአብሔር እንደነበራቸውም የተሰያዩ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ:: ለሽልማት ያሠሩት ኒሻናቸው ላይ ያስቀረፁት ፅሁፍ ራሱ ምስክር ይሆናል:: በዚያን ጊዜ፣ ከግዛቱ እንድ ሶስተኛው መሬት የቤተክርስቲያኗ ነበር:: ስለዚህ ንጉሡ፣ ገበሬውን ከብዝበዛ ለማዳን፣ ቅጥ ያጣውን አንዳንዴም አስነዋሪ የሆነ የካህናቱን ኑሮ በልክ እንዲሆን በሥርአት አደሩ ስላሉ ነው ጠብ የተፈጠረው:: የጥቅም ጉዳይ

ነበር፡፡ ቤተክርስቲያኗ ከያዘችው መሬት የተወሰነው ለመንግሥት እንዲሆንና ወታደሮቻቸው ገበሬውን እየዘረፉ ሳይሆን በደሞዝ እንዲተዳደሩ ሰሞከሩት ንጉሥ፤ ከካህናቱ የመጣው መልስ፣ የንጉሡ ወታደሮች በደሞዝ ሳይሆን ከቦታ ቦታ እየተዟዟሩ ገበሬውን እየዘረፉ እንዲበሉ ነበር፡፡ እዚህ ላይ፣ አፄ ቴዎድሮስ፣ "እኔ ብቻዬን ስሆንልሽ እንደ አፄ ኢዮአስ በሻሽ እንቀሽ ልትገድይኝ፣" በማለት ከወታደሮቻቸው ጋራ ሲንከራተቱ ነው የኖሩት፡፡ አንግዲህ፣ ይችው የተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ በታሪክ፣ በተለይም በጣልያን ወረራ ጊዜ ቀና ብላ ብትታይም፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ አንክስ እያለች፣ በግልፅም ለዕድገት እንቅፋት ነበረች፡፡ ይህ ደግሞ፣ በውስጧ፣ ፈጣሪን ለማገልገል፣ ምዕመናኑን ከፈጣሪ ጋራ ሰማገናኘት፣ በራሳቸው እነሳሽነት ተምረው ቤተ መቅደሱን በሚረግጡ ካህናት አማካኝነት ነበር፡፡ እነሱስ ቢሆን ሥጋ ለባሽ አይደሉምን? ሰቴዎድሮስ፣ የተበተነ ሀገር ብቻ ሳይሆን፣ በትርጉም የተነሣ የተከፋፈለ ሀይማኖትም ነበር ያጋጠማቸው፡፡

ቴዎድሮስ፣ ምንም እንኳን የብልጭልጭ ኑሮ የማይወዱና ኑሯቸው የተራ ወታደር ቢሆንም፣ የሀገሪቱ ንጉሠ ነገሥት እንደመሆናቸው መጠን፣ በሀገራቸው ሰዎችም ሆነ በውጭ ሰዎች በኩል ምንም አይነት ክብር የጎደለው ነገር የማይቀበሉ ሰው ነበሩ፡፡ በተሰያዩ አጋጣሚዎች፣ የንጉሡን ግንፍል ያስ ቁጣ የሚያስነሳው ይህ ነበር፡፡ ለዚህ አንድ ምሳሌ ለመጥቀስ፣ ቴዎድሮስ ጋፋትን ጎብኝተው ሲመለሱ፣ አንድ ሰማኝ ቀርቦ፣ የእውሮፓ ጌቶቼ ይረዱኛል፣ እርስዎም ይርዱኝ ብሎ በመለመኑ የበገኑት ቴዎድሮስ፣ ከእኔ ውጭ ደግሞ ማን ሌላ ጌታ አለህና ነው ጌቶቼ የምትለው በማለት ሰውየው በዱላ እንዲደበደብ አዘው፣ ወደ አውሮፓውያኑ ዞር ብለው፣ እናንተ ደግሞ ማን ሆናችሁና ነው ራሳችሁን ጌቶች የምትሉት በማለት ተሳድበዋል፡፡ የነጮቹ ንቀት ቴዎድሮስን በጣም ያበሳጫቸው እንደነበር ግልፅ ነበር፡፡ ንቀት ከመስላቸውም እርምጃ ይወስዳሉ፡፡ በላቸው ግዛት፣ ቆንስላ ካልሆነ በስተቀር፣ ሌላው ነጭ በሙሉ ከዜጎቻቸው ጋር እኩል ነው የሚታየው የሚዳኘውም፡፡ ይህ ኩራት ግን የኋላ ኋላ የውጭ ዜጎችን በማስራቸው ያስከተለውን ጣጣ ነው ይህ መፅሐፍ የሚዘግበው፡፡

ከዙላ እስከ መቅደላ፣ ከእንግሊዝ ሠራዊት ጋር የተጓዘው ይህ ሰው፣ ለእንግሊዝ ሠራዊት መቅደላ አፋፍ ድረስ መውጣት፣ የጦር መደራጀት ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎች ብዙ የተሠሩ የፖለቲካ ሥራዎችን ያካፍሰናል፡፡ በዘመኑ ወድ የተባለውን የመቅደላን ዘመቻ፣ እንግሊዞቹ በታላቅ ጥንቃቄና ዝግጅት ነበር ያደረጉት፡፡ ለነሱ፣ በዚያን ጊዜ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በየአህጉሩ ቅኝ ግዛት ስለነበራቸው፣ የታላቋ ብሪታንያ ዜጎችን ማሰርና የንግሥቷን መንግሥት መድፈር፣ ሰሌሎች ቅኝ ግዛቶች አርአያ እንዳይሆንም ነበር፡፡



ስለ አፄ ቴዎድሮስ ባህሪ የበለጠ ሰማወቅ፣ ከዛም በግርጌ ማስታወሻዎች ሰአንባብያን ለማጋራት ብዙ ፅሁፎች መመልከት ነበረብኝ፡፡ አብዛኞች ፀሀፊዎች፣ በተሰይም በእስር የነበሩት ንጉሡን በማከፋት የዘገቡ መሆኑ ብዙም አይገርምም፡፡ ከሌሎች አውሮፓውያን በተለየ ሁኔታ፣ አፄ ቴዎድሮስን በበጎ ባህሪ የሚያስታውሳቸው ሄንሪ ዱፍተን የተባለ እንግሊዛዊ ነው፡፡ ከዱፍተን ሌላ፣ ከንጉሡ ጋራ ሰረዥም ጊዜ አብረው የነበሩ ሰዎች፣ እንደ ፕላውደን፣ ጆን ቤል፣ ሆርሙዝ ራሳምን ጨምሮ፣ ሌሎቹ እንዳደረጉት ንጉሡን በከፋነት አይስሏቸውም፡፡ ነገር ግን፣ በብዛት የሚታወቀው ስራ፣ ቴዎድሮስን አከፍቶ የተፃፈው ነው፡፡ ሆኖም፣ እንባቢ ከዚህ ፅሁፍ በቂ ግንዛቤዎች በማግኘት የራሱን አስተያየት መስጠት እንደሚችል ተስፋ አለኝ፡፡

በነዚህ የተሰያዩ ፅሁፎች፣ በአብዛኛው የሰውየው ባህሪ አገላለጥ እንደፀሀፊዎቹ ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እንዱን እንብቤ ሌላውን እስከማነሳ ድረስ፣ በፅሁፉ አገላለጥ የተነሳ፣ ቴዎድሮስ እንደዚህ አይነት ሰው ነበሩ ወይ ብዬም የጠየቅሁበት ጊዜ አለ፡፡ ነገር ግን፣ በተቻለ መጠን የተሰያዩ ፀሐፊዎችን ሥራ ለማየት በመቻሌ፣ በተለይም ከንጉሡ ጋር ቅርበት የነበራቸውን፣ ወይም በዘመኑ የነበሩ ፀሐፊዎች የፃፉትን ስመለከት፣ አከብሮቴ ጨመረ እንጂ አላነሰም፡፡ ያም ሆኖ ቴዎድሮስ ያሳዩትን ባህሪ ለመሸሸግ ወይም ሰማሳመር አልሞከርኩም፡፡ ቴዎድሮስ ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎቹም በዘመኑ የነበሩ ጉልህ ሰዎች ያደረጉትን እንዳለ ነው ያስቀመጥኩት፡፡

ዋናው ነገር፣ ቴዎድሮስም ሆነ ሌሎች መሪዎች ላይ ፍርድ መሠጠት የሚገባው፣ ሚዛን ላይ በማስቀመጥ ነው፡፡ ያም፣ በኔ እስተያየት፣ በሁለት መንገድ መታየት አለበት፡፡ አንደኛ፣ በንፁህ ልባቸው፣ ሰሀገሩ፣ ሰህዝቡ ከጥዋቱ ምን አስበው ነበር? ምንስ ሰማድረግ ፈልገው ነበር? ሁለተኛ ደግሞ፣ ያው ግልፅ እንደሆነው፣ ምን ትተውልን አለፉ? የሚለው ነው፡፡ ይህ ደግሞ በዘመኑ በነበሩ ሁኔታዎች ነው መታየት ያለበት፡፡ እንደምንረዳው፣ ቴዎድሮስ ወደፊት ሲያስቡ ባላባቱና ህዝቡ ደግሞ እንቅፋት ሆነው እንደነበሩ ነው፡፡ የባላባቱ እንኳን አያስደንቅም፡፡ ቴዎድሮስ አዲስ አገር አልፈጠሩም፤ የተበተነች ሀገር ነው የሰበሰቡት፡፡ ይህንንም ሲያደርጉ በዘመኑ የነበረው አማራጭ መንገድ ግልፅ ነበር፡፡

አፄ ቴዎድሮስ ከመንገሣቸው በፊት፣ ህዝቡ ተመችቶት የሚኖር አልነበረም፡፡ ተማሮና ተቸግሮ ስለነበር፣ እንደ ቴዎድሮስ አይነት ሰው እንዲመጣ በናፍቆት ሲጠብቅ ነበረ፡፡ የኋላ የኋላ፣ ይህ በናፍቆት የጠበቃቸው ህዝብ፣ ሰውየው ያሰቡለትን የተረዳ አልመሰለም፡፡ በየቦታው፣ በተወላጅ ባላባቶቹ ሰበካ ልቡን መልሶ ነፍጓቸዋል፡፡ ጨካኝ ወይም እምባ ገነን ስለሆኑ ነው? እምባገነንቱ እንኳን በቀላሉ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ምፅአተ

ቴዎድሮስ በጉጉት ይጠበቅ ነበር። ቴዎድሮስ፣ ካሳ ይሁን ወይም ሌላ ሰው፣ ብቻ የነበረውን አስከፊ ጊዜ የሚያስወግድ ሰው ነበር የተጠበቀው። በዚያን ጊዜም፣ ህዝቡ ለሰውየው በነበረው ፍቅርና አድናቆት፣ የውነት የዲሞክራሲ ምርጫ ቢኖር ኖሮ ባሸነፉ ነበር። በዚያን ጊዜስ ቢሆን የትኛው የአውሮፓ አገር ነው በዲሞክራሲ የሚመራ የነበረው? በርግጥ ጭካኔ ነበር። ነገር ግን የጭካኔ አሰራሩ ቴዎድሮስን ቀድሞ የነበረና ከዚህ በተጨማሪ በዘመኑ የነበረው የአገሪቱ ህግ ወይም የፍትህ ነገሥቱ ቅጣት ራሱ በጣም ጨካኝ ነበር። ከቴዎድሮስ በፊት የነበሩ ባላባቶችና መሳፍንቶችም ብዙ የጭካኔ ሥራዎችን ይሠሩ ነበር። በተጨማሪም፣ ካሳ፣ ከሽፍትነት ጀምሮ ሥነ ሥርአት አጥባቂ ሰው ስለነበሩ፣ የሥነ ሥርአት አርምጃው ወታደሮቻቸው ላይ እንኳን የከረረ ነበር። ያም ቢሆን ወታደሮች ገበሬ ሲበድሉ በመገኘታቸው ነበር። የቴዎድሮስን ቅጣት ለየት የሚያደረገው ዘመናቸውን በሙሉ በውጊያና በዘመቻ ስላሳለፉት በሞት የሚቀጣው ሰው ቁጥር የተበራከተ መሆኑ ነው። ከዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው አብይ ነገር፣ አፄ ቴዎድሮስ ላሳቡት አላማ እንቅፋት የሆነ በሙሉ፣ ዘርና ሀይማኖት ሳይለይ በትራቸውን ቀምሷል። ያስርሀራሄ ከተደመሰሱ ወገኖች አንዱ፣ የወንድማቸው ልጅ የጋረድ ከንፉ ሰዎች ነበሩ።

በመጀመሪያዎቹ ድሎቻቸው፣ የቆሰሉ ባላባቶችን ምረውና ተንከባክበው፣ አንዳንዴም ሾመው ሲሄዱ በጀርባቸው እየከዱ ማስቸገሩ፣ ንጉሡን መረር ያለ ቆራጥ ርምጃ እንዲወስዱ አድርጓቸዋል። በየትኛውም አለም ቢሆን ሀገርንና ንጉሥን መክዳት የሚያስከትለው ቅጣት ከፍ ያለ ነበር።

የቴዎድሮስን መራራ በትር የቀመስ ክፍል አከሌ ከአከሌ ሳይባል ሁሉም ነበር። በርግጥ፣ ብዙ ጉዳት የደረሰበት ክፍል በየጊዜው እየሸፈተ ያስቸገረው መሆኑ ግልፅ ነበር። ታዲያ፣ የቴዎድሮስ ሀይል ካረፈባቸው ከፍሎች፣ የንጉሡን መራራ ቅጣት ወደ ጎን አድርጎ፣ ይልቁንም ሰውየው የታገሉለትን በማስታወስ እንደ ጀግና የሚያወድሰና የሚዘክር ወገን ይታያል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ምን ሲባል የቴዎድሮስ ስም ይነሳል የሚል ወገን ብቅ አያለ ነው። ይህ በርግጥ በፅሞና ማነጋገር የሚገባ ነገር መሆን አለበት። የሞተው በዚያም በዚህ ሆኖ እያለ፤ ሥልጣኑን የተቀማው ባላባት ሁሉም ሆኖ እያለ፤ ያንዱ ወገን ቁስል ብቻ አልሽር የሚልበት ምክንያት ለምን ይሆን? ቴዎድሮስ ያወረዷቸው ባላባቶች ራሳቸው፣ የአብዛኞቹ፣ በዚያን ጊዜ ይዘውት የነበረው ሥልጣን በሀይል ያገኙት ነበር። ባጠቃላይ ሲታይ፣ በዚች ሀገር ታሪክ፣ መጠኑ ይብዛ ይነስ እንጂ ያልቆሰለና ያላቆሰለ የለም።

አፄ ቴዎድሮስ ያሰቡት፣ ሁሉንም በአንድ ሥርአት አሰገብቶ ወደፊት ለመራመድ ነበር። በተቃራኒው በጣም የሚያሳዝነው፣ ህዝብ ወደፊት መሄድ



ፈልጎ መሪ ወደኋላ ሲጎትት ማየት ነው። የቴዎድሮስ ሁኔታ ያ አልነበረም። አውሮፓውያኑ የመሰከሩላቸው ነገር ቢኖር፣ ከሀገራቸው ሰዎች ተለይተው አርቀው ሀሳቢና ወደፊት መራመድ የሚፈልጉም እንደነበሩ ነው።

በዚያን ጊዜ፣ ሁሉም ጉልበት ያለው ባላባት ለመንገሥ ያስብና ይዘጋጅም ነበር። ጉልበት አለን የሚሉት ደግሞ በየግላቸው ከአውሮፓ ሀያላን ጋር በግል ይፃፃፉ ነበር። አንዳንዶቹም የሀገሪቱን መሬት በሥጦታም ሆነ በሽያጭ ለውጭ ሀይሎች ለመስጠት ሞክረዋል። ባላባቶቹ ሲፃፃፉም ራሳቸውን ንጉሥ እያሉም ነበር። ለጊዜው ጉልበት ላለው እየገበሩ፣ ውስጥ ውስጡን ግን የራሳቸውን ቀን ይቆጥሩ እንደነበር ግልፅ ነበር። የግል አላማቸውን ለማስፈፀም ከውጭ ሀይሎች ጋር ከመተባበር አይመለሱም። በዚህ በኩል ደግሞ አከሌ ከአከሌ ሳይባል ሁሉም የሚያደርጉት ነገር ነው የነበረው። በተለይም ታላላቆቹ።

መሳፍንቶቹ ያለማሰለስ በየጊዜው ሀይላቸውን ሲፈታተሹ በመሀከላቸው የተደረጉት የርስ በርስ ጦርነቶች ምስክር ናቸው። በዚህ የርስ በርስ ጦርነት ደግሞ፣ የሚፈሩትን ለማጥቃት ሁለት ወገኖች ነሳ ሳይለዩ ግንባር እየፈጠሩ፣ እንደገናም እርስ በርሳቸው እየተዋጉ ነበር የኖሩት። ካሳ ሲነሱ፣ ህዝቡ በጦርነት ተዳክሞ ሰላም የሚፈልግበት ጊዜ ነው የነበረው። ባላባቱ አንዱ ላንዱ ባይተኛም፣ የዚያን ጊዜውን ሁኔታ ለየት የሚያደርገው፣ እያንዳንዱ አፈንግጦ መውጣት ሳይሆን በሀይል ጠቅሎ ለመያዝ ስለሚፈልግ ነው የሚል የታሪክ ባለሙያተኞች አስተያዬት አለ። እውነታም ሊኖረው ይችላል፤ ሆኖም ካሳ ባይነሱና በጉልበት ባያዋህዱ ኖሮ፣ ሁሉም በየቦታው የራሱን ግዛት ሊያሰፋ ስለነበር የተዋሀደች ሀገር ለመፈጠሩ ዋስትና አልነበረም። ከካሳ በፊት መሳፍንቶቹ ጠቅልለው ለመግዛት ሳይሞከሩ ቀርተውም አልነበረም። ነገር ግን፣ በዚያን ጊዜ ለውጥ ለማምጣት የካሳን አይነት የተለየ ባህሪ የነበረው ሰው አስፈላጊ የነበረ ይመስላል። ስለዚህ ካሳ ባይነሱ፣ ምናልባትም አሁን የምናውቃት ኢትዮጵያ ልትኖር አትችልም ይሆናል። የዚህ የርስ በርስ ሁኔታ፣ በተቃራኒው፣ ደንበራቸውን ጠንክረው መያዝ የሚችሉ ጉልበታም ባላባቶች በሌላው ሲመቱ፣ በደንበሩ በኩል ያለው ሀይል ሲደክም ነው የሚታየው። ለዚህም አንድ ትልቅ ምስክር፣ ከተከዜ እስከ ቀይ ባህር ሲገዙ የነበሩት ሀይለኛው የእንደርታው ባላባት የራስ ወልደ ስላሴ ቤት፣ ከዚያም የተከተላቸውና መዲናውን ወደ አዲግራት ያዞረው የሰባጋዲስ ጦር በራስ ማርዬ ጦር ሲመታ፣ የራስ ማርዬ ጦር ተመልሶ ወደ መጣበት ሄደ እንጂ ደንበሩን ለማስጠበቅ አልሞከረም።

ይህ ሥራ፣ ርእሱ መቅደላ ቢሆንም፣ የቴዎድሮስን ማንነትና አላማ ለአንባቢ ለማስገንዘብ የጣረ ፅሁፍ በመሆኑ፣ አንባቢ ሰፋ ያለ ግንዛቤ

እንደሚያገኝ ተሰፋ አለኝ። ሌላው ምኞቴ ደግሞ፣ ይህ ፅሁፍ መወቃቀሻ ሳይሆን፣ ንጉሡ የደከሙበትን፣ ከዚያም በተከታዮቻቸው ተጠናክሮና ተሰፋፍቶ የተረከብነው ሀገር ውስጥ አብሮ መኖር እንዲቻል መመካከሪያም እንዲሆን ነው። ኢትዮጵያ ተብላ የምትጠራው ሀገር ደንበር፣ በባለሙያተኞች መልካም ፈቃድ የተሳለ አይደለም፤ የብዙ ወገኖቻችን፣ ንጉሥንም ጨምሮ፣ ደም የፈሰሰበትና አጥንት የተከሰከሰበት አጥር ነው። አሁን መሀል አገር የሚባለው ክፍል፣ ደንበሩ በመሰዋትነት ተጠብቆ ሰለቆየ እንጂ፣ ራሱ መሀሉ ዳር ከመሆን የሚያሰጥለው ነገር አልነበረም። በዚች አገር ታሪክ፣ በተለይ በቁጥራቸው ታላላቅ የሚባሉ ብሔረሰቦች፣ በስማቸው በየተራ ሥልጣን ይዘዋል። አንዱ ብቻ በዳይ ሆኖ ሌላው ተበዳይ ከመሆን በለተቀር ምንም አይነት ሚና እንዳልነበረው ተደርጎ የሚቀርበው ከእውነታ የራቀ ነው። ይልቁን፣ የየራሱን ባላባት ሥልጣን ላይ ለማቆየት ሲል በአንድነት መዳዝ የሚቻልበትን መንገድ አዳከሞታል። ደጋግሞም የሚታየው በአንድ ወገን ሰም ጉልበት ያለው ሥልጣን ቢይዝም፣ የዚያ ወገን ለሆነው ለተራው ህዝብ ግን ከኑሮው የሚያሻሽለው ምንም ነገር አልነበረም። ግብሩም አይቀንለለትም፤ እንዲያውም አዲስ ለመጣው፣ የኔ ነው ለሚለው ባላባት መከፈሉን አያቆምም ነበር። በሁሉም ወገን ለደሀው ጠብ የሚልለት ነገር አልነበረም። በዚህ መፅሐፍ ውስጥም፣ ከቴዎድሮስ ያፈነገጡ፣ ነገር ግን አዲስ ለተተካው ለዋግሹም አልገብርም ያሉ በጦር ሲቀጡ ይታያል።

እዚህ ላይ ግን፣ ተራው ህዝብ የሚባለውስ ሀላፊነት አልነበረበትም? ወይስ የለበትም ወይ? ቴዎድሮስ ተራውን ህዝብ ክፉ ነው ብለው ነው የሚወቅሱት። ለራሱ የሚመቸውንና የሚሆነውን መንገድ አለማሰቡና ከውሰጡ በሚፈጠሩ ጥቂት መሪዎች በመነዳት አንድ ላይ ሆኖ ለሚበጀው ሥርአት አለመታገሉ፣ ንጉሡ እንዳሉት ክፉ ነው ወይ?

አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸው የጭካኔ ሥራ እንደለሩ የሚያውቁ ይመስላሉ። አብዛኛውን የጭካኔ ሥራ ከባላንጣዎቻቸው ወይም ከሽፍቶች እንደተማሩ ይገለጣል። በተለይም፣ በንጉሡ ወታደሮች ላይ ይደረግ የነበረውን የጭካኔ ሥራ፣ ንጉሡ መልሰው ሌሎቹ ላይ አድርገውታል። እንደታየው ከሆነ፣ በወሰዱት ርምጃ ተዝናንተው የሚቧርቁም አልነበሩም። በተለያዩ ጊዜያት እንደተፀፀቱ የሚገልፁ ዘገባዎች አሉ። ተራውን ሰውና ባላባቱንም ይቅርታ የጠየቁበት ጊዜ አለ። አውሮፓውያኑንም ሳይቀር ይቅርታ የጠየቁበት ጊዜም አለ። እንደ ቴዎድሮለ ኩራት፣ ራሰን ዝቅ አድርጎ ይቅርታ መጠየቅ የይለሙላ አይመስልም። መቅደላም ላይ ቢሆን፣ ሰዎች ከተገደሉ በኋላ በመፀፀት አቡኑን ለምን አልገዘቱኝም ነበር በማለት የጠየቁበት ጊዜ አለ። ባንድ በኩል ግን፣ ንጉሡ፣ ክፉ ናቸው የሚሏቸውን ሰዎች ለመቅጣት ሥልጣናቸው ከፈጣሪ



እንደሆነ አድርገው የተቀበሉት። ያም ሆነ ይህ፣ የብሰጭታቸው መነሻ የሆነው፣ የሰዎች በየቦታው ከህደትና መሸፈት፤ የአውሮፓውያኑ ንቀትና ከውጭ ጠላቶቻቸው ጋር ሲተባበሩ ማየት፤ እየጨመረ እንጂ እያነሰ ሰላልሄደ ብሰጭቱም ቀጠለ እንጂ አላባራም ነበር። ብዙዎች ምስክርነት እንደሰጡበት፣ ሰውየው ከጥዋቱ ክፉ ሰው አልነበሩም። ይህም በመፅሐፉ በተለያዩ ክፍሎች ይጠቀሳል። እዚህ ላይም ሌላው ዋናው ነገር፣ የሰውየው ባህሪ ተቀየረ ነው። ይህን ደግሞ የውሰጥም ሆነ የውጭ ታሪክ ፀሐፊዎች በሙሉ የሚሰማሙበት ነገር ነው።

አፄ ቴዎድሮስ ወደ መቅደላ ሲገሰግሱ ፍፃሜያቸውን በግልፅ ያውቁ ነበር። በመቅደላ እንደሚሞቱም ያውቁ ነበር። ለእንግሊዙ መልከተኛ፣ ለራሳም፣ ሲሞቱ እስከሬናቸው እጠገብ ቆሞ ሊዛበትባቸው እንደሚችል አስቀድመው ነግረውታል። እኔ ራሴን ለፈጣሪ እሰጣለሁ እንጂ ለማንም አልሠጥም ነው ያሉት። በዚያን ጊዜ፣ ያለሯቸውን ነጮች ለመግደል ምንም የሚያግዳቸው ነገርም አልነበርም። በምክር ሲወለን፣ ቴዎድሮስ ነው የተቃወሙት፤ ለህገሬ ሰው ጠንቅ ጥዬ አልሄድም ነበረ መልሳቸው። ቢዚያ ባለቀና በጨለም ሁኔታም ቢሆን እርቆ ማሰቡ አልጠፋም። አንዳንዴ፣ እንዲህ ቢሆን ኖሮስ የሚል ጥያቄ ማንሳት የማይመሰልና የማይመች ቢሆንም፣ በሀሳብ ለመሚገት፣ ቴዎድሮስ ባይነሱ ኖሮስ? ብሎ መጠየቅ እንግዳ አይሆንም። ለዚህ ጥያቄ መልሰ ግን፣ ቴዎድሮስ ሲነሱ አገሪቷ በምን ሁኔታ እንደነበረች መረዳትን ይጠይቃል። ባጭሩ፣ ለመቶ አመታት በአርለ በርሰ ጦርነት የደከመች አገር ነው የነበረችው።

መለሰ ብለን ካየነው፣ በዚች ሀገር ውሰጥ ጥሩ ነገር ለመሰራት እንኳን ከባድ የነበር ይመሰላል። ይህ ጉዳይ፣ በአፄ ቴዎድሮስ ብቻ ሳይሆን፣ አፄ ኃይለ ሥላሴም ቢሆን በመጀመሪያው የንግሥናቸው ዘመናቶች ብዙ ለመለወጥ ሞከረው ሳይላካላቸው ተስፋ ቆርጠው የተውት ይመስላል። ያም ሆኖ፣ አፄ ቴዎድሮስ የጀመሩት የማዕከላዊ መንግሥት ምሰረታ ሙሉ በሙሉ ሥር የያዘው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነው።

ቴዎድሮለ፣ ሀገር ብቻ ሳይሆን፣ ቤተክርሰቲያኗ አንድ እንድትሆን ሞክረው ነበር። የቤተክርሰቲያኗ ሊቃውንቶችና ካህናቱ፣ ሁለት ልደትና ሶስት ልደት በሚባሉ ወገኖች ተከፋፍለው ነበር። ከዳጃች ውቤ ጋር የነበሩት፣ የግብፁ አንድርያሰ፣ በኋላም አቡነ ሰላማ፣ ደጃች ውቤ በራለ አሊ ሲሸነፉ፣ ከራለ አሊ ጋራ ቆይተው ነበር። ሆኖም፣ የአዘዞና የሸዋ ካህናት፣ በዚሁ በትርጉም የተነሳ፣ አንድ ላይ በመሆን አብረው፣ ለራለ አሊና ለእናታቸው ለወይዘሮ መነን ብር በመሰጠትና በመወትወት አቡኑን ወደ መጡበት ወደ ደጃች ውቤ እንዲመለሱ አድርገዋቸዋል። ሶሰት ልደቶቹ፣ የአዘዞና የሸዋ

ካህናት የአቡነ ሰላማን ወገኖች ዘርፈውና ገፈው ሰደዷቸው ይላሉ ደብተራ ዘነብ፡፡ በዚያን ጊዜ፣ አቡኑም ቢሆን አዝነው ስቴዎድሮስ መምጣት ፀልየዋል፡፡ አፄ ቴዎድሮስ ከነገሱ በኋላ፣ ከንጉሡ ጋራ የተመለሱት አቡነ ሰላማ ቂማቸውን ሳይረሱ፣ ቴዎድሮስ በሌሉበት ጊዜ አግራቸውን እየጠበቁ ብድራቸውን መልሰዋል፡፡ ቴዎድሮስ ሀይማኖቱን ወደ አንድ ሰማምጣት ቢጥሩም፣ አፄ ዮሐንስ አራተኛ ናቸው ሊቃውንቱን ቦሩ ሜዳ አከራክረው አንድ ያደረጉት፡፡ ከዚያ በኋላ ተዋህዶዎች ወይም ሁስት ልደት የሚባሉት ከርከሩን አሸንፈው ቤተክርስቲያኗ በተዋህዶ እንደፀናች ይታወቃል፡፡ የተረቱት ሶስት ልደቶች ግን ተደበቁ እንጂ ጭራሽ ለመጥፋታቸው ማረጋገጫ የለም፡፡

በየትኛውም የአለም ክፍል፣ በሰላማዊ መንገድ የተመሠረተ አገር ያለ አይመስልም፡፡ ሀገር ቀርቶ፣ ታላላቅ ሀይማኖቶች የሚባሉት እንኳን፣ በውስጥ ታሪካቸው ጥፋትና የሕይወት ማለፍ አብሯቸው የተፈጠረ ይመስላል፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ ያለፈ የርስ በርስ ጦርነት ታሪኳ ብርቅ አይደለም፡፡ ዋናው ነገር፣ አዲሱ ትውልድ የተረከበውን አገር ወደ የት ይዞ መሄድ እንደሚፈልግ ማወቅና መወሰን ይኖርበታል፡፡ አንደ አገር ጠብቆ፣ በውስጡ መብቱን አስከብሮና ተከባብሮ መኖር ይችላል ወይ? ነው ጥያቄው፡፡ በአሜሪካ አመሠራረት ላይ አንድ ተደጋግሞ የሚነገር ታሪክ አለ፡፡ ይኸውም፣ የአሜሪካ መስራች አባቶች የሚባሉት ተወካዮች ስብሰባ ጨርሰው ሲወጡ፣ ከተወካዮች አንዱ የሆነውን ቤንጃሚን ፍራንክሊንን፣ በቦታው የነበሩ ሰዎች ቀርበው፣ ምን አይነት መንግሥት ፈጠራችሁልን ብለው ይጠይቁታል፡፡ የሰውየው አጭር መልስ ደግሞ፣ "ጠብቃችሁ መያዝ ከቻላችሁ፣ ሪፓብሊክ ነው፡፡" የሚል ነበር፡፡ በዚህ መፅሐፍ፣ ራሳቸው ባያዩትም፣ ይችን ሀገር መልሰው ስብስብ አድርገው የሠጡንን ሰው ታሪክና ፍፃሜ ነው የምንከታተለው፡፡ የቴዎድሮስ የመጨረሻው ሰአት እንደዚህ በዝርዝር ተገልጦ አያውቅም፡፡ በሌሎች፣ ስለ ቴዎድሮስ በሚጠቅሱ ሰዎችም፣ በመቅደላ ላይ ስለሆነው ሁኔታ በዝርዝር አፃፃፉ የሚጠቀሰው ይህ የስታንሊ ስራ ነው፡፡

ገበየሁ ተፈሪ ዶ/ር

2009 (እኤአ 2017)

# ምዕራፍ አንድ

የእንግሊዞች ካምፕ፣በአለም ምርጥ ሰው፣ ለትልቅ ሰው የሚያስፈልጉ ነገሮች፣ መግቢያ

የዙላ ወደብ ሳርፍ፣ በጣም አስገራሚና አዲስ የሆነ ትዕይንት ነው ያጋጠመኝ፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ከወገብ በላይ ራቁት የሆኑ ሰዎች፣ በማያባራው የአፍሪቃ ሞቃት ፀሐይ ሥር፣ እየጮሁና እየዘመሩ ሥራቸውን ያከናውናሉ፡፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዩኒፎርም የለበሱ አሠሪዎች፣ መግረፊያ አለንጋቸውን ይዘው፣ በምድባቸው ያሉ ሠራተኞችን በማስገደድ ያሠራሉ፡፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ የሚያናፉ አህዮች፣ የሚያስካኩ ፈረሶችና በቅሎዎች፣ በዝቅተኛ ድምፅ የሚያጓሩት ውሀ የተጠሙ የቀንድ ከብቶች፣ የሚሰቀጥጥ ድምፅ ያላቸው ሁለት ያልተለመዱ ሎኮሞቲቮች፣ ወዲያና ወዲህ የሚመላለሱ ጨኸት ያላቸው ተሽከርካሪዎች ተደማምሮ፣ መጀመሪያ ለተመለከተ ሰው፣ የሀገሩ ሰው ሁሉ በስደት መጥቶ በአነስሊ[1] ወሽመጥ ዳርቻ ትልቅ ከተማ ሊመሠርት ያለበ ይመስላል፡፡ በሸራ የተሸፈኑ የጋራ ክምር የመሰሉ የቁሳቁስ ቁልሎች፣ ረዣዥም ለጦርነት መገልገያ በሆኑ ቁሳቁሶች የተሞሉ የአንጨት ጣራ ያላቸው መካዝኖች፣ በወደቡም፣ ሞገስ ያላቸው የባሕር ማማለሻ መርከቦች፣ ወታደሮች፣ የተለያዩ የባሕር ማመላለሻ ቀላልና ከበድ ያሉ ጀልባዎች፣ ቁጥር ሥፍር የሌላቸው፣ ከሞካ፣ ሶአኪም፣ ጀዳና ምፅዋ የመጡ የቱርክ ጀልባዎች፣ እንደ ክንፍ ከተዘረጋው በነፋስ የሚገፋው ሸራቸው ጋር ወደቡን ሲርመሰመሱበት የተፈጠረውን ህልማዊ ትዕይንት አባብሰውታል፡፡

ከእንግሊዞች ሠራዊት የማውቀው ሰው ስላልነበረ፣ ይህንን የእንግሊዞች የጦር ካምፕ ኑሮ የሚያስተዋውቀኝ ሰው የግድ ማግኘት ነበረብኝ፡፡ ሳስታውስ፣ በአንድ ሻለቃ (ሜጀር ኤስ)፣ ከአንድ የእንግሊዝ ጦር የትጥቅና ስንቅ መኮንን ጋር እንድተዋወቅበት የተሠጠኝ ደብዳቤ በእጄ እንዳለ ተገነዘብኩ፡፡ አገልጋዩን አሊን፣ እስከመለስ ድረስ ከአንድ ትልቅ መካዝን አጠገብ እንዲጠብቀኝ ትዛዝ ሠጥቼ ተሰናበትኩት፡፡ በፍጥነትም፣ በአንጨት

[1] የዙላ ወይም የአራፋሊ ሠርጥ ተብሎም ይታወቃል፡፡ የቀይ ባህር ደንበር ነው፡፡

ከተሠራ ቤት አጠገብ የተተከሉ የተንጣለሉ ድንኳኖች ወዳሉበት ሥፍራ አመራሁ:: ቁጥራቸው በርከት ያለ ነጭ እጀጠባብ የለበሱና ራሳቸው ላይ ጥምጣም ያደረጉ ህንዶች በፍጥነት ይሯሯጣሉ:: ሰፋ ካለውና ምቾት በተመላበት ሁኔታ በተንጣለለው ድንኳን አጠገብ ዘብ የቆመውን ወታደር ጠየቅሁት:: "የካፒቴን ዚ ድንኳን የትኛው ነው?" ወታደሩም፣ ብዙም ራቅ ሳይል የተተከለ፣ ተለቅ ወዳለ ድንኳን አቅጣጫ አመላከተኝ:: ድንኳኑ፣ ዙሪያውን ችፍግ ባሉ ተከሎች ተከቧል፤ ከሌሎች ድንኳኖች መለያ ምልክት መሆኑ ነው:: ከተጠቀሰው ድንኳን እንደደረስኩም፣ በውስጡ ላለው ሰው ኀብኘ መምጣቴን ለማሳወቅ የድንኳኑን ሸራ ጫር ጫር አደረኩት:: ወድያውኑ፣ የህንዶች ረጅም ጀለብያና ሰፋ ያሉ ሱሪዎች (ፒጃማ ይባላሉ) ለብሶ በሙሉ ሰውነቱ ሰፋ ላይ በተጋደመ ሰው ወደ ውስጥ እንደገባ ተጋበዝኩ::

"የኮሚሳሪያቱን ካፒቴን ዚን[2] ለማየት ነው የመጣሁት፣ ሰር፣"፣ በእንግዳ ፊት ምንም ስሜት ያልተሰማው ሰው መሆኑን በማየትና በመገረም፣ "እርሰዎ ነዎት ወይ ሰውየው?" ብዬ ጠየቅሁ::

ቅንድቦቹን በመጠኑ ወደላይ ሰብሰብ በማድረግ፣ "እዎ፣ ሰውየው እኔ ነኝ::" ብሎ መለሰልኝ:: በማስከተለም፣ "አንተ ማነህ? ምንስ ትፈልጋለህ?" አለ::

"ከሜጀር ኤስ የተላከ፣ ከርሰዎ ጋር እንድተዋወቅ የተፃፈ ደብዳቤ ይዤ መጥቻለሁ::" በማለት ደብዳቤውን ለመስጠት ወደፊት ራመድ ብዬ ኀንበስ አልኩኝ::

"ህም፣ አሃ! ከሜጀር ኤስ በርግጥ፣ አው! እስኪ ልመልከተው፤ ቁጭ እትልም እንዴ? ሰለግድየለሽነቴ ይቅርታ ፣ ይህ ሀገር ሙቀቱ የሰው መቅኔ ያቀልጣል!"

ይቅርታ ሲጠይቅ ከተቀመጠበት ግማሽ እንደመነሳት ብሎ ነበር:: ወድያውኑ ግን፣ ወደ ነበረበት የሰውነት እቀማመጥ ጥልቅ የእፎይታ ትንፋሽ በመተንፈስ ተመለሰ:: ደብዳቤውን ከማንበቡ በፊት አሳዛኝ በሆነ አመለካከት ተመለከተኝ:: ከተጋደመበት ለመነሳት ምን ያህል እንደተሠቃየም በቂ ምልክት ነበር:: ሶዳ ውሀና ብራንዲ እንዲመጣ በሰውየው ታዞ፣ ጠቆር ባለ የሀገሩ ተወላጅ ቀረበልን:: ለሁለታችንም ርካታ ሠጥቶናል:: እኔም፣ ድንኳንና ሌሎች ራሽኖች እንዲሠጡኝ ጠየቅሁኝ::

---

[2] ፀሀፊው የሰዎችን ስም የመጀመሪያ ፊደል ብቻ ስላስቀመጠ፣ ሙሉ ስም መጥቀስ አልተቻለም:: ይህ ሁኔታ ወደ ፊት በሌሎች ስሞችም ላይ ይታያል::



የጥንታዊው የአዱሊስ ከተማ ፍርስራሽ በዙላ አጠገብ
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

"አ፣ አዎ፣" በማለት ካፒቴኑ መልሰ ሠጠ። "ቀላል ነው፤ ዝርዝሩን ፃፍ፤ የለም፤ እንዲህ ይሁን። መጀመሪያ፣ ወደ ሜጀር ኤክለ ትሄድና ለድንኳንና ለራሽን ትዛዝ ማግኘት አለብህ። ከዚያ በኋላ ችግርም አይኖርብህም።"

ሜጀር ኤክስ፣ የዙላ ሠራዊት አዛዥ እንደሆነም ነገረኝና፣ በመቀጠልም "በጣም ጥሩ የተከበረ ሰው ነው፤ ምለጉን፣ አንደኛ ደረጃ፣ የሚቻለውን ሁሉ ከማድረግ አይቆጠብም።" ለኔ መሆኑ ነው። እኔም እንደዚህ የተመሰገነውን መኮንን ለማየትና ጉዳዬን ለመፈፀም፣ ካፒቴኑን ወደፊት እንደምንገናኝ ምኞቴን በመግለፅ፣ ደህና እርፍድ ብዬ ተሰናበትኩት።

ካፒቴኑ ድምፅ ሲያሰማ ከድንኳኑ እየወጣሁ ነበር። "እኔ የምለው፣ ከኛ ጋር በምግብ ሥፍራችን መመገብ ትችላለህ። በዚህ ካምፕ ውስጥ እስካለህ ድረሰም ራስህን የክብር እንግዳችን አድርገህ መቁጠር ትችላለህ? የተከበሩ መልካም ሰዎችም ታገኛለህ። የኮሚላሪያቱ ኤ፣ ቢ፣ ሽማግሌው መርከበኛ፣ አሁን የማረፈያው ወደብ ሀላፊ፣ ከሶስተኛው ቀላል ፈረሰኞች ደግሞ፣ ሲ አለ። ከዝሆኖች አዝ በኩል ደግሞ ዲ፣ በመጨረሻም፣ ከቦምቤይ ክፍል ኢ አለ። ባክህ ና፤ ትመጣለህ? ርግጠኛ ሁን! አራት፣ ከምሽቱ ሶስት ሰአት፤ ታ-ታ[3]፣ ጓደኛ"

"በርግጠኝነት፣ ውድ ካፒቴን፣ በደስታ ነው የምቀበለው። አርቧር። ታ-ታ ጓደኛ፣" በማለት የዚያን ምለጉን ሜጀር ካምፕ ቦታ ለማግኘት ወጣሁ።

የሜጀሩ ድንኳን፣ ከካፒቴኑ ድንኳን የአንድ ሙሉ ማይል[4] ርቀት አለው። ወደ ሰፍራው ሰሄድም፣ በአለቸጋሪ ሁኔታ፣ በሙቀት የጋለው አሸዋ ጫማዬን እያቃጠለው፣ ነፋሱ ከሙቀቱ ጋራ ፊቴን ሲገርፈው፣ የትሮፒካል ወይም የበረሀ ኑሮ ችግርን ምን እንደሚመስል ተገነዘብኩ። ከበረሀው ሙቀት ሥቃይ ለመተንፈስ ቀዝቃዛ መጠጦችን በየጊዜው ለሚጎነጨው ለዚያ ጀግና ካፒቴንም አዘንኩኝ።

ወደ ሜጀሩ ድንኳን ሰገባ፣ መምጣቴን ለማስታወቅ ሳል ጀመርኩ። ይህም፣ ፊቱ በፂም የተሞላውን ሰው አይን ሳበልኝ። ወደኔ እየመጣም፣ ሌንሱ ወፈር ያለ የአይን መነፀር አይኑ ላይ እያስተካከለ፣ በጥያቄ መልክ ተመለከተኝ። ለዚህ ድምፅ አልባ ጥያቄ ለመመለሰም፣ ማን እንደሆንኩ ራሴን አስተዋውቄ፣ የመጣሁበትን ጉዳይም በመግለፅ፣ የያዝኩትን፣ ተቀብሎ በጥንቃቄ የተመለከተውን ደብዳቤ አስረከብኩኝ። ደብዳቤውን በርካታ ከተመለከተ በኋላም፣ ከፊቱ ላይ በሚነበብ ውጥረት በመላበት አጠያየቅ ምን

---

[3] የአነጋገር ዘይቤ

[4] አንድ ማይል 1.61 ኪሎ ሜትር ነው



እንደምፈልግ ጠየቀኝ። "ብራንዲና ሶዳ፣ ቸሪ ብራንዲ፣ ፖርት ወይን፣ የሎሚ ጭማቂ?" እነዚህን የመሰሉ ርካታ የሚሠጡ መጠጦች፣ በአንግዳ ተቀባዩ ለሰለስ ባለ አንደበት ሲጠሩ መሰማት ብቻ፣ በሙቀት ብዛት አእምሮውን የሳተ መንገደኛን መልሶ ያነቃል።

ሥልጡኖቹ አገልጋዮቹ፣ ገና የሰውየውን ድምፅ ከመሰማታቸው፣ የተጠሩትን መጠጦች በማቅረቢያ ሰሀን ይዘው ወደ ውስጥ መጡ። ሜጀሩ፣ አሜሪካዊነቴን በመገንዘብ ግማሽ ብርጭቆ የሚሆን ብራንዲ ወደኔ መጠጫ ቀዳልኝና ላዩ ላይ ቀዝቃዛ ሶዳ ውሀ ሞላበት። ከሜጀሩ ጋርም ለጤና ተባብለን መጠጫችን አጋጨን። ቀጥሎም፣ መተኪያ የሌለውን የአይን መነፀሩን በጥንቃቄ ቀኝ አይኑ ላይ እያስተካከለ ስለ አሜሪካ ሁኔታ ይጠይቀኝ ጀመረ። "መልካም ነው። እኔ እንኳን ፈኒጋን[5] ነበርኩ ነገር ግን ቴዎድሮስን ለማገልገል እዚህ ድረስ መጥቻለሁ።" በማለት፣ በታቸለኝ አቅም በቀልድ መልክ መለሰኩለት። ሜጀር ኤክስ፣ ባህሪው ፈጠን ያለ ቢሆንም ከአይን መነፀሩ በስተቀር እንከን የሌለው ትልቅ ሰው ነው። በህንድ አገር ታዋቂ ነው። "ኑሮ በጫካ" የተባለው ሰዕሉ የተዋጣለት የሥነ ጥበብ ሥራ ነው።

ከሰአት በኋላ፣ የኔ ድንኳን ከካፔቴን ዚ ድንኳን አጠገብ ተተከለ። አገልጋዬ አሊም ለአምስት ቀናት የሚሆን ራሽን እንዲያመጣ ተላከ። በነጋታው፣ ጥዋት፣ ወደ ግንባር ለመሄድ አሰቤያለሁ። የጓዝ በቅሎ ከኮርቻ ጋር ተሠጠኝ። በዚህም ምክንያት ጉዞዬ ምቾት ያለው ይሆናል ብዬ ተሰፋ አደረኩኝ።

አሜሪካ ብሆን ኖሮ፣ ወይም አውሮፓ ያለ ሠራዊት የምከተል ብሆን ኖሮ፣ ሁኔታው የተሻለ ይሆን ነበር። አፍሪቃ ውስጥ ግን የተለየ ነው። ከሰህተቴ የነቃሁት፣ ከእንግሊዝ ወታደሮች ጋር ዘመቻ ለመሄድ መወሰኔና ለዚህ ቦታ የሚመች ልብሰ አለማወቄን የተገነዘብኩ ጊዜ ነው።

"እኔ የምልህ፣ ሰውየው!" ካፒቴን ዚ ነበር ወደኔ የተጣራው። "ነገ መንገድ ልትጀምር ነው?፤ እንዴት ነው ፈረስና አገልጋዮች የሉህም እንዴ?"

"መልካም፣ ውድ ካፒቴን፣ ራሴን በደንብ አላዘጋጀሁም። እዚህ ከመድረሴ በፊት የሚያስፈልገኝን ነገር አላወቅሁም ነበር። አሁን እንደማየው ግን የሁሉም ነገር እጥረት አለብኝ።"

"በፈጣሪ፣ ያማ የሚሆን አይደለም፤ ታውቃለህ። አዋቂ ሰው የአስፈላጊ ነገሮች እጥረት ሊኖረው አይገባም። ሰንት አገልጋዮች አሉህ?" ብሎ ጠየቀኝ።

"አንድ ብቻ ነው ያለኝ።" በማለት በሀፍረት መለሰኩ።

---

[5] የአየርላንድ ተወላጅ ነኝ ለማለት ይሆን?

"የፈጣሪ ያለህ! አንድ ብቻ፣ ለንትለ ፈረሶች አሉህ?"

"አንድ ፈረስና አንድ በቅሎ፤"


"T T፣ ያ እንኳን የሚያዋጣ አይደለም፡፡ የሚያስፈልግህ ነገር፣ ወጥ ሠሪ፣ ፀጉር አስተካካይ፣ (ኩቻ ዋላ)አስተናጋጅ፣ (ፓኒ ዋላ)ውሀ ተሸካሚ፣ በተጨማሪም የግል ጓዝህን የሚሸከም አንድ ፈረስ፣ የምግብ ማብሰያ ዕቃዎችህን የሚሸከም አንድ ፈረስ፣ ድንኳንህን የሚሸከም ሌላ ፈረስ፣ እና አንተ የምትጋልባቸው ሁለት ፈረሶች ያስፈልጉሃል፡፡ እነዚህ ሳይኖሩህ እዚህ ሀገር መኖር ያስቸግራል፡፡ በተጨማሪም ሰዎች ዝቅ አድርገው ነው የሚመለከቱህ፤ ታውቃለህ አይደል?" በተመሠጠ አለተያየት ተናገረኝ፡፡

"ያም ሆነ ይሁ፣" የቀረ ንግግሩን ሲጨምር፣ "መከበር ከተፈለገ፣ ቢያንስ ቢያንስ ሶስት ነገሮች ሊኖሩህ ይገባል፡፡"


"በርግጥ?" እልኩኝ፤ የግድ፣ የራሴን የመከላከያ ሀሳብ መስጠት ይኖርብኛል በሚል ስሜት፣ "ከዚህ በፊት ብዙ ጉዞዎችን ተሳትፌያለሁ፤ ብዙ የጦር ዘመቻዎችንም ተከትዬ ሄጃለሁ፤ ከነዚህ ቀደም ካሉ ጉዞ ልምዶች እንዳየሁት፣ የምፈልገውንና መያዝ የሚገባኝን ነገር ያወቅሁ መስሎኛል፡፡ ወደ አቢሲኒያ ለመምጣት ስነሳ፣ ሰር ሮበርት ናፒየር አንድ ቦታ ላይ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ አልመሰለኝም፤ እንዲያውም፣ በተቻለ መጠን ዘመቻውን በፍጥነት የሚቀጥል ነው የመሰለኝ፤ በዚህ ሁኔታ ትርፍ ጓዝ መያዝ ለአንድ ሰው የሚያጓትት ነገር ነው፡፡"

"እሃ፣ አያስፈልጉኝም የምትለው አንድ አስራ ሁለት አገልጋዮች፣ ወደ ስድስት የሚሆኑ ፈረሶች፣ ላንተ ብዙ ናቸው ነው ወይ?፤ እንደዚህ የምታስብ ከሆነ ስለ ሀገሩም ሆነ ስለ እንግሊዝና ህንድ ጥምር ሠራዊት እና ስለሚያስፈልጉት ነገሮች እውቀቱ የለህም፡፡"

የኋለኛው ንግግር እንኳን ማታ ራት ላይ የተለዋወጥነው ነበር፡፡ ቀን፣ ካምፑ ውሰጥ እንዳስተዋልኩት ከሆነ፣ በርካታ አገልጋዮች መኖራቸውን ተገንዝቤያለሁ፡፡ እንደ እንግሊዞቹ የህንድ አኗኗር ከሆነ፣ እነዚህ አገልጋዮች በጣም አስፈላጊ መሆናቸውን አንድ ሰው መረዳት ይችላል፡፡ ለአገልጋዮቹ ቁጥር መበርከት ሌላው ምክንያት ደግሞ፣ የህንድ አገልጋይ ሲቀጠር፣ ለአንድ አይነት ሙያ ብቻ ይሆንና፣ ሠራተኛውም ያችኑ ሥራውን ብቻ ስለሚሠራ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የፈረሶች ባልደረባ፣ የግልቢያ ፈረሶችን መንከባከብና ማዘጋጀት ነው ሥራው፡፡ ሁሉም እንደ አቀጣጠራቸው፣ ውሀ አቅራቢው ውሀ ማቅረብና መሸከም፣ ፀጉር ቆራጩ ቢበዛ ሣር ቢያጭድ ነው፡፡ እነዚህ ሠራተኞች እያንዳንዳቸው፣ አንዱ ያልተቀጠረበትን የሌላውን ሥራ ቢሠራ እንደ ነውር ነው የሚቆጥሩት፡፡



የአርምስትሮንግ መድፎች ሲጫኑ



የተራራ ከባድ መሳሪያዎች ሲጫኑ

(ዋቢ. መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

እንግዲህ ለነዚህ የእንግሊዝ ወታደሮች በዚህ በዙላ አሸዋ ላይ መሰብሰብ ምክንያት የሆኑ ነገሮችና ሁኔታዎችን መግለፅ ከርዕስ ውጭ አይሆንም፡፡

በአቢሲኒያ ለብዙ አመታት ከትውልድ ትውልድ እየተቀባበለ የሚነገር ትንቢት ነበር፤ ይህም ትንቢት እየጠነከረ በመምጣቱ፣ የሀገሩ ተወላጆች ወቅቱና ጊዜው ደርሷል በሚል አምነት የተነገረለት አዳኝ ሰው መምጫው አሁን ነው በማለት መጠበቅ ጀመሩ[6]፡፡ ይህን ትንቢት፣ ካሳ የተባለ ልቡ ትልቅ የሆነ ወጣት፤ ባሏ የሞተባት፣ ከደምቢያ ወደ ምዕራብ በኩል ቋራ በሚባል ቦታ የምትኖር፣ ኮሶ ሻጭ ሴት አንድ ወንድ ልጅ መስማት ጀመረ፡፡ ይህ ትንቢት በየቀኑና በየወሩ በጆሮው ይወርድ ጀመር፡፡ በህልሙ ሆነ በገሀድ፣ ይህ ትንቢት ይከነክነውና ያሳድደው ጀመር፡፡ በመጨረሻም፣ ኢየሩሳሌምን ከሙስሊሞች ለማዳን የተመረጠው ሰው እሱ ራሱ ነው የሚል አምነት አደረበት፡፡

ትንቢቱም እንደዚህ ነበር፡፡

*“ በኢትዮጵያ የሰለሞን ሀረግ[7] ወይም ትውልድ ያለው ንጉሥ ይነግሣል፡፡ በምድር ላይም ታላቅነቱ ይታወቃል፡፡ ሀይሉም በኢትዮጵያና በግብፅ ላይ ይንሰራፋል፡፡ አረመኔዎችን ከፍልስጥኤም ጠርጎ ያወጣል፤ ኢየሩሳሌምንም ከደፈሯት ሰዎች ያነፃታል፤ ስሙም ቴዎድሮስ ይባላል!”[8]*

ካሳ፣ የደምቢያው ገዥ የደጃች ክንፉ ቤተሰብ ስለሆነ ትምህርት እንዲማር ይደረጋል፡፡ ዝምድና ባይኖረው ኖሮ ምንም ማዕረግ ለሌለው ለዚህ ወጣት ይህ አይነት ዕድል ባላጋጠመው ነበር፡፡ ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ[9]፣ በዚያ ጊዜ በማንበብና መፃፍ የተወሰነ ብቻ ነበር[10]፣ በደጃች ክንፉ ጦር ሥር ለማገልገል ይመለመላል:: ይህም በፍጥነት ዕድገትና ማዕረግ እንደሚያስገኝለት ቃል ስለተገባለት ነው፡፡ ወዲያውኑ፣ ትልቅ ችሎታ እንዳለው ግልፅ መሆን

[6] ህዝቡ ይህን አይነት ትንቢት የተቀበለበት (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[7] አፄ ቴዎድሮስ፣ ባባታቸው (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[8] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[9] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[10] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)



ጀመረ፡፡ የጦር ችሎታው፣ የደጃች ክንፉን የጋለ አድናቆትን አተረፈለት፡፡ ክንፉም የሻምበልነት ማዕረግ በመሥጠት፤ የሚተማመኑበትና የሚያምኑት ተከታያቸው አድርገው ወሰዱት[11]፡፡ ጀግንነት፣ በበጌምድርና በአካባቢው ግዛቶች በተደረጉ ከባድ ፍልሚያ በታየባቸው ዘመቻዎች፣ በፍጥነት የጦር ሜዳ ወይም የውጊያ አሰላለፍ የመገንዘብ ችሎታው ዕድገቱን በጣም አፋጠነለት፡፡ ይህ ችሎታውም የነበረውን ገዥ[12] ክብር ስላስገኘለት፤ ገዥው ሴት ልጁን በመዳር የወረዳ ገዥነት ማዕረግ ሠጠው፡፡

በጥንቃቄና በታማኝነት ካገለገለ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፤ ካሳ በድንገት ከገዥው ጋር በመጣላት ጦርነት ያውጃል፡፡

በደጃዝማች የሚመራ ጦር አመፀኛው ካሳ ላይ ይዘምታል፡፡ ሆኖም፣ ከሀይለኛ ውጊያ በኋላ ጦራቸው ተሸነፎ ብዙ ሰዎች ያልቃሉ፤ ራሳቸው ደጃዝማቹም በካሳ እጅ ሕይወታቸው ያልፋል፡፡ ካሳም፣ ከዛ በኋላ አንዳንድ ሠንገደኛ ፀሐፊዎች እንደሚጠቅሱት፣ ወደ ሰልሳ ሺ የሚሆኑ ተከታዮችን ይዞ ወደ ጎንደር ይገሰግሳል፡፡ የከተማው ኗሪዎችም ያለ ምንም ደም መፋሰስ ለአዲሱ ባለጉልበት ከተማውን ያስረክባሉ፡፡ ከዚህ ድል በኋላም የጎንደር ገዥነቱን አስታውቆ፤ ያሠለጠናቸውን ወታደሮቹን በማዝመት የአካባቢ ግዛቶችን አንድ በአንድ በማንበርከክ በተሸነፉት ገዥዎች ምትክ የራሱን ታማኝ ሰዎች፣ የጦር መኮንኖቹን መሾም ጀመረ፡፡

በጦርነት ላይ ባሳየው ጀግንነትና[13] ድንቅ በተባለ ፍጥነቱ፤ በዘመኑ በአንዳንዶች፣ ከፈጣሪ እንደተሠጠ ችሎታ በመቆጠሩ፤ ካሳ በገዥነቱ ወንበር ላይ ራሱን አደላደለ፡፡ ከአንድ ሙሉ አመት ሰላም በኋላ፤ ካሳ ተከታዮቹን በውትድርና ካሠለጠነና ለጦርነት እንዲዘጋጁ ካደረገ በኋላ፤ ከበጌምድሩ ገዥ ጋራ የሚጣላበት ሰበብ ያገኛል፡፡ ወደፊትም ጦሩን ያዘምትና በዚህ ተራራማ በሆነ ግዛት ተደጋጋሚ ድል ይቀዳጃል፡፡ በገዥው ስር የነበሩ የበጌምድር ወታደሮችም ድል ተመተው በካሳ ሰይፍ እጅ ይወድቃሉ፡፡ ገዠው ግን በካሳ ትዛዝ ለእስር ይዳረጋል[14]፡፡ የዚህ ድል ወሬ በየቦታው ሲናፈስ፤ የአጎራባች ገዥዎች ካሳን የጋራ ጠላት ያደርጋሉ፡፡

እነዚህ ቁጥራቸው የላቀ ጠላቶቹን ከመግጠሙ በፊት፣ የራሱን ጦር በሚገባ ያጠናክራል፡፡ ከንጉሥ ሰለሞን የዘር ሀረግ በመጥቀስ ራሱን

[11] ክንፉ፣ ካሳን የልጃቻቸው ጣውንት አደርገው ነበር የሚቆጥሩት፡፡ አዋቂ ሲጠየቅ የሚወርሰው ካሳ ነው እንጂ ልጆችህ አይደሉም ብሎ ነግሯቸዋል ይባላል፡፡

[12] ትንሹ ራስ አሊ (ተዋቦችን የሰጡት እያትየዋ ወይዘሮ መነን ናቸው)

[13] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[14] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

ቴዎድሮስ፣ በተወላጆቹ አጠራር ቴድሮስ[15]፣ ብሎ በመሰየም ትንቢቱ የተነገረለት የመሐመዳን መንግሥቶችን ጠርጎ የሚያጠፋው አዳኝ እሱ እንደሆነ ያስነግራል፡፡

ይህ አዋጅ ግን እሱ ካሰበው በላይ ትልቅና ሰፊ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡ ተዋጊዎች፣ በየአካባባዊ የነበሩበትን ጦር እየከዱ፣ ወደፊት የሚመጣውን የቴዎድሮስን ድል በማለብ፣ በሱ ስር ለመዋጋት በገፍ መቀላቀል ጀመሩ፡፡ ይህ ትልቅ ሀሳብ በቴዎድሮስ ሲነገር ሲሰሙ፣ ጠላቶች የሆኑት ገዥዎች በመሳቅ እንደፌዝ ይቆጥሩት ጀመር፡፡ ነገር ግን እየከዳቸው በሚሄደው የራላቸው ሠራዊት ምክንያት ርቃናቸውን መቅረታቸውን ሲረዱና በሰላዮቻቸው አማካኝነት በሚያገኙት መረጃ ምኞተ ሩቁ ጠላታቸው ሀይሉ እየተጠናከረ መምጣቱን ሲገነዘቡ ሹፈቱን ቀየሩ፡፡ አንዳንዶቹ መሳሪያቸውን አውርደው በሰላም ገባሪነታቸውን አሰታወቁ፤ አንዳንዶች ደግሞ፣ ፊት ለፊት መጋጠም የወሰኑት፣ ተራ በተራ ድል እየተመቱ በሕይወት የተረፉት የቁም መቃብር በሆነው በጌምድር ተራራ እሰር ቤት ከበጌምድሩ ገዥ ጋር ተደረቡ፡፡ አንድ ባንድ እያንዳንዱ በአቢሲኒያ የሚገኝ ግዛት ከትግራይ[16] በስተቀር ለቴዎድሮስ ተገዥ ሆነ፡፡ ከዚህ ድል በኋላ ራሳቸውን ዳግማዊ ቴዎድሮስ ሰዩመ እግዚአብሔር በማለት አወጁ[17]፡፡ ይህ የሆነው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1851 ነው፡፡[18]

ራሳቸውን የድፍን አቢሲኒያ ገዥ ሲያደርጉ የሰላሳ አምስት አመት ጎልማሳ ነበሩ፡፡ በዚህ ዕድሜ፣ ጠንካራ ሰውነት[19]፣ እንደ ግሥላ ፈጣን፣ እንደ አንበሳ ደፋር፣ የተወደዱና፣ በሁሉም ተዋጊ ወታደሮች ዘንድ በፍቅር የሚታዩ ሰው ነበሩ፡፡[20]

በታሪክና በልምድ ስላለፉት መንግሥታት የተማሩትን፣ ራሳቸውም በልምድ የደረሱበትን የኢትዮጵያ ነገሥታትን የውስጥ ሸርና አደጋ በማጤን የጎንደር ቤተመንግሥትን ኑሮን መጥላት ጀመሩ፡፡ ለራሳቸውም "መናገሻ ከተማ አይኖረኝም፤ ራሴ መንግሥት ይሆናል፤ ድንኳኔም መናገሻ ይሆናል፡፡" ብለው ወሰኑ፡፡

---

[15] ስለ ንግሥና ስማቸው (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[16] ቴዎድሮስ ትግራይ ላይ ያልዘመቱት፣ የሰሜኑን ገዢ ደጃች ውቤን ድል በማድረጋቸው ፣ በውቤ ስር የነበረው ትግራይ በእጃቸው ስለወደቀ ነው፡፡

[17] ከዚህ በኃላ እንደአግባቡ አርሳቸው ማለት ተገቢ ነው፡፡

[18] ሰኔ ሀያ ሶስት፣ 1845 (እኢአ)(በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[19] ስለ ሰውነታቸው ጥንካሬ ሲነሳ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[20] ቴዎድሮስን ተወዳጅ ሊያደርጓቸው የቻሉ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)



ያላቸው የተፈጥሮ ብልህነትና የወታደራዊ ችሎታቸው በየጊዜው የተነሡትን አመፆች ፀጥ ማድረግ አስችሏቸዋል፡፡ የአሮሞ አመፀኞች[21] በየጊዜው ድል ተመተዋል፤ ነገር ግን በአንድ ቦታ ሰክነው የማይቀመጡ ስለሆነ፤ የተቀዳጇቸውን ድሎች ውጤት አላሳመሯቸውም፡፡ ስማቸው ግን የሚፈራ ሆነ፡፡ በስማቸው ብቻም ሰላም የመፍጠር ችሎታ እንዲኖረው ተጠቀሙበት፡፡

ነጋዴዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ተጋበዙ፤ የእጅ ባለሙያተኞች ደግሞ እንዲበረታቱ ተደረገ፡፡ [22]የአውሮፓ ባለሙያተኞች ስለዚህ ዕደገት ፈላጊ ሰው ሲሰሙ ወደ ጎንደር ይጎርፉ ጀመር፤ በጎንደርም ቅጥር ሥራ(ባለሟልነት)፣ ቀረቤታና ሀብትም ይሠጣቸው ጀመር፡፡ የጦር ሙያተኞች ከሆኑ ደግሞ የተለየ እንክብካቤ ይደረግላቸው ነበር፡፡ ብዙዎቹም ሀገሪቷ ውስጥ እንዲኖሩ የተጋበዙ መንገደኞች ነበሩ፡፡

ቆንስል ፕላውደን[23]፣ የቅርብ ወዳጅ ስለነበር ከቴዎድሮስ ጋር ለአምስት አመታት አብሮ ኖሯል፤ በዚህ ጊዜ፣ ንጉሡ በተቻላቸው አቅምና በሚቻለው መንገድ ሁሉ ሀይላቸውን ያጠናከሩበትና መንግሥትን ያደራጁበት ጊዜ ነበር፡፡ ምንም እንኳን በጊዜው ከራላቸው ሰዎች የላቁ ዘመናዊ ወታደር ቢሆኑም፣ ባገኟቸው ድሎች ተጠቅመው የሀገሩን ተወላጆች ፍላጎት[24] ማሟላቱን አላወቁበትም ነበር፡፡ አንዱን ግዛት ሲያሰገብሩ ሌላው እያመፀ፤ በማያባራ ሁከት ተወጠሩ፤ ይህም ቀስ በቀስ የነበራቸው ባህሪ እንዲለወጥ አስገድዷቸዋል፡፡ በሙሉ ልብ፣ ያለማሰለስ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የሚያደርጉትን ጥረትና ድካም ከምንም ያልቆጠሩት ምሲጋና ቢስ ሰዎቻቸው ላይ የመረረ ስሜት ፈጠረባቸው፡፡[25]

ጥቂት ምስኮቦችና የጀርመን መሐንዲሶችም ወደ ሀገሪቱ በመግባት ባለሟልነት ጠየቁ፡፡ መስራት የሚችሏቸውን ትልልቅ መድፎችና መተኮሻዎች በነገሯቸው ጊዜም፣ በአእምሯቸው የሚያስቡትን የግብፅ፣ የፍልስጥኤምና የአረብ አገሮችን ማሸነፍ የሚችሉበት ጊዜ እየተቃረበ መጥቷል በሚል እምነት በሀሲናቸው እንዲስሉ አደረጓቸው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ እኒህ ድንቅና ሩቅ አላሚ

---

[21] አመፅ ከተነሳ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[22] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[23] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[24] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[25] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

ንጉሥ እነዚህን አስደናቂ መሣሪያዎች ካገኙ ምኞታቸው እንደሚሳካ በማመን ወዲያውኑ ከመሐንዲሶቹ ጋር ተስማሙ::

ትልልቅ የባሩድ ማምረቻ ቦታዎች ተገነቡ:: የግሪክ ነጋዴዎች ለንጉሡ ጠመንጃ ገዥ እንዲሆኑ ተደረገ፤ የመድፍ መሥሪያ የሚሆኑ ማቅለጫዎች[26] ተሠሩ፤ ሁሉም ነገር ለሳቸው ብልፅግናና ተስፋ በሚሠጥ መንገድ ተዋቀረ::

ቴዎድሮስ፣ የግብፁን ገዥ እንደ ዋነኛ ጠላታቸው አድርገው ነው ያዩት[27]:: ወራሪነትና ጠብ አጫሪነት በግብፆች በኩል ተደጋግሞ ነበር የሚፈፀመው:: ግብፆች የማረኳቸውን ኢትዮጵያውያኖች ደግሞ ወደ ናይል በመውሰድ በካይሮና በእስከላንድርያ ለሚኖሩ ፓሻዎች በባርነት ይሸጡ ነበር:: የቀሩትንም በመርከብ ወደ ሩቅ ወንድሞቻቸው ወደ ኮንስታንቲኖፕል ይልኳቸው ነበር:: በግብፆች የተፈፀሙት በደሎች እነዚህ ብቻ አልነበሩም:: ይህንንም፣ ቆንስሉ ፕላውደን፣ በታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ፅሕፈት ቤት እንዲታወቅ አድርጓል::

ፕላውደን ለቆንስላነት ሲሾም በግልፅ መታወቅ ያለበት ነገር ሹመቱ ለአቢሲኒያ ነው የነበረው፤ ለለዚህም አቋሙ ከገዥው ንጉሥ ጋር ነው የነበረው:: ገዥው ንጉሥም አፄ ቴዎድሮስ ሆኑ:: በነበረው በጎ ሀላብና፣ በእንግሊዝ መንግሥትና በቴዎድሮስ መካከል ግንኙነትና ወዳጅነት ለመመስረት ብርቱ ፍላጎት፣ የቴዎድሮስን ፍቅርና መልካም አስተያዬት ሊያገኝ ችሏል:: በመሀል ኢትዮጵያ፣ የሱ ስራ የነበረው ከውጭ የሚመጣውን ሸርና ተንኮል መከታተልና ማከሸፍ፤ የባሪያ ንግድን ማስቆምና በተቻለው መጠን ንግድ እንዲስፋፋ ማድረግ ነበር:: ከእነዚህ ግቦቹ ለመድረስ ቴዎድሮስን ወደ እንግሊዝ አገር አምባሳደር እንዲልኩ ይወተውት ነበር:: በዚህም ልዑካኑ በሁለት አገሮች መሀከል የንግድ ግንኙነት መፍጠሩ ሊኖረው የሚችለውን ጥቅም በቀጥታ እንዲያዩ አስቦ ነው:: አፄው ግን በማያባራ ጦርነት ስለተጠመዱ የዚህን ጉዳይ ራሱ ፕላውደን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ሀላፊነት ሰጡት::

ቆንስል ፕላውደን ግን እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1860 ወደ ምፅዋ በሚጓዝበት ጊዜ በሽፍቶች ተገደለ[28]:: ቴዎድሮስ መሪር ሀዘን ተሰምቷቸው የቆንስላውን ገዳዮች በቅጣት ተበቀሉ:: ለቆንስላው ባሳዩት ደግነት፤ የእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶርያ የተለያዩ ሥጦታዎችን የላከች ስትሆን፤

[26] ቴዎድሮስ ማቅለጫዎቹን ሲጎበኙ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[27] ቴዎድሮስ፣ ቱርኮችንም ሆነ ግብፆችን (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[28] ቆንስላው የተገደለው በጋረድ ከንቶ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)



ከስጦታዎች አንዱ ሽጉጥ ነበር:: በሽጉጡም ላይ እንዲህ የሚል ፅሁፍ ተቀርፆበት ነበር:: "ለአቢሲኒያ ንጉሥ ለአፄ ቴዎድሮስ፣ ለአግልጋዩዋ ለፕላውደን ለተደረገለት ደግነት፣ ከቪክቶርያ፣ የእንግሊዝና የአየርላንድ ንግሥት የተሠጠ፣ 1861" ይህ ሥጦታ የተላከው በፕላውደን ተከታይ በካፒቴን ካሜሩን አማካኝነት ነበር:: ካሜሩን የተከበረ ሰውና ከዚህ ቀደም በንግስቲቱ ሥር በካፒቴን ማዕረግ በህንድ ሲያገለግል የነበረ ነው::

ቴዎድሮስ መድፍ የመስራት አላማቸውን[29] በመከተላቸው፤ አንድ በአንድ እያሉ መድፎቹ ከማቅለጫው እየተሰሩ ይወጡ ጀመር፤ በሚፈተሹበትም ጊዜ የቴዎድሮስን ያልተገደበ ደስታ በሚያስገኝ ሁኔታ አስፈሪ የሆኑ የውጊያ መሳሪያዎች ለመሆናቸው በሚያሰሙት ድምፅና ከሰፊው አፈሙዛቸው በሚወረወሩት ትልቅ አሩሮች ተረጋገጠ:: በርግጥም በነዚህ የተረገሙ ግብፆች ላይ ጦርነት የሚከፈትበት ቀን እየቀረበ መጣ::[30]

ግብፅ በአባስ ፓሻ ስር እያለች በጣም ድሃና ስርአት ያጣች ሀገር ነበረች:: ሰዒድ ፓሻ ወደ ዙፋኑ በወጣበት ጊዜ ግን ሁኔታዎች ሁሉ ተሻሽለው በጊዜው ሀይለኛ ሀገር ለመሆን በቅታለች::

በየካቲት 9፣ 1862 እኤአ፣ አዲሱ ቆንስል ካፒቴን ካሜሩን ወደ አቢሲኒያ በመምጣት ከንጉሡ ፊት ቀርቦ የተሾመበትን ደብዳቤ አቀረበ፤ የተሻለም የሆነው ይዞ የመጣቸውን ሥጦታ ሲያበረክት ነበር:: ቴዎድሮስ ንጉሣዊ ልብስ እንደለበሱ፣ ከተሰያዩ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር በመሆን ነበር የተቀበሉት::

ለፕላውደን እንደተደረገው፣ ተመሳሳይ ቀረቤታና ወዳጅነት ለካሜሩንም ተሠጥቶት ሁሉም ነገር ለጊዜው በሰላም ቀጠለ:: ወድያውኑም፣ ሚሲዮናውያኑ ቄሶቹ፣ ሚስተር ስተርንና ሚስተር ሮዘንታልም ተከትለው ሲመጡ፣ ተመሳሳይ አቀባበልና አቀራረብ ተደረገላቸው:: ሌሎች ሚሲዮናውያንም ቀስ በቀስ መግባት ጀመሩ፤ እነዚህም ከስኮትላንድ ሚሲዮን እና ክርስትናን በአይሁዳውያን ከሚያስፋፉ ማህበራት አባሎች ነበሩበት:: እነሱንም ቢሆን፣ ንጉሡ በመልካም ሁኔታ ነበር የተቀበሏቸው::

በዚህ ጊዜ ግን የንጉሡ ጭካኔ እየጨመረ መጣ:: በየግዛቱ የሚነሳው አመፅ ህይወታቸውን መሪር እንዲሆን ሲያደርገው፤ መላ ተፈጥሯቸውን ወደ ጭካኔና ሀይለኝነት እንዲቀየር አደረገው:: ትዕግስት ማጣርና ግንፍልነተኝነት ዋና ባህሪ እየሆኑ መጡ:: በዚህም ምክንያት የቅጣቱ አይነትም ክረር እያለ

[29] አፄ ቴዎድሮስ በተፈጥሯቸው ፈጠራም የሚወዱ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[30] ቴዎድሮስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመዝመት (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

መጣ፡፡ የከዱ ሰዎች ግንባራቸው ላይ ምልክት ይደረግባቸው ጀመር፤ ሌሎቹንም በአደባባይ መሬት ላይ አስተኝቶ በጦር መውጋት ተጀመረ፡፡

እገር ወይም መሪዎችን የሚከዱን ሰዎች ከፍተኛ አሰቃቂ ቅጣት መቅጣት[31] በታሪክ በሠለጠነ በሚባለው የአለም ክፍልም የተለመደ ነው፤ የቴዎድሮስን የተለየ የሚያደርገው፣ ቅጣቱ፣ ንፁህን ሰዎችንም ስለሚጨመር ነው፡፡ ቅጣቱ እየከፋ በመምጣቱ በጅራፍ የሚገረፈው፣ በጥይት የሚደበደው ሰው ቁጥር እየጨመረ መጣ፤ በዚህ ምክንያትም ሰማቸው በዜጎቹ ዘንድ መጠላት ጀመረ፡፡

የእንግሊዝ ቆንስላ ወደ አቢሲኒያ ከመምጣቱ ከጥቂት ጊዜ በፊት፤ ሎርድ ራሰል[32] በኢየሩሳሌም ለሚገኙ የኢትዮጵያ ገዳማት የነበረውን የእንግሊዝ ጠባቂነት አነሳ[33]፡፡ እንግዲህ በዚህ ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት ውጭ እያወጣ ከኢትዮጵያ ንጉሥ ጋር ወዳጅነት ለመመስረት ልዑካን በሚልክበት ጊዜ ራሰል ግን ተቃራኒውን ነበር ያደረገው፡፡

አዲሱ ቆንስላ ካሜሩንም የቀደሙን ቆንስላ ዱካ በመከተል፣ በሁለቱ አገሮች፣ በኢትዮጵያና በእንግሊዝ መንግሥት የወዳጅነት ውል ወይም ስምምነት እንዲፈጠር፤ በተጨማሪም ወደ እንግሊዝ ንግሥት አምባሳደር እንዲላክ ንጉሡን ይገፋፋ ነበር፡፡

በመጨረሻም ቴዎድሮስ ለጉዳዩ ግንዛቤ መስጠት ጀመሩ፡፡ ለንግሥት ቪክቶርያም ደብዳቤ ላኩ፡፡ በደብዳቤውም የተለመደው የኢትዮጵያ ነገሥታት መግቢያ ፅሁፍ በኋላ፤ ቱርኮችን(ግብፆችን) ለማጥቃት ያላቸውን ሃሳብ ግልፅ አደረጉ፡፡ ይህም፣ እነዚህ ጠላቶቻቸው ያለምንም ሰበብ ኢትዮጵያውያን ላይ፣ ቦጎስ የሚባል ቦታ ጥቃት በመፈፀማቸው፤ ምክንያት የሌላቸውና ህጋዊ ያልሆኑ በተደጋጋሚ[34] የሚያደርጓቸው ወረራና ጥፋቶች፤ ሌሎችም ተጨማሪ ጥቃቶችን በማካተት ነው፡፡ በዚሁ ደብዳቤም፣ ተስፋው ለሁለቱም እገሮች ጥቅምና ዝና በሚፈጥር ሁኔታ፣ በሁለቱ እገሮች መካከል ዘላቂ የሆነ ወዳጅነት እንዲኖር ምኞታቸው እንደሆነ በመግለፅ፤ ንግሥቷ የላቸው አምባሳደሮች ወደ እንግሊዝ አገር የሚመጡበትን ሁኔታ እንዲዘጋጅ እንድታደርግ በመጠየቅ፤ በተቻለ ፍጥነት ትውውቅ ለማድረግ ሁሉም ነገር ዝግጁ እንደሆነ፤ ልዑካኑም ወደ ባህር ወደብ እንደሚላኩ ነው፡፡

---

[31] ስለ ቴዎድሮስ ጭካኔ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[32] ሎርድ ራሰል የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[33] በዚህ ምክንያት በኢየሩሳሌም ገዳማት (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[34] የባርካ ነዋሪዎች(በግብፅ ስር) (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)



ቆንስል ካሜሩን ይህን ደብዳቤ እንደያዘ ወደ ምፅዋ በሚሄድበት ጊዜ በአንድ ሽፍታ መሪ ቢያዝም በስውር በሀገሩ ተወላጆች በኩል የንጉሡን ደብዳቤ ማሳለፍ ችሏል፡፡

ደብዳቤውም፣ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር የካቲት 1863 በሰላም ሎንደን ይደርሳል፡፡ ደበዳበቤውን የተቀበለው ራሰል፣ ከፍቶ ካነበበ በኋላ ጠረጴዛ ላይ ወርውሮ በመተዉ ምክንያት ደብዳቤው ፋይዳ ሳይሰጠው ያልሆነ ቦታ ተቆጣጥሮ ቀረ፡፡[35]

ቆንስል ካሜሮን ከአጭር ጊዜ እስር በኋላ በሽፍቶቹ ተለቀቀ፡፡ ከዚያ በኋላም የባሪያ ንግድ እንዳይኖር ወይም እንዲቆም ለፓሻዎች የእግር እሾህ እስከሆን ድረስ መታገሉን ቀጠለ፡፡ በዚህም ምክንያት መልክተኞችና ሰሞታ ከሳሾች ወደ ራሰል ይላኩ ጀመር፡፡ ለተሰማው ችግር፣ ለይድ ፓሻ፣ እንዲሰናና ተደርጎ፣ ቆንሰል ካሜሩን በቀጥታ ወደ ምፅዋ እንዲሄድና እዛ ሆኖ የቆንስላ ጉዳዮቹን ብቻ እንዲመለከት ይታዘዛል፡፡

ብዙም ሳይቆይ በአሜሪካ የሚደረገው ጦርነት እንግሊዞችን እያሳሰባቸው ስለመጣ፤ አዲስ የጥጥ እርሻ በጉጉት የሚፈለግበት ጊዜ በመሆኑ፣ የውጭ ጉዳይ ፅህፈት ቤቱ ካሜሩን ወደ ሱዳን ሄዶ ሀገሩ ለጥጥ ምርት ያለውን ቁጥጥሩና አመቺነት እንዲያጠና ትዛዝ ያስተላልፋል፡፡

የካሜሩን ወደ ግብፅ[36] ግዛት መሄድ በቴዎድሮስ በኩል የተለየ ትርጉም ነው የተሠጠው፡፡ በሚመለሰበት ጊዜም፣ አፄ ቴዎድሮስ በማፋጠጥ መልከ ካሜሩን የት እንደከረመ ይጠይቃሉ፡፡ ካሜሩንም ወደ ሱዳን ተልኮ የጥጥ እርሻና ንግድ ሁኔታ እንዲያጠና እንደተጠየቀ ምላሽ ይሰጣል፡፡ ቴዎድሮሰም በአንድ አመት በፊት ለንግሥቲቱ ለላኩት ደብዳቤ ምላሽ ይዞ መጥቶ እንደሆን ይጠይቃሉ፡፡ ካሜሩን በእሉታዊ ሲመልስ ቴዎድሮስ በጣም ተናደዱ፤ እሃ! ንግስቲቱ ጠላቶች ወደሆኑት ወደ ቱርኮች ስትልክህ ምናልባትም በላቸው ላይ ሴራ እስባ ቢሆን ነው እንጂ እንዴት ለመሪ የሚገባውን ህጋዊ ደብዳቤ አትሰፍም፤ ስለዚህ የደብዳቤው መልስ እስኪመጣ ድረስ ካሜሩን መንቀሳቀስ አይችልም፡፡ በዚህ ምክንያት፣ በሐምሌ 1863 ካሜሩን እስረኛ ሆነ፡፡ ብዙ ሳይቆይ፤ ከፈረንሳይ መንግሥት መልስ መጣ፡፡

---

[35] ይህ ሁኔታ የንቀት ብቻ ሳይሆን፣ እንግሊዞቹ በዚያን ጊዜ በሩስያ በኩል የነበረውን ፉክክርና ንግድ መስፋፋት ለማስቆም የቱርክን እርዳታ ይፈልጉ ነበር፡፡ ስለዚህ ከቱርክ ጋር መጋጨት አልፈለጉትም፡፡ ቴዎድሮስ የቱርኮች ጠላት ነበሩ፡፡

[36] ሱዳን በግብፅ ፓሻዎች ስር ስትዳደር ነበር

የደብዳቤው ይዘት የሚያረካ ስላልነበር የፈረንሳዮ ቆንስላ መንሲንጀር[37] በአስቸኳይ ከአቢሲኒያ እንዲወጣ ተደረገ:: ከሶስት ወራት እስራት በኋላ፣ ካሜሩን ከሎርድ ራስል መልስ ተላከለት::

ነገር ግን፣ በዕድሜ ገፋ ያለው ባለሥልጣን የረሳው ትልቅ ነጥብ ነበር:: በደብዳቤው ቴዎድሮስን ለለመጠየቅ የተገለፀ ነገር የለም፤ እንዲያውም የቴዎድሮስን ስም የሚጠቅስ አንድ ቃል እንኳን አልነበረበትም:: በጉዳዩ የበገኑት ቴዎድሮስ የካሜሩን አገልጋይ እንዲደበደብ ትዛዝ ይሰጣሉ:: በዚህ ጊዜም የሚሲዮናዊው ሁለት አገልጋዮችም በከፉ ሁኔታ ስለተደበደቡ ማምሻውኑ ህይወታቸው አለፈ:: በዚህ የተደናገጠው [38]ሚሲዮናዊ ስተርን አፉን በአጁ ሲሸፍን ያዩት ቴዎድሮስ የድፍረት ስለመሳለቸው፣ "ይህን ሰው መሬት ላይ ወርውራችሁ እንደ ውሻ ደብድቡልኝ" ብለው ትዛዝ ከመሰጠታቸው ወታደሮቹ ራሱን አስኪስት ድረስ ደበደቡት:: ከዚህ ከጥቅምት ወር፣ የስተርን የረጅም ጊዜ እስራቱ ይጀምራል::

የቴዎድሮስ ባለሟል የሆነ ባርደል[39] የሚባል ፈረንሳዊ ነበር:: ለእንግሊዞቹ ያለው ጥላቻ ከፍ ያለ ስለነበር የነዚህ ሰዎች ወደ ሀገር የመጡበትን አውነተኛ ጉዳይ ለማወቅ ሳጥኖቻቸውና ደብዳቤዎቻቸው እንዲፈተሹ ለቴዎድሮስ ሃሳብ ይለግሳል::

ቴዎድሮስ፣ ሁሉንም በአቢሲኒያ የሚኖር አውሮፓዊ፣ በተለይም እንግሊዞችን በጥርጣሬ ነበር የሚያዩት:: የንግሥት ቪክቶርያ ለደብዳቤያቸው ምላሽ አለመሰጠት በነስተርን ውክልና ምክንያት ነው፤ የፈረንሳዩ አፄ ናፖሊዮን የምን ግዴ አፃፃፍ ደብዳቤም የአውሮፓ ሸር ነው፤ በማለት ነበር ቴዎድሮስ ሀሳባቸውን የደመደሙት:: እንደውነቱ ከሆነ እንደዚህ ለማሰብ በቂ ምክንያት ነበር::[40]

በምፅዋ፣ የቆንስል ካሜሩን ምክትል ካፒቴን ቻርለስ ሰፒዲ የሚባል ቁመቱ ስድስት ጫማ ከሰድሰት ኢንች የሆነ ግዙፍ ሰው ነበር:: ለአንድ አመት የሚሆን የቆንስላ ስራ ከሰራ በኋላ አርግፍ አድርጎ ትቶ፣ ዝሆን አዳኝ ለመሆን ወደ መሀል አቢሲኒያ ይዘልቃል:: ከሱም ጋር በትውልዱ አየርላንዳዊ የሆነ፣ የዘመዱ ልጅ፣ ከረንስ የሚባል ወጣት አብሮት ነበር:: ሁለቱም በአዳኝነቱ

[37] የአፄ ናፖሊዮን ወይም የፈረንሳዮቹ ፍላጎት (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)


[38] ሚሲዮናዊው ስተርን (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[39] የባርደል ሸር በተክለፃዲቅ መኩሪያ "ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት" ተዘግቧል::

[40] አፄ ቴዎድሮስ ምኞታቸው (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)



በጣም የቀናቸው ይመስላል፤ በዚህም ምክንያት ይህ ቴላሞኒያን አጃክስ[41]፣ በስውነቱ ግዙፍና ጠንካራ ሰው፣ ዝነኛና ስሙ የገነነ ነበር:: የካሜሩንን መታሰር ሲሰማ፣ የአፄ ቴዎድሮስ ችሎት ድረስ ከተፍ ይላል:: የሰውነቱ ግዙፍነትና ጠንካራነት የቴዎድሮስን አድናቆት አትርፎለታል፤ ቴዎድሮስም ሠሩ ውስጥ እንዲያገለግል ይጋብዛሉ:: ሰፒዲ የቴዎድሮስን ወዳጅነት ቢያገኝም፣ ከዚህ ቀደም ከፕላውደን ጋር የነበረውን አያህልም ነበር::



ሎርድ ጆን ራስል

አፄ ቴዎድሮስ ከዚህ ቀደም የነበራቸውን የሚታወቁበትን የስው መውደድና ደግነት[42] ባህሪያቸውን አጥተዋል:: በውጊያ፣ እንግሊዛዊው ጦረኛ ባሳየው ድፍረት፣ ጀግንነትና ጥንካሬ ቴዎድሮስ የአንድ ሺ ጦር አለቃ አድርገው በመሾም "የባሻነት"[43] ማዕረግ ሰጡት፤ ከዚያ ወዲህ ባሻ ፈለቀ ተብሎ ይጠራ

[41] በግሪክ ታሪክ፣ የሳላሚሱ ንጉስ የቴላሞን ልጅ አጃክስን ለመጥቀስ ነው::

[42] ስለ አፄ ቴዎድሮስ ደግነት (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[43] የወታደራዊ ማዕረግ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)



ሎርድ ጆን ራሰል

ጀመር:: የስፒዲ ምኞትና ፍላጎት ግን እየጨመረ መጣ፤ ይህ በቴዎድሮስ ሚኒስትሮች በኩል የተስተዋለም የታሰበም ነው፤ ስለዚህ ይህንን፣ ነጭ የንጉሡን ወዳጅ ለማባረር ብዙ ተንኮልና ሸር ይሸረብ ጀመረ:: ባሻ ፈለቀ፣ ከህንድ ገዥ(መሀራጃ) የተሠጠው የቱርክ ጎራዴ ነበረው:: በዚህ ጎራዴ በጎችን ከጭንቅላት እስከ ጅራታቸው በአንድ ሰንዞር ከሁለት በመክፈል ቴዎድሮስን ያስደንቅ ነበር፤ ይህ ግን አቢሲኒያውያኑ ማድረግ የሚችሉት ነገር አልነበረም:: በዚህ ሙያና ችሎታው ለረዥም ጊዜ ከቴዎድሮስ ጎን መቆየት ችሏል::

ለአስራ ስምንት ወራት ያህል ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር አብሮ ከከረመ በኋላ፣ ስፒዲ ወደ ጎንደር ይሳካል:: በመንገዱ፣ አስራ ሁለት ከሚሆኑ የፈታውራሪ ገብርዬ ሰዎች ጋር ይገናኛል:: ገብርዬ፣ ቅናትም ይሆናል ስፒዲን ይጠላው ነበር:: የያዘውን መሳሪያ እንዲያስረክብና ቴዎድሮስ ወዳሉበት ወደ ደብረ ታቦር እንዲመለስ ያዙታል:: ስፒዲም በመገረም፣ ገብርዬን፣ ራሱ መጥቶ መሳሪያውን ከእጁ እንዲወስድ ግን ከተጠጋው ደግሞ በያዘው ጎራዴ በጎቹን ከሁለት እንደሚጎምዳቸው ሁሉ ገብርዬን ከሁለት እንደሚከፍለው ያስጠነቅቃል:: ገብርዬም ጠብ እንዲነሳ እንደማይፈልግ ያስታውቃል:: ስፒዲም፣ "እንግዳውስ፣ ወደ ጌታህ ተመለስና የጎንደር ጉዳዬን ስጨርስ እንደምመለስ ንገር" ይላል:: ስፒዲም መንገዱን ቀጠለ:: ገብርዬም ወደ ንጉሡ ካምፕ በመመለሰ ስፒዲ ሰላደረገው ነገርና ስለ እምቢተኛነቱ ጨመርመር በማድረግ ከስፒዲ ጋር ስለተደረገው ግንኙነትና የቃላት ልውውጥ በዝርዝር ለአፄ ቴዎድሮስ ያቀርባል:: እንደ ገብርዬ አቀራረብም፣ ስፒዲ የንጉሡን ትዛዝ አላከበረም::

በዚህ መሀል፣ በጎንደር የነበረውን ሥራ ለራሱም ሆነ ለንጉሡ በሚያረካ መንገድ ካጠናቀቀ በኋላ፣ ስፒዲ፣ ንጉሡ ወዳሉበት ወደ ደብረታቦር ይመለሳል:: ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ቃላት ልውውጦች በሁለቱ መሀከል የሆነ ነው ይባላል::

ስፒዲ፣ "ይኸው ተመልሻለሁ::"

ቴዎድሮስ፣ "እንደተመለስክ እይቻለሁ፤ ግን እንደትመለስ ሰው ስልኩብህ ለምንድን ነው ያልመጣኸው?"

ስፒዲ፣ "ምክንያቱም፣ ታማኝ አገልግሎቴን በቅጣት ይሸልሙኛል ብዬ ስላላመንኩ ነው::"

ቴዎድሮስ፣ "ምን?፣ ገብርዬ እኔ እንደምቀጣህ ነገረህ ወይ?"

ስፒዲ፣ "አዎ! ነግሮኛል"

ቴዎድሮስ፣ "እንግዲያማ እኔ ከማውቀው በላይ ነው የነገረህ"



ስፒዲ፣ "እሱ ውነት ሊሆን ይችላል፤ በጎንደር ያዘዙኝን ሥራ በሚገባና በታማኝነት ጨርሼ መጥቻለሁ:: አሁን የምጠይቀው፣ ከፍያዬ እንዲሰጠኝና ከሥራም እንድሰናበት ነው::"

ቴዎድሮስ፣ "አይሆንም፤ ያማ ሊሆን አይችልም፤ በሠራዊቴ ውስጥ ካለ ምርጥ ወታደር ጋርማ መለያየት አልችልም::"

ስፒዲ፣ "ግርማዊነትዎ! ትልቅ ሰው ሊሆኑ ይችላሉ፤ ልብዎ የሚያስበው ምክንያትም ይኖርዎታል፤ እኔ ንጉሥ ባልሆንም የራሴ ልቡናና ምክንያት ደግሞ አለኝ:: መጀመሪያ ወደዚህ ስመጣ፣ ለአገልግሎቴ ጥሩ ክፍያና ጉርሻም እንደማገኝ ቃል ገብተውልኝ ነበር:: እርስዎን ለማገልገል ተስማማሁ፤ እርስዎንም በታማኝነት አገለገልኩ:: በጦር ሜዳ ውያለሁ፤ ራስዎ በአይንዎ እንዴት እንደተዋጋሁ ተመልከተዋል፤ በዚህም በዚያም ዕደገት ሰጥተውኛል፤ ነገር ግን እርስዎን ማገልገል ከጀመርኩ ጀምሮ ገንዘብ የሚባል ተከፍሎኝ አያውቅም:: የምበላውን ዳቦና ጨው በገንዘቤ ገዝቼ ነው፤ ለአገልጋዮቼም ከራሴ ገንዘብ እየከፈልኩ ነው:: የርስዎን ትዛዝ ለመፈፀም መንገድ በወጣሁ ጊዜ፤ ርስዎ የሀሰት ወሬ፣ እነ ፊታውራሪ ገብርዬ የሚያወሩትን፣ በጆሮዎ በመስማት እኔን መልሰው የሚያመጡ ሰዎች ልከውብኛል፤ በምን ምክንያት እንደሆነ ርስዎ የበለጠ ያውቃሉ:: ገንዘቤ ተከፍሎኝ ከሥራ እንደሰናበት እጠይቃለሁ::"

ቴዎድሮስ፣ "እናስ ወደየት ትሄዳለህ?"

ስፒዲ፣ "ወዳገሬ ነው የምሄደው"

ቴዎድሮስ "ምናልባትም ሀገሩን እንዳትሰቅ ምርጫዬ ቢሆንስ?

ስፒዲ፣ "እንደዛ ከሆነ ሰው ይሞታል፤ ልጅ እንዳልሆንኩ ያውቃሉ፤ ስለዚህ እጄን ዝም ብዬ አልሠጥም::"

ቴዎድሮስ፣ "ከኔ ጋር እንድትቆይ የሚያደርግህ ምንም ማድረግ የምንችለው ነገር የለም?"

ስፒዲ፣ "ምንም! በኔ ዙርያ የሚሸረበውን ተንኮልና ሸር ማየት በቅቶኛል::"

ንጉሡ፣ ስፒዲን ጥሎ ከመሄድ የሚያስቀረው ነገር እስመኖሩን ሲረዱ፣ የሚገባውን ሁሉን ገንዘቡን በመክፈል፣ ፈረስ፣ ጋሻና ጦር በመሸለም በፍቅር ተሰናበቱት[44]::

ባሻ ፈለቀ፣ ካፒቴን ስፒዲ፣ ዘመዱን ከረንስን ይዞ ወደ ምፅዋ ሄደ:: ወጣቱ ከረንስም፣ የቆንስል ካሜሩንን ደብዳቤ ይዞ ወደ ሎንደን ሄደ:: ዕረፍት

---

[44] እነ ቴዎድሮስ ለሌሎች አውሮፓውያን (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

የስኾ ስፒዲም ሌላ ሥራ በመፈለግ ወደ ኒውዚላንደ ሄደ:: በኒውዚላንድም የሚሊሻ ካፒቴን በመሆን በማኦሪ[45] ጦርነት ጊዜ ዕውቅናን ሊያገኝ ችሏል:: ወደፊት ስለሱ እንሰማለን::

ከረንስ፣ ከውጭ ጉዳይ ፅህፈት ቤት ለካሜሩን የሚሠጥ ደብዳቤ በመያዝ ወደ አቢሲኒያ እንዲመለስ ተላከ:: አቢሲኒያ የደረሰውም በህዳር 1863 ነበር:: ደብዳቤው ከአፄ ቴዎድሮስ ስለተላከው መልክት ምንም አይጠቅስም:: እንደዚህ አይነቱ ለረዥም ጊዜ መልስ አለመሠጠቱ፤ በአፄ ቴዎድሮስ በኩል እንደስድብና ከብራቸውን እንደመናቅ ተደርጎ በመቆጠሩ ከፍተኛ ጥላቻ ነው ያሳደረባቸው:: ይህ የሎርድ ራስል የዲፕሎማሲ ሥራ ውጤት ደግሞ ቆንስል ካሜሩን፣ ሚሲዮናውያኑን እና ሠራተኞቻቸውን በእግር ብረት እንዲታሰሩ ነው ያደረገው::

ከረንስም ቢሆን ዕድለኛ አልነበረም:: ስሥጦታ ያመጣው ምንጣፍ ላይ ጁለስ ጌራርድ የተባለ አንግሊዛዊ[46] ሰው የአረብ ልብስ እንደለበሰ አንበሳ ሊገድል ሲል ተስሎበታል:: ይህን በማየት ከስድብ ስለቆጠሩት ቴዎድሮስ በቁጣ ይገነፍላሉ:: በቴዎድሮስ አመለካከት፣ ጁለስ ጌራርድ የሚገለው አንበሳ፣ የይሁዳን አንበሳ ሆኖ በግብፆች(የአረብ ልብስ) እንደሚሸነፍ አድርገው ነው የወሰዱት:: ከረንስም ያለርህራሄ ተገርፎ እንደሌሎቹ በእግር ብረት ታሠረ::

ግብረ ሠናይ ባላቸው በአንዳንድ የእንግሊዝ ሰዎች፣ እስረኞቹን ስማስፈታት ጥረት ተደርጎ ነበር:: ወይዘሮ ስተርን የባሏን መታሰር ስትሰማ፣ ንግሥቲቷ የተፈረመ ደብደቤ ስቴዎድሮስ እንድትልክ ተማፅና ነበር:: ሎርድ ሻፍትስበሪ የተባለ ሰውም በደግነት ሰዎችን ወክሎ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ደብዳቤ አቅርቦ ነበር:: የተሠጠው መልስ ግን "ንግሥቲቷ ስአቢሲኒያ ንጉሥ ደብዳቤ አንድትፅፍ ማድረጉ በኔ በኩል ጥሩ ምክር አይደለም::" ነበር:: እንዲህ አይነቱ የከፋ ፖሊሲ፣ ፖሲሲ ከተባለ፣ ያስከተለው ነገር ቢኖር በምርኮ በእስር ቤት ላሉት ሰዎች ቅጣትና ስቃይ ነው ያበዛባቸው:: ቴዎድሮስ እያደረ ሀዘናቸው እየጨመረ፤ ጨካኝም አየሆኑ መጡ::

በተለይም ንጉሥነታቸውን የሚያዋርድና እንደ ስድብም የሚቆጠር ነገር በሴት[47] በኩል መደረጉ በጣም ነው ያበሳጫቸው:: ስለዚህ በቀላቸውን

[45] ከ1845 -1872 እኤአ በተወላጆቹ በማኦሪዎችና በኒውዚላንድ መንግሥት ተከታታይ ጦርነቶች ተካሄደዋል:: ሰውየው ቅጥረኛ ወታደርም ነበር::

[46] ፈረንሳዊ ሆኖም ይጠቀሳል:: የሚታወቀውም በአዳኝነቱ ነበር:: ሄንሪ ዱፍተን ከአቢሲኒያ ሲመለስ፣ ከረንስን ምፅዋ ላይ አግኝቶት ይህን ገደ ቢስ ምንጣፍ እንዳሳየው ዘግቧል:: ቴዎድሮስ ግን ምንጣፉን የላከው ባሻ ፈለቀ ነው የሚሉት::

[47] ንግሥት ቪክቶርያን በመጥቀስ::



በእስረኞቹ ላይ ይወጡ ጀመር:: እስረኞቹ በእስራት አያሉ ያሳለፉት መከራ የሚነገር ታሪክ ነው የሆነው::

ገንዘብ ካስ በአቢሲኒያ ውስጥ መደረግ የማይቻል ነገር አልነበረም:: ከቴዎድሮስ ጋር ወዳጅነት የነበረው፣ ካሜሩን ከመታሰሩ በፊት አቢሲኒያ ሲመጣና ሲገባ ሲከተሰው የነበረ አቶ ሳሙኤል የሚባል ሰው ጉቦ የሚደልሰው ሰው ሆኖ ተገኝቷል::

በገንዘብ፣ አቶ ሳሙኤል[48] ደብዳቤዎችን ምፅዋ ድረስ ይወስድ ነበር፤ ራሱ ካልሆነም በሱ ታማኞች በኩል ደብዳቤዎች በምስጢር እንዲወጡ ያደርግ ነበር:: ከነዚህ ደብዳቤዎች፣ በአንዱ፣ ካሜሩን የእስራቱን ምክንያትና የደረሰበትን ችግር በሰፊው አትቶ "ለጃንሆይ (ቴዎድሮስ) መልስ ደብዳቤ ካልተላከ በስተቀር የኔ መፈታት ተስፋ የለውም::" ብሎ ፅፏል::

ይህ የካሜሩን ደብዳቤ ታይምስ ወደ ተባለ ጋዜጣ ይደርሳል፤ ጉዳዩም በእንግሊዘ ጋዜጦች በመጥፎ ሁኔታ ነው የታየው:: ታይምስ የተባለው ጋዜጣም መንግሥት ባደረገው የጅል ስራ ቁጣና ጥላቻውን ሲያወርድ፤ ሌሎች ጋዜጦችም ያስተጋባሉ:: በዚህ የቁጣ ማዕበል ምክንያትም ሚኒስትሩ ሀሳቡን ቀይሮ ንግሥቲቱ ደብዳቤውን እንድትፅፍ ይመክራል:: ደብዳቤው ተፅፎ ይላካል::

ሚስተር ላያርድ የሚባል የፓርላማ አባል፣ ከዚህ ቀደም በጤግሮስ ወንዝ ላርጅ ጥንታዊ ቁሳቁሶችን በሚፈልግበት ጊዜ ስሠራተኞቹ ደሞዝ ከፋይ ሆኖ የሚሠራ አንድ ፀሐፊ ነበረው:: ይህ ፀሐፊ ደግሞ አርመናዊው ሆርመዝ ጄ ራሳም ነበር::

"ኒነቨህ" የተባለው ፅሁፍ ደራሲው ሚስተር ላያርድ ፣ እንግሊዝ አገር በሚመሰሰበት ጊዜ፣ የሠራተኞቹ ደሞዝ ከፋይ የነበረውን ፀሐፊውን አልረሳም:: ራሳም፣ በጊዜው በኤደን የፖለቲካ ወኪል ስነበረው ስኮሎኔል መርዌዘር ተቀጥሮ ይሠራ ነበር፤ ይህም የእንግሊዝ ሚኒስቴር በቴዎድሮስ ላይ የነበረው ፖሊሲ በእንግሊዝ ጋዜጦች ከተወገዘ በኋላ ነበር:: ራሳም በመተማመን፣ ለላያርድ ደብዳቤ በመፃፍ የንግሥቷን መልስ ስቴዎድሮስ ለመውሰድ ዝግጁ መሆኑን ይገልፃል::

አመሲጋኙ ጥንታዊ ቁሶች ሰብሳቢው፣ ራሳም መልክተኛ ሆኖ እንዲሾም ሥሪት ያደርጋል:: ስስተሳካስትም፣ መልስ ለመስጠት ይህን ያህል ረዥም ጊዜ የወሰደውን ደብዳቤ ለማድረስ የተላከው ራሳም ነበር:: ከራሳም ጋር ሁለት የእንግሊዝ መኮንኖች፣ ሉተናንት ፕሪዶና ሰርጀን ሄንሪ ብላንክ የሚባሉ ነበሩ::

[48] አቶ ሳሙኤል የአፄ ቴዎድሮስ አስተርጓሚ ነበረ:: (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

የራሳም ሹመት፣ ለአንድ ፀሐፊና ደሞዝ ከፋይ ለነበረ ሰው ከሚገባው በላይ፣ "ልዩ ከፍተኛ መልከተኛ" የሚል ነበር፡፡

ራሳም ካይሮ ሲደርስ፤ የካቲት 1865 መሆኑ ነው፤ አንድ በጣም ወሳኝ የሆነ ነገር ከመልክተኞቹ ጋር አብሮ አለመላኩ ይታወቃል፡፡ ይህም የንግሥቷ የቀለበት ማህተም ነበር፡፡ መልከተኛው እንዲመለስ ይደረጋል፡፡ ዶሴው ከተሟላ በኋላ እንደ አዲስ ወደ አቢሲኒያ ጉዞ ይጀመራል፡፡ ለደብዳቤው መዘግየት ለእንግሊዝ መንግሥት በሚስማማ ሁኔታ ዝርዝር ምክንያት እንዲያቀርብም ታዟል፡፡

ከተወሰነ ጊዜ በኋላም መልከተኛው ራሳም ምፅዋ ይደርሳል፡፡ ሆኖም ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ አንድ ሙሉ አመት በምፅዋ ይቆያል፡፡ [49]

በነዚህ ረዥም ጊዜያቶች መሀከልም እስረኞቹ ይሰቃያሉ፡፡ ለነሱ ሁኔታዎች እየከፉ ነው የሄዱት፡፡ ዳቦና ውሃ ብቻ እየተሠጣቸው፤ በሠንሰለት ከማድግዳ ጋር እንደታሰሩ ይደበደቡ ነበር፡፡ ካሜሩን ተሠቃየ፤ እንደሱ አባባል "ህያ የሚሆኑ አቢሲኒያውያን እጅና እግሮቼን በገመድ ወጥረው ራሴን እስከሰት ድርስ ይጎትቱኝ ነበር፡፡ የትከሻ መጋፊያ አጥንቶቼ እስኪጋጠሙ ድረስ ወደኋላ እወጠር ነበር፡፡ ጭንቅላቴ ጭኖቼ ውስጥ እስከሚቀበር ድረስ ኩርምት እንድል ተደርጌ ጀርባዬ ከጉማሬ ቆዳ በተሠራ አለንጋ ይገረፍ ነበር፤ ጀርባዬም ሰምበር ያወጣና ደምም ይደማ ነበር፤ እንደዚህ ሲሆን ደግሞ አሸዋ ላይ እንድንከባለል ይደረጋል፡፡"

ይህ ሆኖ፣ ራሳም ግን ምፅዋ ይከርማል፡፡ በፓርላማው ወስጥ በተደረገው ክርክር ምክንያት ሚስጥር ወደ ውጭ ሲወጣ፣ ለሎርድ ላያርድ ደቀመዝሙር የሚስማማ ሁኔታ አልነበርም፡፡ ሎርድ ራስልም አማራጭ ስላልነበረው፤ የታወቀውን መንገደኛ ሚስተር ፓልግሬቭን ወደ አቢሲኒያ ዘልቆ እስረኞቹን እንዲያስፈታ ጥረት እንዲያደርግ ሾመው፤ ራሳም ደግሞ እንዲመለስ ተጠየቀ፡፡ ተመላሹ ራሳም አዲሱን መልከተኛ ምፅዋ ላይ አገኘው፡፡ ራሳም ወዲያውኑ ወደ ሱዌዝ በማምራት፣ እለከሳንድርያ (እስክንድርያ) ላለው ፅሕፈት ቤት ካሜሩን ተለቋል የሚል የቴሌግራም መልከት ላከ[50]፡፡

ይህ የምስራች መልከት በኢንግላንድ በፍጥነት በዜና ሲሰራጭ በሁሉም በኩል በሙሉ ልብና በደሰታ ስሜት ነበር የተደመጠው፡፡ ፓልግሬቭ ካይሮ ቢደርስም በዚህ ምክንያት የሱ ተልኮ አለቀለት፡፡ የያዘውን ሥጦታም ለራሳም አስረከበ፡፡

---

[49] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[50] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)



*ባሻ ፈለቀ ከናፒየር ጋር(በቀኝ በኩል በጥግ የሚታየው ግዙፍ ሰው)*



*የአውሮፓ እስረኞች*

(ከግራ ወደቀኝ፣ ከረንስ፣ ራሳም፣ ስተርን፣ ሌተናንት ፕሩዶ፣ ወይዘሮ ሮዘንታልና ልጇ፣ ሮዘንታል፣ ዶክተር ብላንክ፣ ፒየትሮ፣ ካሜሮን ናቸው)



*ሆርሙዝ ራሳም*

ራሳም ስጦታውን እንደያዘ ወዲያውኑ ወደ ምፅዋ ተመለሰ፤ ምናልባትም፣ ሥጦታውን የተፈታውን ካሜሩንን አጅበው እስከ ምፅዋ ድረስ ለሚመጡ ሹሞች ለመሥጠት ነበር፡፡

መልክተኛው ራሳም፣ ከአጃቢዎቹ ከብላንከና ፕሩዶ ጋር ከምፅዋ ተነስቶ፣ መንገድ ላይ ሳያቆም በጥር 28፣ 1866 ደብረ ታቦር ገባ፡፡[51] "ገናናው ንጉሥ ሆይ! ለዘላለም ያኑርዎ!" የሚል ሰላምታ ነበረ ከአቢሲኒያውን ንጉሥ ከአፄ ቴዎድሮስ ፊት የቀረበው የእንግሊዝ መልክተኛ ያቀረበው፡፡ ከንግስቷ የተላከው ደብዳቤ ግን የተጠበቀውን ያህል አልነበረም፤ የሚገባውን ክብርም ለቴዎድሮስ ባለመስጠቱ ካሜሩንም አልተለቀቀም፣ እንዲያውም ራሳም፣ ፕሪዶ እና ብላንክ ቴዎድሮስ ካሰሯቸው እስረኞች ጋር ተደረቡ፡፡ ራሳም በነበረው ብልጣ ብልጥነት[52] ዲፕሎማሲ ምክንያት አልተደበደበም፤ ከንግስቷ በኩል የጎደለውን እከብሮት፣ እራሱ በመልካም ፈቃዱ ጨማምሮ አቀረበ፡፡ የቴዎድሮስ ጭካኔም ቢሆን እንዲህ ያለውን አክብሮት በመልካም ሁኔታ

[51] ሶስቱ መልክተኞች፣ ሀኪሙ ብላንክ፣ ወታደሩ ፕሩዶ እና ዲፕሎማቱ ራሳም ይበቃሉ ተብሎ የተወሰነው ከብሪታንያ ነው፡፡ ፕሩዶን የመረጠው መርዊዘር ነበር፡፡

[52] ቴዎድሮስ ራሳምን በጣም ይወዱት ነበር፤ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)



ስለተቀበለው ለእስረኛ የሚገባውን ደግነትና እንክብካቤ ለመልክተኛው ራሳም እንዲደረግለት ሆኗል፡፡ በራሳም ተፅኖ የካሜሩን ሁኔታም ተሻሽሎ ነበር፡፡[53]

መልክተኞቹ ከታሰሩ ከሶስት ወር በኋላ፣ ሚስተር ፍላድ እለክሳንድርያ ይደርስና የመልክተኞችን ዕጣ ዜና ያሰማል፡፡ ሆኖም እሱ ራሱ ወደ አቢሲኒያ ሲመለስ ከእስረኞቹ ጋር ይደመራል፡፡

ቴዎድሮስ፣ የነበራቸው ሥልጣን በእርግጥ ከእጃቸው እየወጣ እንደሆነ ተሰምቷቸዋል፡፡ ከዚህ ቀደም የነበራቸው ጥንካሬና ችሎታ፣ የነበራቸው ጀግንነት፣ ማዕረግና ክብሩ፣ ወይም ጭካኔያቸው የነበሩትን ግዛቶች በሥራቸው ማቆየት አላስቻላቸውም፡፡ ኦሮሞዎቹ ሀይላቸውን አሰባስበው ከኋላቸው ይወጉቸው ጀመር፡፡ ለተወሰነ ጊዜ፣ ቴዎድሮስ በጀግንነት ተቋቋሙት፤ ሆኖም የመለሱት እየፈረሰ ሲሄድ መንዳታቸውን ያዩ ጠላቶቻቸው የልብ ልብ ይሰማቸው ጀመር፡፡ የቴዎድሮስ ሞራልም እየተዳከመ መጣ፡፡ ነገር ግን የትም ቦታ ቢሆን፣ የቴዎድሮስ ካምፕ፣ በነበሯቸው መድፎች ምክንያት የማይጣስ ሀይል ነው የሆነው፡፡ የአውሮፓውያን ሠራተኞቻቸው ሀያ የሚሆኑ መድፎች አምርተውላቸዋል፤ ከነዚህ አንዳንዶቹ በጣም ግዙፍ ነበሩ፡፡

መድፎቹን እየወደዷቸው ነው የሄዱት፡፡ አስራ ሁለትና አስራ አምስት ኢንች አፉሮቹ ነብሳቸውን ነው የሚያስደስቷቸው[54]፡፡ የመድፎቹ ጩኸት ብቻ ጠላቶቻቸውን እንዲሚያሸብራቸው ነው ያሰቡት፡፡ የነዚህ መድፎች ዝና በድፍን ሀገሩ በተወራ ጊዜ፣ ደፍሮ የቴዎድሮስን ካምፕ የሚያጠቃ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ሁሉም በያሉበት ይሸፍታሉ፣ ቴዎድሮስም ፍፁም የማያወላውል ቆራጥ የሥነ ሥርአት አርምጃ[55] ስለሚወስዱ፣ በሚደረገው ጭካኔ የተመላበት ቅጣት ምክንያት በመቶ በመቶ የሚቆጠሩ ወታደሮቻቸው እየከዷቸው ይሸሹ ጀመር፡፡

እሁን፣ ጦርነት እንዲታወጅ ወደ ሆኑት ምክንያቶች እየመጣን ነው፡፡ ሰበቡ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ የእንግሊዝ እስረኞች በቁጥጥር ስር እንዳሉ

[53] የአፄ ቴዎድሮስ ኒሻን፣ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[54] መድፍና የጦር መሳሪያዎችን በጣም በመውደዳቸው (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

[55] ቴዎድሮስ ሥነስርአት የሚወዱ ሰው ነበሩ፡፡ ሥርአቱን መተላለፍ ከባድ ነው፡፡ ወደ ሸዋ ሲዘምቱ ወታደሮቻቸው ገበሬውን ዘርፈው እንዳይበሉ ጥብቅ ትዛዝ ሠጥተው ነበር፤ ነገር ግን ትዛዙን የተላለፉ ስላሳ ሰባት ወታደሮች በሞት እንዲቀጡ አድርገዋል፡፡

ናቸው:: እነሱን ለማስፈታት የተደረገው ተልኮ ውጤት አልባ ሆነ:: የዚህ ሁሉ መጨረሻ ምን ይሆን? እስኪ እንመልከት::

በ1866፣ በእንግሊዝ አገር፣ የወግ እጥባቂው ፓርቲ ሥልጣኑን ያዘ፤ የደርቢው መስፍን ጠቅላይ ሚኒስትር ሲሆን፤ ልጅየው ሎርድ ስታንሊ ደግሞ በውጭ ጉዳይ ፅህፈት ቤት ሀላፊ በመሆን ወንበሩን ያዘ:: ከረረ ወዳለ ደረጃ ከመሻገራቸው በፊት፤ ሚኒስትሮቹ፣ የታሰሩትን ለማስለቀቅ ለቴዎድሮስ እጅ መንሻ ለመስጠት ሀሳብ አቀረቡ:: ያም አልተሳካም::

ቴዎድሮስ፣ እንግሊዞቹ ዜጎቻቸውን ለማስለቀቅ ሲጨነቁና ሲጠበቡ ሲያዩ፤ እንግሊዞች (ህዝቡ) ዜጎቻቸው በእስር ከሚከርሙባቸው የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ ብለው ገመቱ:: በአንድ በኩል የቴዎድሮስ ጥርጣሬ ትክክል ነበር፤ እዎ የእንግሊዝ ህዝብ ለዜጎቻቸው ሲሉ ያማያደርጉት ነገር አልነበርም፤ ጦርነትም ቢሆን:: ነገር ግን ቴዎድሮስ ራሳቸው ባዋረዱት ዙፋን ላይ እንዲቆዩ በጭራሽ መርዳት አልፈለጉም:: ስለዚህ የእንግሊዝ መንግሥት ጦርነት አወጀ::

የሚገርመው ነገር ግን፣ ጦርነቱ ሲታወጅ፣ የእንግሊዝ ህዝብ ምንም አይነት የድጋፍ ወይም የተቀባይነት ስሜት አላሳየም ነበር:: የጦርነቱ ዕቅድ በርጋታና በፅሞና ነበር ውይይት የተደረገበት:: በህዝቡ ዘንድ የተቀባይነት ስሜት ባለመፍጠሩ ምክንያት፣ አደጋ፣ መጥፎ ንግርትና ምልክቶችን የሚጠቅሱ ደብዳቤዎች እየተላኩ በጋዜጣ አዘጋጆች ይወጡ ጀመር:: ሁሉም የራሱን ትንቢት መናገር ጀመረ::

አንድ ራሱን "እውነተኛው ጆን ቡል" ብሎ የሚጠራ ዘጋቢ፣ በራሱ አመለካከት እንደፃፈው ከሆነ፣ አንድም ሠራዊት ከዚያ አገር ተመልሶ እንደማይመጣ ገለፀ[56]:: የእንግሊዝ ታከስ ከፋይ ህዝብም ቢሆን ራዕይ ነው የታየው፤ በጊዜው በሀርትፎርድሽር የነበረ ሩቅ አላሚ፣ እያንዳንዱን ወታደር ዝናብ ጠርጎ ወደ ባህር ይወስደዋል ብሎ ተነበየ:: ጆሊ ብሪቶን፣ የእንግሊዝ ወታደሮች በምንም አይነት ቴዎድሮስን መማረክ አይችሉም አለ:: ራሱን የካምብሪጅ ተማሪ ነኝ የሚል፣ በአእምሮው ውስጥ የግሪክና የትሮይን ጦርነት ስሎ፣ የአቢሲኒያን ሸለቆዎች የሚያሻግር ድልድይ እንዴት እንደሚሠራ ጠየቀ፤ አቢሲኒያ ግሪክ ካልሆነች፣ አራት ሺ ጫማ ጥልቀት ባለው ሸለቆ ላይ ያለ ድልድይ እንዴት መሻገር እንደሚቻል በአእምሮው ሊመጣለት አልቻለም:: ይህ አዋቂ ሰው ደግሞ፣ የእንግሊዝ ጄኔራሎች ከትሮይ እንደሚበልጡ

56 (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)



እ፡ግጠኛ ነው፤ እንደዚያም ሆኖ፣ የትሮይን ታክቲክ በመጠቀም የአቢሲኒያን ሰፋፊ ሸለቆዎች መሻገር መቻሉ ተስፋ የሌለው ነገር ነው ይላል::

በአጠቃላይ፣ በዘማቾቹ ላይ ይደርሳል ተብሎ ያልተተነበየ አደጋ፣ እስከፊ ነዝ፡ና በሽታ አልነበረም:: መርዛማ እና አደገኛ የእባብ ዝርያዎች[57] የወታደሮቹ ልብሰና ብርድ ልብስ ላይ እንደሚተራመሱ ተገለፀ:: ሀኪሞችም ቢሆኑ ወታደሮችን፣ ጭንቅላቱ የሮዝ ቀለም ካለው ትንሽ  ዝንብ እንዲጠነቀቁ፣ በመንገድ ዳር የሚያገኙትን ማር እንዳይነኩ፣ የኖረ የጉድጓድ ውሀ እንዳይጠጡ፣ ከአይን በሽታ እንዲጠነቀቁ፣ ድንገት ተቅማጥ[58] ከያዛቸው ቶሎ መፍታት የሚችሉት ቀበቶ እንዲታጠቁ፣ በቶሎም መድሃኒት እንዲጀምሩ፣ አገራቱን ከሞላው የጅብ መንጋና ከጉማሬ ለመከላከል የሚቻላቸውን እንዲያደርጉ በማለት አስጠነቀቁ:: የእንግሊዝ ወታደሮችን ከላይ እስከታች ድረስ የተቅማጥ በሽታ እንደሚያውካቸውም ተነገረ::

ከዚህ ቀደም ወደ ሌሎች አገሮች ተጉዘው የሚያውቁ ሰዎች፣ ብዛት ያላቸው የማይመስሉ ምክሮችን ሰገሉ፤ ከሎንደን ቲያትር ቤቶች ውጭ ወጣ ብለው ተጉዘው የማያውቁ ሰዎችም ቢሆን፣ ከልምዳቸው በመነሳት፣ ለውጭ ጉዳይ ፅሕፈት ቤቱ ምክር በነፃ ይሰግሱ ጀመር:: ታማኝ የሆኑ የእንግሊዝ ዜጎች ደግሞ ያለምንም ርዳታ በራሳቸው እስረኞቹን ማስፈታት እንደሚችሉና ለመሰለፍም ዝግጁ መሆናቸውን አስታወቁ[59]:: በራሳቸውም ስለሚተማመኑ፣ ግዳጁን ያለምንም አደጋ ሳይቸገሩ መወጣት እንደሚችሉ ነው፤ ይህንንም የሚያደርጉት ራሳቸውን ለማዝናናት ሲሉ ነው::

ሌሎች ደግሞ፣ የውጭ ጉዳይ ፅሕፈት ቤቱ ሊከሽፍ የማይችል ሰቅዳቸውን እንደሚቀበል ተስፋ አደረጉ፤ ዕቅዱም፣ የፈረሰኞች ካምፓኒ ጦር ይዞ ከአቢሲኒያው ንጉሥ ካምፕ ውስጥ ጥሶ በመግባት በሀይል መማረክ ነው:: ታይምስ የተባለ ጋዜጣ ልዩ ዘጋቢም ቢሆን ከተፈጠረው ውዥምብር ነፃ አልወጣም:: እንደሌሎቹ ሁሉ ሀሳብ ሲሰጥ፤ ኮሎኔል መርዌዘር የፈረሰኞች ስኳደርን ይዞ ቢሄድ፣ ሁሉም ነገር አንድ ወር ባላነሰ ጊዜ ይጠናቀቃል በማለት የራሱን እምነት በርግጠኛነት አቀረበ::

ካፒቴን ስመልፈንገስ፣ ለታይምስና ለሎርድ ስታንሊ በላከው ፅሁፍ፣ ያለ ሀውሳዎች እርዳታ የእንግሊዝ ወታደሮች በአቢሲኒያ መንቀሳቀስም አይችሉም፤

57 ከሀሉት አይኖቹ በላይ ቀንድ ያለው ሰራሰተስ የሚባል አባብ ፣ ጀርባው ላይ ጥቁር ባመዝማዛ ቀለም ያለው አደገኛ መርዛማ እባብ

58 (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

59 የታሠሩ ቤተሰቦችን በመወከል የመጣው ዶክተር ቤክ (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)

ሀውሳዎች መደበኛውን ጦር ለመርዳት አገሩን በማለስ፣ ከጦሩ ፊት ፊት እንደ ቃፊር እየሆኑ በመላከ ማገልገል እንደሚችሉ ገለጠ። በጦሩ ውስጥም በኮሎኔሌነት ማዕረግ ተመድቦ መርዳት እንደሚችል አስታወቀ። ሀውሳዎች በናይጀሪያ፣ በሌጎስ ብቻ ስለሚኖሩ እንዴት አድርገው በአቢሲኒያው ውስጥ እንደሚመለመሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ሊታየው አልቻለም። ለምን ግን የማይሆነውና የማይመስለውን ነገር መከተል ያስፈልጋል። ሁሉም ነገር የአቢሲኒያ ብሉ ቡክ[60] በሚባል ማህደር አልተመዘገበም ወይ? ጦር ከየት ነው የሚመጣው? የተወሰነው፣ ጦሩ እንዳለ የህንድ ጦር እንዲሆን፣ በቦምቤይና በኢንግላንድ የሚገኘው የአውሮፓና የሰፖይ ጦር ስንቅና የመጫኛ አጋሠሶችን ብቻ እንዲሠጥ ተወሰነ። ስለዚህ፣ የቦምቤዩ አገረ ገዥ፣ ሰር ሲሞር ፊትዝጀራልድና የቦምቤይ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ ሰር ሮበርት ናፒየር በውጭ ጉዳይ ፅሕፈት ቤቱ ከተነገራቸው በኋላ ዝግጅት ማድረግ ጀመሩ። ጦሩ አስራ ሁለት ሺ ወታደሮች እንዲኖረው፣ ሁለት ሺ ሰዎች ለባህር ዳርቻ ዙላ ወደብና በአቢሲኒያው ደጋማ መሬት በሰናፌ የሚመደቡ፣ ሁለት ሺ በዙላና በመቅደላ ግማሽ መንገድ አንጣሎ ላይ የሚመደቡ፣ ሁለት ሺ ደግሞ በጦሩ መሀከል ያለውን ግንኙነት እንዳይቋረጥ የሚያደርጉ፣ የተረፉት ስድስት ሺ ወታደሮች ግን ቀጥታ ዘማቾች እንዲሆኑ ነበር።

መኮንኖች፣ ከብትና አጋሰስ ለመግዛት ወደ ስፔይን፣ ግብፅና ሶሪያ ተላኩ። መድፎችን፣ ኮርቻ፣ ሰንሰለትና ልጓሞችን፣ ድንኳኖችና ሥንቅ ማቅረብ የእንግሊዞች ወሳኝ የጦር ዝግጅታቸው ነው። ለሆስፒታል አገልገሎት የሚሆኑ መርከቦች ወደ እነስሊ ወሽመጥ ተላኩ፤ እነሱም የታመሙትን ለመቀበልና ዙላን የሚጠብቁ ሰዎችን ለመንከባከብ ነበር።

በታላቅ ጥንቃቄና ግልፅ ባለ ሁኔታ የዘመቻው ዕቅድ በሰር ሮበርት ናፒየር ቀረበ። አንዴ ቴዎድሮስ ያለበት ቦታ ከታወቀ፣ ዘመቻው በምንም አይነት መንገድ መከሸፍ አይጠበቅበትም። የተዋጊውን ክፍል ራሱ ናፒየር ነው የመረጠው። ሌሎቹ፣ የማዳራስና የቤንጋል አዛዦች መጠነኛ የሆነ የራሳቸውን ድርሻ ለመስጠት ቢጓጉም፣ ጀኔራል ናፒየር በጦሩ ውስጥ ስምምነትና መዋሀድ እንዲኖር ከአንድ ክፍል ብቻ ቢመጣ ይሻላል ብሎ ነው ያሰበው።

ጦሩ ከባህር የሚወርድበት ቦታ በሌፍተናንት ኮሎኔል መርዌዘር እንዲመረጥ ነው የተወሰነው። ኮሎኔሉ፣ በኤድን ተቀማጭ የነበረ የፖለቲካ ሀላፊ፣ ጀግና ደፋርና ብልህ መኮንን ነው። የአቢሲኒያን የባህር ደንበር ከላይ አስከታች አጥንቷል። እነስሊ ወሽመጥ ምንም እንኳን ከመቅደላ ቢርቅም፣

[60] (በምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች)



ለወደብነት በመመቸቱ፣ ለተራሮች የቀረበ በመሆኑና ባለው በቂ የውሀ መጠን ምክንያት ተመረጠ።

በታጁራ ሠርጥና በመቅደላ መሀከል የመቶ ሃምሳ ማይሎች ርቀት አለ። ከአምፌላ ሠርጥ ከሆነ፣ ሁለት መቶ ሃምሳ ማይሎች፣ ከሆዋኪል ሰስት መቶ ሀያ አምስት፣ ከእነስሊ ወሽመጥ ደግሞ ለትንሽ ከአራት መቶ ማይሎች በታች የሚሆን ርቀት ነበር።

የሚቀጥለው ርምጃ፣ ሁለቱንም፣ እንግሊዝኛና የአቢሲኒያ ቋንቋ መናገር የሚችሉ አስተርጓሚዎች መፈለግ ነበር። ቄስ ሉዊስ ሲ ክራፕ የተባለ ከዚህ ቀደም በአቢሲኒያ መንገደኛ የነበረ ሰው ተመረጠ። ሆኖም በእድሜ ገፋ ያለ በመሆኑ ለዘመቻው የሚሆን አልነበረም። ሚስተር ሄንሪ ዱፍተን፣ ሌላው መንገደኛ፣ ስለ ቋንቋው የማውቀው ነገር አለ ስላለ በመረጃ ስብሳቢው ክፍል ተመደበ ኮሚሳሪያቱንና የስንቅና ትጥቅ ሀላፊውን፣ በሚናገራቸው ጥቂት ቃላት እንዲረዳ ተደረገ። የተሠጠው ሥራ መደበኛ የሆነ አልነበረም። በመጨረሻ ግን፣ ሎርድ ስታንሊ ለዚህ ሥራ ትክክለኛ ነው ከሚባለው ሰው ጋር ተዋወቀ። ይህም ሰው በኒውዚላንድ ሚሊሻ እያገለገለ ያለ ከዚህ ቀደም የቴዎድሮስ ሠራዊት አባል የነበረው ካፒቴን ስፒዲ ወይም ባሻ ፈለቀ ነበር። በኋላም፣ ከቦምቤይ በተላከለት ቴሌግራም ለሰር ሮበርት ናፒየር ሪፖርት እንዲያደርግ ተነገረው። ባሻ ፈለቀ ለእንግሊዝ ሠራዊት ያደረገው ታላቅ አስተዋፅኦ በግልፅና በዝርዝር በሚቀጥሉት ክፍሎች ይገኛል።

በ1867 በህዳር ወር ቀዳሚው የአቢሲኒያ ዘማች ጦር ዙላ ወደብ ያርፋል።

አንባቢዎች፣ አሁን፣ ለዚህ ዘመናዊ ክሩሴድ ጦርነት መከሰት ምክንያት የሆኑትን ሁኔታዎች በየተራ ከተመለከትን በኋላ፣ የተሳሳተ ዲፕሎማሲ ያስከተለውን ውጤት ከመረመርን በኋላ፣ በመጠኑም ቢሆን የዘመቻውን ዋና ዝግጅት ካካፈልኩ በኋላ፣ ቀዳሚው ጦር እነስሊ ባህር ዳርቻ መድረሱን ካስታወቅሁ በኋላ፣ ወደዚህ ዝነኛ አገር አብረን እንድንጓዝ እየጠየቅሁ፣ የወታደሮቹንና የጀግናው ሽማግሌ መሪያቸውን አስገራሚ ጉዞ በመከተል እንዴት መቅደላ አፋፍ ላይ ስንደቅ አላማቸውን እንደተከሉ እንመልከት።



ፀሀፊው ሄንሪ ሞርተን ስታንሊ

## የምዕራፍ አንድ ማስታወሻዎች

**ቁጥር 6፤** ህዝቡ ይህን አይነት ትንቢት የተቀበለበት ምክንያት በዘመኑ የነበረውን ከፉ ሥራ በማየቱ ነው፡፡ ደብተራ ዘነብ፣ የቴዎድሮስ ታሪክ ብለው በዘገቡት ፅሁፍ የሚከተለው ይገኝበታል፡፡ "የዚህ ዘመን ካህናት ስለ ምድራዊ ንብረታቸው ነው፡፡ የነሱስ ሥራቸው፣ ምንዝር፣ አለማት፣ ስካር፣ የዚህን ዓለም ከብር፣ ጌጥና ኩራት፣ የማኅሌት ዘፈን፣ ለሰው ለመታየት፤ ብርሃን ለማግኘት ነው፡፡ ቀን ቀን የሰውን ስራ ይሰራሉ፤ የየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይተረጉማሉ፤ የሚሰማቸውም የለም፡፡ ሌሊት፣ ዘላሞታ ያደራሉና፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል እንዳለው፡፡ ለሰው ጥኑ፤ ሸክም አሰራችሁ በሜንቃው ላይ ትጭኑበታላችሁ፡፡ እናንተ ባንድ ጸንታችሁ አንኳ አትነኩትም አንዳለ፡፡ ደግሞም አትሰረቁ ትላለህ፤ አንተ ትሠርቃለህ አንዳለ፡፡ ይህንን ሁሉ ከፉት ባየ ጊዜ እግዚአብሔር በሀበሻ ላይ ንጉሥ ቴዎድሮስን አስነሳ፡፡ ምንዝር የማይወድ፣ ገንዘብ፣ ሐሰት፣ ሥርቆት የማይወድ፡፡ ሸፍጥንም ሁሉ የማይወድ፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈራ፡፡ ለጅግ የሚሰጥ፤ እንግዳ የወደደ፣ ለታመመ የሚያዝን፤ ለአንድ ሴት የቆረበ" ደብተራ ዘነበ የጠቀሷቸውን ባህሪያትን ቴዎድሮስ ያሳዩና ያስመሰከሩበት ጊዜ ነበር፡፡

ቴዎድሮስ ራሳቸውን፣ "የክርስቶስ ባሪያ" ብለው ነበር የሚጠሩት፡፡ ሀይላቸው ከፈጣሪ እንደሆነ አድርገው መቀበላቸውን በተለያዩ ጊዜያቶች ከተናገሯቸው ንግግሮች መረዳት ይቻላል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን የገለፁበት ሁኔታ በዚህ መልክ ነበር፡፡ ካሳ፣ ወታደራቸው ሲፎክር፣ በሰሜት የያዙትን ብርሌ ይወረውራሉ፤ የወረወሩበት ዝቢታ በብዙ ቦታዎች ሲሰባበር፣ ብርሌው ሳይሰበር ይቀራል፡፡ በዚህ ጊዜ ፎክረው በመነሳት፣ "እኔ የክርስቶስ ባርያ፣ ክርስቶስን ከያዝኩ ከፊቴ ማን ይቆማል" ብለው፣ በብርሌዋ ጠጅ ከቀረበላቸው በኋላ እግዚአብሔርን አመስገኑ፤ ማዳን ይቻልሃል ጌታዬ የሚለበረውን አዳንክ ብለው ወደ መሬት ወድቀው ሰገዱ፡፡ ይላሉ ደብተራ ዘነብ፡፡

በሌላ አጋጣሚ፣ በወሎ፣ አምባ ማርያም የሚባል ቦታ ሠፍረው አያሉ፣ ወታደሮቻቸው ካልዘረፍን ብለው አስቸገሯቸው፤ ንጉሡ ተበሳጭተው የሚቀጥለውን ተናገሩ፡፡ "የመቅደላ ሰዎች አስቲ ምከሩኝ፤ ይህንን መንግሥት ትቼ ለመሄድ ሞከርኩ፡፡ ደግሞም ፈጣሪዬን ፈራሁት፤ ግዛ፣ ንዳ ብዬ ብሠጥህ እምቢ አልክ ብሎ ይጣላኛል ብዬ፡፡" ቴዎድሮስ ቅጣቱን ቢሆን በፈጣሪ ፈቃድ እንደሆነ አድረገው ነበር የተቀበሉት፡፡ ከመልከተኛው ራሳም ጋር ሲጨዋወቱ፣ "በጊዜዬ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ገድያለሁ፤ ነገር ግን ለሞታቸው ፀፀት ተሰምቶኝ አያውቅም ምክንያቱም የፈጣሪን ፈቃድ አየፈፀምኩ ስለሆነ የሚገባቸውን ነው ያደረግሁት...፡፡" ብለዋል፡፡

ካሳቸው ውጭ፣ ሌሎችም ቢሆን በዚህ ነገር አምነት ነበራቸው፡፡ ቴዎድሮስ ወደ ወሎ ሲዘምቱ፣ ወረሂመኑ የሚባል ቦታ የሚኖር፣ ሼህ ያሲን የሚባል ቃልቻ ነበር፣ ይህን ንጉሥ አላስመጣውም (ወሎ አንዳይገባ) ብሎ ወዳጃ ያዘ፡፡ በሶስተኛው

*ቀን ግን፣ ሼህ ያሲን፣ በህልሜ፣ መልአክ ከምድር እስከ ሰማይ የሚሆን ጦር ይዞ፣ ለሁሉም መቅጫ ያወረደውን ግደልልኝ አለኝ፣ አሁን ከመሬት ጋር በሰፋሁህ ብሎ አስፈራራኝ፤ ብሎ ተናገረ። ወደ መቅደላም ሄዶ፣ ንግሥት ወርቂትን አንቺም ሸሺ፣ እኔ አልሆንልኝም፤ ይህ ሰው ከአላህ የተላከ ነውና ዛሬ ሌሊት ሞቼ ነበር በማለት እርሱ ራሱ ግን ለቴዎድሮስ የሚመኟን መሆኑን በመግለጥ ማለ። ቃሏቸውም ሸሸ፤ ወርቂት በዛን ጊዜ ከጨጨሆ እስከ ሸዋ ደንበር ትገዛ ነበር፤ እሷም ሸሸች።*

*ንጉሡ ከእግዚአብሔር የተላኩ ናቸው በማለት ሊዋጓቸው የተሰለፉ ኦሮሞዎች እንኳን ቴዎድሮስን ካዩ ይሸሹ ነበር። ቴዎድሮስ የገበሬ ልብስ ለብሰው፣ ተሰውረውም ቢገቡ ስለሚያውቋቸው ይሸሹ ነበር። ቴዎድሮስ በሌሉበት ጦር ከተላከ ግን ጦሩን ገትረው ይዋጉ ነበር። ይህን ሁኔታም ምርጫ ወርቄ ነገረኝ ብሎ ከለመንት መርካም ዘግቦታል። ሁኔታውም፣ መቶ የሚሆኑ የኦሮሞ ፈረሰኞች ታይተዋል ተብሎ ለንጉሡ ሲነገር፣ ማንንም ሳያስከትሉ፣ ብቻቸውን እየጋለቡ ወደ ሰዎቹ ሲገሰግሱ አይተው ሰዎቹ ሳይዋጉ ሸሹ። ያን ጊዜ ምርጫ ወርቄ ከንጉሡ ጋር አብሮ እየተጓዘ ነበር።*

***ቁጥር 7፤*** *አፄ ቴዎድሮስ፣ ባባታቸው በሀይሉ ወልደ ጊዮርጊስ በኩል ከአፄ ፋሲል ሀረግ የነጋሲ ዘር አላቸው። በዝርዝር ሲታይ፣ የትውልድ ሀረጉ እንደዚህ ነው። አፄ ፋሲል→ ልዕልት ሰብለ ወንጌል→ እንስት→ እንቁዋል→ ከንፈ ሩፋኤል→ ወይዘሮ ወለተ ገብሬ→ ደጃዝማች አልፍዮስ ሀላዌ ነው። ደጃዝማች አልፍዮስ፣ የቋራና የደምቢያ ገዥ የነበሩትን ደጃዝማች ወልደጊዮርጊስን ይወልዳሉ። ደጃዝማች ወልደጊዮርጊስ የቋራውን ገዥ ደጃዝማች ሀይሉ ወልደ ጊዮርጊስን ይወልዳሉ። ደጃዝማች ሀይሉ ከመጀመሪያ ሚስታቸው ከወይዘሮ ወለተ ተክሌ ስመ ጥሩውን ገዥ ደጃማች ክንፉን ሀይሉን፣ ደጃዝማች ገብሩ ሀይሉን፣ ደጃዝማች እንዳዋ ሀይሉን ይወልዳሉ። ከወይዘሮ አትጠገብ ደግሞ ልጅ ካሳ ሀይሉን (አፄ ቴዎድሮስን) ይወልዳሉ። ደጀዝማች ሀይሉ ሁለት ሴቶች ልጆች ነበራቸው። አንደኛዋ ወይዘሮ ወለተ ወርቅ ሌላኛዋ ደግሞ ወይዘሮ የሴፋ ነበሩ። ወይዘሮ ወለተ ወርቅን፣ አፄ ቴዎድሮስ ከፈረንሳዩ መልከተኛ ከሙሴ ሌዣን ጋራ አጋብተዋት ነበር። ከዚህ በተጨማሪ፣ እንግሊዛዊው ሄንሪ ዱፍተን፣ የደጃች ካሳ (አፄ ዮሐንስ) መልከተኛ፣ ምርጫ ወርቄ፣ ቴዎድሮስ የነጋሲ ዘር አላቸው ብሎ ነግሮኛል ይላል።*

***ቁጥር 8፤*** *ይህ ትንቢት ቀላል ግምት የሚሠጠው አልነበረም፣ እኤአ በ1830 አንድ ሰው፣ በጎንደር፣ ቀሀ የሚባል ወንዝ አጠገብ ጥሩምባ ነፍቶ፣ ቴዎድሮስ የሚባለው ንጉሥ እኔ ነኝ ብሎ አስነገረ፤ ተከታዮችም አግኝቶ ነበር። ወዲያውኑ ግን በሥልጣን ላይ የነበረው ንጉሥ አሰፈልጎ ካገኘው በኋላ፣ በጎንደር በአደባባይ በሰቅላት እንዲቀጣ አድርጎታል። ህዝቡ ነፃ የሚያወጣው ሰው ይጠብቅ ነበር። ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ እንኳን፣ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት፣ ምን ያህል እውነት እንደሆነ ባይታወቅም፣ ቴዎድሮስ ነኝ ብሎ ጭፍራ ያሰከተለ ሰው እንደወጣ፣ ሲታይ ግን፣ የሩሲያ ተወላጅ ሆኖ ስለተገኘ፣ ምኒልክ ገንዘብ ሠጥተው ወደ ሀገሩ መለሱት የሚል ፅሁፍ አለ።*



***ቁጥር 9፤*** *ካሳ ሀይሉ፣ ቸንከር ገዳም እየተማሩ እያለ የደምቢያው ደጃማች ማሩ ሲሸፍቱ፣ በዚያን ጊዜ የበጌምድር ገዥ የነበሩት የራስ ይማም ጦር ገዳሙን ሰብሮ በመግባት አብረው የሚማሩትን አርባ ሰምንት ልጆች ሰልቦ ካሳን ትቷቸው ሄደ። የካሳ መትረፍ ከእግዚአብሔር ነው በማለት ደብተራ ዘነብ ዘግበዋል። ከዚህ በኋላ፣ በተለያዩ ባላባቶች ቤት ባለሟል በመሆን አገልግለዋል፣ ያደጉት ግን በታላቅ ወንድማቸው በደጃች ክንፉ ቤት ነበር። ክንፉ ሲሞቱ በልጆቻቸው፣ በይልማና በመኮንን መሀከል በተደረገው ውጊያ፣ ካሳ የወገኑት ከመኮነን ጋር ነበርና፣ መኮንን ድል ሲሆን ካሳም ተማረኩ። አብሮ አደግ በመሆናቸው ምሯቸው ያውም ዝነኛ፣ ጉማው ረዥም ፈረሳቸውን መልሶ ሰጣቸው(ታጠቅ የሚባለው ፈረሳቸው ይህ ይሆን?)። ከዚያ በኋላ እቶ ቢተዋ ከሚባሉ የቋራ ገዥ ቤት ነበሩ። በዚሁ በፈረሳቸው ሆነው ባንድ ቀን ሁለት ዝሆን ገደሉ፤ ይህ ግን ቢተዋን ስላስቆጣ፣ ቢተዋን ጥለው ሸሽተው በየቦታውና በሸፍትነት ኖረዋል። ካሳ በሸፍትነት ዘመናቸው የሚታወቁት፣ የዘረፉትን መልሰው ለደሃ በማከፋፈል ነበር። ባህሩ ዘውዴ፣ "የአቢሲኒያው ሮቢን ሁድ" ይሏቸዋል።*

***ቁጥር 10፤*** *ትምህርቱን ያገኙት በናታቸው በኩል ገዳም ተልከው ነው። እናታቸው ኮሶ ሻጭ ናቸው ተብሎ ቢወራም፣ በሌላ በኩል ንብረት የነበራቸው ሴት እንደሆኑ ይነገራል። የኮሶው ታሪክ አመጣጥ፣ ሴትዮዋ፣ በጎንደር ኮሶዬ የሚባል ቦታ የነበራቸውን መሬት አስፈርደው ሲመለሱ፣ አብራቸው የነበረች ሠራተኛ የኮሶ ፍሬ ሸምጥጣ ወደ ጎንደር ይዛ ስትሄድ ያዩ ሰዎች ናቸው ይህን ወሬ የጀመሩት ይባላል። ወይዘሮ አትጠገብ ከዳሞቱ ደጃዝማች ወንድ በወሰንና የንጉሥ ዘር አለባቸው ከሚባሉት ከእናታቸው ከወይዘሮ ትሳል ቡዳሞት ነው የተወለዱት። አፄ ቴዎድሮስ በኮሶ የተነሳ የተበቀሉት፣ ከአቴጌ መነን የተላከ ቀኛዝማች ወንድይራድ የሚባል ሰው ነው። ወንድይራድ ይህን የኮሶ ሻጭ ልጅ ይዤ አመጣለሁ ብሎ ፎክሮ ነበር፤ ሆኖም ሲማረክ፣ ካሳ ፉከራውን ሰምተው ስለነበር፣ እግዚአብሔርን አመሰግነው፣ ለወታደሮቻቸው፤ ኮሶ የሚመገብ እንግዳ መጥቶብኛል ብለው ብዙ ኮሶ አሰበሰቡ። ለቀኛዝማች ወንድይራድም፣ እናቴ ከገበያው ኮሶ ሳይሸጥላት ቀረ፤ እህል ታጣና ይህንን ኮሶ ተመገብ ብለው ለቀኛዝማቹ ሰጡ። ይህን ሲያደርጉ ጦራቸውን ጭናቸው ላይ እንደያዙ ነበር። ሰውየው ግማሹን እንደጠጣም አሰመለሰው (አስተፋው)።*

***ቁጥር 13፤*** *የልጅ ካሳ የመጀመሪያ ድል የሚባለው፣ በሸፍትነታቸው ጊዜ፣ ከሌሎች ሽፍቶች ጋር፣ እኔም ባገኝ እናንተም ብታገኙ ባንድነት እንድንበላ ብለው ተማምለው ነበር። ሆኖም በቁጥራቸው በርከት ያሉት ሌሎቹ ሽፍቶች፣ ወንደሞቹ ሲገዙን የነበረው ላይበቃ እሱም የሌባ አለቃ ልሁን አለ ብለው ከካሳ ጋር የነበራቸውን መሀላ አፍርሰው ፍሪዳ አርደው መብላታቸውን የሰሙት ካሳ፣ ከአሰራ ሁለት ሰዎች ጋር ሆነው ገሰግሰው፣ ለምንድነው የከዳችሁ ብለው ሽፍቶቹን ሲጠይቁ፣ ሽፍቶቹ፣ አንተም የራስህን እኛም የራሳችን እንበላለን ባሉ ጊዜ፣ ካሳ ጎራዴ መዘው በለው ባሉ ጊዜ ሰባ ጋሻ(ሰባ ሰው) ሲሸሽ፣ ሰባቱ ተያዙና ተቀጡ። አስራ ሁለት ሆነው ሰባውን*

ሰው በእግዚአብሔር ሀይል አሸንፉ ተብሎ ተዘግቧል፡፡ ሰባቱ የከዱት ሰዎች፣ ከጉልበት በታች ነው የተቆረጡት፡፡ ይህ ደግሞ፣ ካሳ፣ ከልጅነት ጀምሮም ቢሆን ከሀደት በጣም የሚጠሉ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡

**ቁጥር 14**፣ ለይስሙላ ንጉሥ የነበሩት ሣልሳዊ ዮሐንስን (ፃዲቁ፣ አንዳንዴም ጆሉ ዮሐንስን የሚባሉትን ለመጥቀስ ነው)፡፡ የራስ አሊ እናት፣ መነን፣ የእቴጌነት ማዕረግ ለማግኘት ሲሉ ሰውየውን እንደባል አድርገው ቢይዙም ሥልጣኑ ግን በቤትዮዋና በልጃቸው ነበር፡፡ ሰውየው መጀመሪያ ሳር አምባ፣ ከዚያም መቅደላ በእስር ኖረዋል፡፡ መነንና ልጃቸው ራስ አሊ የእሮሞ ባላባቶች ናቸው፡፡ ከነራስ ጉግሳ ጀምሮ ሀገሪቱን ቢያስተዳድሩም፣ በሥርአቱ መሰረት የግድ ንጉሥ መኖር ስለነበረበት የጎንደር ነገሥታትን ለይስሙላ እያስቀመጡ ሥልጣኑን ይዘው ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ በህዝቡ ተቀባይነት ለማግኘት፣ ሀይማኖታቸውን ከእስልምና ወደ ክርስትና ይቀይሩ ነበር፡፡ በዚህ በተለይ በጣም የሚታወቁት ራስ ጉግሣ ነበሩ፡፡

እዚህ ላይ፣ በዘመኑ ሀይለኛ መሳፍንቶች ስለነበሩት ስለነራስ ጉግሣ ሥልጣን አመሰራረት መጥቀስ ተገቢ ነው፡፡ አፄ ተክለጊዮርጊስ የሚባሉ ንጉሥን ለመጀመሪያ ጊዜ፣ የየጁ ተወላጅ የሆኑ፣ ራስ አሊ (ትልቁ) በአፈረዋናት ውትሜራ የሚባል ቦታ መታቸው፡፡ ከዚያም ሥልጣኑን በመረከብ ለአራት አመታት በጌምድርን ሁሉ ገዛ፡፡ እሱ ሲሞት ወንድምየው አሊ ጋዝ አምስት ዓመት ገዝቶ ሞተ፡፡ ከዚያም የላስታ ሰዎች የሆኑ ራስ አሥራትና ራስ ወልደ ገብርኤል ሰባት አመት ገዝተው እርስ በርስ ሲጣሉ፣ ራስ ወልደ ገብርኤል ተሰደው ወደ መቅደላ በሸሹ ጊዜ፣ የመቅደላው ገዥ አመዬ፣ ጉግሣንና እሉላን ራስ ወልደገብርኤልን እንዲረዱ ላካቸው፡፡ ጉግሣ ግራዝማች ተብለው ፎገራ ተሥጣቸው፡፡ ጦርነቱም ወገራ ላይ ነበር፤ የራስ አሥራት ረዳቶች ደግሞ፣ ከጎጃም ራስ መርድ፣ ከሰሜን ራስ ገብሬ ነበሩ፡፡ በዚህ ጦርነት፣ ራስ ወልደ ገብርኤል፣ ራስ አሥራትና፣ ራስ መርድ ሞቱ፡፡ የተረፉት፣ የሰሜኑ ራስ ገብሬ ሸሹ፡፡ ድል የራስ ወልደ ገብርኤል ስለነበር ልጃቸው ወንበሩን ያዝ ቢባል በአባቱ ሞት እያለቀሰ እምቢ አለ፡፡ እሊጋው ከፍት በመሆኑ፣ እሉላ፣ ጉግሣን ባሊጋው ተቀመጥበት ብሎ ሲመክር፣ ጉግሣ ደግሞ፣ ማን ሥጠን ብለን ነው በሰው እሊጋ የምንቀመጥ ብሎ ሲጠይቅ፣ እሉላም፣ "ረቢ ሰጠን ብለን" ብሎ መከረ፡፡ ከዚህ በኋላ፣ እሉላ እንዲህ የሚል አዋጅ አስነገረ፤ "የምትንም እኛ፣ ያለንም እኛ፣ ለጉግሣ ያልታጠቀ፣ ወንዱ ብልቱን፣ ሴቱ ደግሞ ጡቱ ይቆረጥ፡፡" ብሎ አስነገረ፡፡ ይህንን አዋጅና አፈፃፀም፣ ሌሎች የዘገቡት፣ ጉግሣ ወንበሩ ላይ ለመቀመጥ የግድ ክርስትናን ተቀብሎ መጠመቅ ስለነበረበት፣ አንጠመቅም ያሉ የራሱ ዘመዶችን ብልትና ጡት አስቆርጧል ብለው ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ፣ የየጁው ጉግሣ፣ በጌምድርን፣ ጎጃምን፣ ወሎን ሁሉ ለሃያ ሰባት አመታት ገዝተዋል፡፡ በራስ አሥራት በኩል የተሰለፉት ባላባቶች፣ ራስ መርድ የደጃች ተድላ ጓሉ አያት ሲሆኑ፣ ራስ ገብሬ ደግሞ የሰሜኑ ገዥ የደጃች ውቤ ኃይለ ማርያም አያት ናቸው፡፡



ይህን የምጠቅሰው ልጅ ካሳ ድረስ ለማምጣት ነው፡፡ ጉግሣ በሞቱ ጊዜ፣ ልጃቸው ይማም ተተክተው ሁለት አመት ከዘጠኝ ወር ገዙ፡፡ የዚህ የራስ ይማም ጦር ነው ካሳ ይማሩበት በነበረው የቸንከር ገዳም ገብቶ ካሳ ሲያመልጡ ሌሎቹን ተማሪዎች የሰለበው፡፡ ራስ ይማም ሲሞቱ፣ ወንድምየው ራስ ማርዬ በቦታው ተተኩ፡፡ ራስ ማርዬ ከትግራዩ ገዥ ከሰባጋዲስ ጋር ደብረ ዓባይ ላይ ሲዋጉ፣ በሰባጋዲስ ልጅ በሀጎስ ተገደሉ፡፡ ሆኖም ድሉ የራስ ማርዬ ወገን ስለነበር፣ የራስ ማርዬ ሰዎች ሰባጋዲስን ገደሉ፡፡ ከራስ ማርዬ ቀጥሎ ወንድማቸው ራስ ዶሪ ለሶስት ወር ከገዙ በኋላ ሲሞቱ፣ በምትኩ፣ የጉግሣ ልጅ፣ የዶሪ፣ የይማም፣ የማርዬ ወንድም እሉላ ሥልጣኑን ያዙ፡፡ እሉላ ለሀያ ሁለት አመታት ገዝተዋል፡፡

እሉላ ከመነን ራስ አሊን ወለዱ(ትንሹ ራስ አሊ)፡፡ እነዚህ መሳፍንቶች ሲገዙ፣ ነገሲታቱን በስም እያስቀመጡ ሥልጣኑን በጃቸው ይዘው ነበር፡፡ እሉላ ሲሞቱ ልጃቸው ራስ አሊ በናታቸው በመነን ሞግዚትነት ሥልጣኑን ያዙ፡፡ መነን ደግሞ ለእቴጌነት ማዕረግ ሲሉ፣ ለምሳሌ የተቀመጡትን፣ የጎንደር ሰው ፃዲቁ ዮሐንስ እያሰ የሚጠሩቸውን ንጉሥ (ሳልሳዊ ዮሐንስን) አገቡ፡፡ በዚህ ዘመን ግን እንደ ደብተራ ዘነበ አገላለፅ ብዙ ነውር ነገር ይፈፀም ነበር፡፡ "ምንዝርና ከፍቶ ወንዶች በወንዶች ነውር ያደርጋሉ፤ ዘመዶቻቸው፣ ደሃን፣ የአበሻ ሰዎችን ሁሉ ይበድላሉ፤ መልካም መስራትን፣ እግዚአብሔርን መፍራትን ትተው፣ በስም ክርስቲያን ተብለው፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ፋንታ እስማት፣ ምንዝር፣ ስካር፣ ቧልት ባደረጉ ጊዜ፣ እግዚአብሔር አምላከ ቀናኢ ነውና፣ ሁሉን የሚቀጣ ንጉሥ ቴዎድሮስን አስነሳ፡፡" ይላሉ፡፡ እንግዲህ ቴዎድሮስ የነበራቸው ጀግንነትና ብልህነት ሳይጎድል በዚህ መሀል ብቅ ማለታቸው ለነበራቸው ተከታይ መብዛት ምክንያትም ነበር፡፡ "ያባቶቼን አገር አረከሱት" የሚሉት አባባላቸውም በዚህ ምክንያት መሆን አለበት፡፡

**ቁጥር 15**፣ ስለ ንግሥና ስማቸው ለወታደሮቻቸው የተናገሩት ደጃች ውቤን ሊወጉ ሰሜን በዘመቱ ጊዜ ነበር፤ ሊቀመኳስ ቤል በሩቅ መነፀር የደጃዝማች ውቤን ካምፕ አይቶ እንደዲነግራቸው ከጠየቁ በኋላ፣ ካምፑ መኖሩን ሲነግራቸው፣ "እያሳድረኝ አላሳድረውም" ብለው፣ ወታደሮቻቸውን ሲያነሳሱ፣ "እንኳን ይህን ቁርጥማታም፣ ሠለሠን መትቼ የሸዋውን ንጉሥ አይዘዋለሁ፤ ሰሜን ሰሜን እነግራሃለሁ ያልኩህ ወታደር፣ ስሜ ቴዎድሮስ ነው፡፡" አሉ፡፡ ከዚህ በፊት አስቀድመው ወታደሩን በንጉሥ አምላክ በል፤ ሰሜን ሰሜን እነግርሃለሁ ብለው ነበር፡፡

**ቁጥር 18**፣ ሰኔ ሀያ ሶስት፣ 1845(እ.ኢ.አ) ራስ አሊ ያላቸውን ሀይል በሙሉ፣ የሰሜን፣ የደምቢያንና የበጌምድርን ጦር ይዘው ከካሳ ጋር አይሻል የሚባል ቦታ ውጊያ ገጠሙ፣ ብዙ ሰው አልቆ "ደሙ እንደጎርፍ ወረደ፤ ሬሳውም እንደ ካብ ሆነ፡፡"፣ ራስ አሊም ተሸንፈው ሸሹ፡፡ ድሉም የደጃች ካሳ ስለሆነ፣ ደብተራ ዘነበ፣ "ንጉሥ በጠፋ በሰባ አንድ አመት፣ እግዚአብሔር ቴዎድሮስን አስነሳ፡፡ የኦሮሞዎች ግዛት፣ በበጌምድር፣ በጎጃም፣ በላስታ፣ በየጁ፣ በወሎ በዚህ ነው ያለቀው፡፡" ይላሉ፡፡ እንግዲህ የተራ ጉዳይ ሆኖ ነው እንጂ፣ ራስ ማርዬም ቢሆን፣ የትግራዩን ባላባት፣ ከተከዜ እስከ ቀይ

ባህር ድረስ የነበረውን ግዛት ባንድ ጦርነት እንዳከተሙት ተገልጧል:: ቴዎድሮስ የነገሱት ደጃዝማች ውቤን ድል ካደረጉ በኋላ በየካቲት አምስት ቀን ነበር::

**ቁጥር 19፣** ስለ ሰውነታቸው ጥንካሬ ሲነሳ፣ የብሪታኒያው መልከተኛ ራሳም፣ የወንዝ ዳርቻ ሲሻገር አንሸራቶት ሊወድቅ ሲል ቴዎድሮስ በፍጥነት በእጃቸው ይዘው እንዳወጡትና በአረብኛ አይዞህ በርታ ብለው መናገራቸውን ገልጧል:: የንጉሡን የሰውነት ጥንካሬ በእጃቸው እያያዝ ምስክርነት ይሰጣል:: ራሳም ሲጨምርም፣ ንጉሡ ከድንጋይ ወደ ድንጋይ በባዶ እግራቸው በፍጥነት እየዘለሉ ሲንቀሳቀሱ በማየቱ የተገረመ መሆኑን ይገልጣል:: በሌላ አጋጣሚ፣ ሄንሪ ዱፍተን የሚባል እንግሊዛዊ ያየውን ሲመሰክር፣ ቴዎድሮስ የኮርቻውን እርካብ ሳይረግጡ ዘለው ፈረሱ ላይ በመውጣት በፍጥነት አይጋለቡ ሲሄዱ አይቶ "ፈጣንና ንቁ" ናቸው ብሎ መስክሯል:: ራሳም፣ ቴዎድሮስ ጉግሥ ሲጫወቱ፣ ከዚያም የውጊያ ትርኢት ሲያደርጉ አይቶ፣ ፍጥነትና የጦር አያያዛቸው የተለየ ነው ይላል:: የሚገርመው፣ ይህንን ትርኢት ካሳዩ በኋላ፣ ወደ ራሳም ሄደው፣ "ሚስተር ራሳም፣ ራሳችን ለማዝናናት ባደረግነው በዚህ ኋላ ቀር ነገር መቼም አትስቅብን:: የናንተን የውጊያ አይነት ለማየት በጉጉት እጠብቃለሁ::" ብለውታል::

**ቁጥር 20፣** ቴዎድሮስን በመጀመሪያው የሥልጣን ዘመናቸው ተወዳጅ ሊያደርጓቸው የቻሉ በሳቸው በኩል የተወሰዱ ርምጃዎችን መጥቀስ ተገቢ ነው:: ይህን የምጠቅሰው ደግሞ፣ ከእንግሊዛዊ ፀሀፊ፣ ከሄንሪ ዱፍተን፣ ያገኘሁትን ነው:: ከብዙዎች የውጭ ፀሐፊዎች፣ ቴዎድሮስን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የገለጠ ቢኖር ዱፍተን ነው:: ይህ ምስክርነት ሰፋ ያለ ስለሆነ ያንባቢዎችን ትግስት በፅሞና እጠይቃለሁ:: ዱፍትን በመጀመሪያ ስለቴዎድሮስ ገፅታ ሲገልፅ፣ "ጠየም ያሉ ሆነው ግን በምንም አይነት የኔግሮ ገፅታ አይታይባቸውም ይላል:: ሲቀጥልም፣ ግንባራቸው ከፍ ብሎ ጎላ ወይም ወጣ ያለ ነው፤ መላ ገፅታቸው አውሮፓዊ ነው የሚመስሉት፣ ጠጉራቸው በወፍራሙ ተጎንጉኖ ባንገታቸው ጀርባ ይወርዳል:: አይኖቻቸው ጥቁር ሲሆኑ፣ እሳት የለበሱ ይመስላሉ፣ ፈጣንና በስተው የሚገባ ዕይታ አለባቸው:: አፍንጫቸው እንደ ሮማዊ አፍንጫ ሰልከክ ብሎ ጫፉ ላይ ሾል ብሎ ግን ለአመል ያህል ሰበር ይላል:: አፉቸው በትክክል የተሠራ ሆኖ፣ ፈገግ ሲሉ ደግሞ በጣም ተስማሚና፣ አስደናቂ ነው ይላል:: መላ ባህሪያቸው፣ ሰው አክባሪ፣ አስደሳችና ሊጋስነት ይታይበታል:: ጠቅላላ ሁኔታቸው፣ እርፈው ተቀምጠው ቢሆን የብልህነትና የበጎ ስሜትን ያሳያል::" ይላል::

ቴዎድሮስ በተከታታይ ያወጧቸው አዋጆች እንደሚከተሉት ነበሩ:: የመጀመሪያው፣ "ሁሉም ሰው ወደ ነበረበት ሙያ እንዲመለስ፤ ነጋዴው ወደ ንግዱ፣ ገበሬው ደግሞ ወደ እርሻው"፤ በዚህ አዋጅ፣ በእርስ በርስ ጦርነት ታምሶ የነበረው ሀገር ወደ ሰላምና ብልፅግና እንዲመለስ ታስቦ ነው:: ይህንን ህግ ለማጠናከር፣ ወታደሮቻቸው ምግብ እየገዙ እንዲበሉ እንጂ፣ ገበሬውን እንዳይዘርፉ አደረጉ:: ከዚያም መደበኛ የወታደር ሥርአት መስረተው ደሞዝ እየተከፈለው እንዲተዳደር ለማድረግ አሰቡ:: ይህ መደበኛ ወታደር ደግሞ ጠመንጃ የታጠቀ እንዲሆን ወሰኑ::



የሃረውን ጦርና ጎራዴ ግን፣ ወደ ማረሻ፣ መቆፈሪያና የርሻ መሳሪያ እንዲቀየር ፍላጎታቸው መሆኑን ገለጡ:: ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ ገበሬው በየመንደሩ፣ በራሱ ዳኛ እንዲዳኝ እንጂ እየዘረፈ በሚበላ ወታደር እንዳይዳኝ ወሰኑ:: (የመጨረሻው፣ ከተገላውደን ሪፖርት ነው) በጦርነት ምክንያት ተዘግተው የነበሩ የንግድ መንገዶች እንዲከፈቱ፤ የቀረጥና የግብር ሁኔታም ቀለል ያለ እንዲሆን አደረጉ:: ለሥራ ከመጡት ሰዎች ጋር በመሆን መደበኛ መንገድ መስራት እንዲጀመር፣ መንገዶቹም ከደብረታቦር ወደ ጎንደር፣ ወደ ጎጃምና ወደ ዋናው ምሽጋቸው ወደ መቅደላ የሚወስዱ እንዲሆኑ ነበር:: እንግዲህ አቢሲኒያን በመሰለ ሀብታም ሀገር እንደዚህ አይነት መደበኛ መንገድ ተሠርቶ አያውቅም ነበር:: በሀገሪቱም የድንጋይ ከሰልና የብረት ማዕድን ያለባቸው ቦታዎች እንዲታሰሱ ፈልገው ነበር:: በተጨማሪም ንቁ የሆኑ የአቢሲኒያ ልጆች ወደ ውጭ ሀገር፣ ፈረንሳይና እንግሊዝ አገር ተልከው የእጅ ሙያ ተምረው እንዲመለሱ፤ የእጅ ባለሙያተኛ የሆኑ የውጭ ሰዎችም ወደ ሀገሩ መጥተው ኗሪ እንዲሆኑ ለመሳብ ሞከሩ::

ምፅዋ በቱርኮች ቁጥጥር ስር ስለነበር፣ በቂ የጦር መሳሪያ ወደ መሀል አቢሲኒያ እንዲገባ ስለማይፈቅዱ፣ ቴዎድሮስ፣ መሳሪያዎች በመሀል ሀገር መሰራት እንዳለባቸው ወስነዋል:: በጉቦ የባለገውና ሥርአት ያጣው የዳኝነት ሥርአት እንዲታደስ ያደረጉ ሲሆን፤ ለዚህም ድጋፍ ለመስጠት፣ በሄዱበትና ባረፉበት ቦታ ሁሉ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በማቋቋም የተበደሉ ሰዎችን ከርከር ራሳቸው መስማትና መበየን ጀመሩ:: (ይህንን ይግባኝ ሰሚነት አውሮፓውያኑ ሲያናንቁት ይታያል)

ለድሆች የተለየ እንክብካቤ በማድረግ፣ ችግራቸውን ማዳመጥና፣ ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊትም ምፅዋት ይሰጡ ነበር:: በሰብአዊ ርህራሄ ስሜትና እንደ አስተዳደራቸው ፖሊሲ በመቁጠር በዘመቱበት ቦታ ሁሉ ለድሆች ገንዘብ ይበትኑ ነበር:: በዶክተር ከረፕ ሚሲዮናዊ ጥናት ውስጥ የተገኘ መረጃ እንደሚጠቁመው፣ ቴዎድሮስ፣ "እኔ ራሴ ድሃ ነበርኩ፤ ድሆችን ባልረዳ፣ ለፈጣሪ ስሞታ ያቀርባሉ" ይሉ ነበር:: ለናፒየር በፃፉት በመጨረሻው ደብዳቤ፣ "ራሴ የምጦራቸው ሰዎች" በማለት፣ የሚያስተዳድሯቸው ባልቴቶች፣ ሴቶችና ህፃናት እንደነበሩ ይጠቅሳሉ:: በተለያዩ ጊዜያት የሚሠጡት ፍርድም በሰው መወደድንና መደነቅን አትርፎላቸው ነበር:: ሁለት ምሳሌዎች ለመጥቀስ፣ ሁለት ሰዎች ተካሰው ንጉሡ ፊት ቀረቡ፣ አንደኛው ላንዱ ፈረስ በትውስት ሠጥቶት ኖሮ፣ ተቀባዩ ግን ይከዳል:: ሠጭው ሰጥቸዋለሁ ብሎ ሲምል፣ ተቀባዩ እግዚአብሔርን በመፍራት መቀበሉን ያምናል:: ይህን የሰሙ ቴዎድሮስ፣ ሰውየው በነበረው ፈሪሀ እግዚአብሔር ምክንያት፣ እዳውን እኔ እከፍልሃለሁ በማለት ለከሳሹ ፈረስና ብር ሠጥተዋል::

ሌላው ምሳሌ ደግሞ፣ በጋይንት አያሉ፣ የቴዎድሮስ ወታደር ባላገር ይገድላል:: ዘመዱ የሞተበት ሰው ንጉሡ ፊት ቀርቦ ጮኸ፤ ቴዎድሮስ ወታደሮቻቸውን ቢጠይቁ (በአፈርሳታ)፣ ወታደሮቹ አላደረግንም አሉ:: ንጉሡም ተጨንቀው ነበርና አሰበው እንዲህ አሉ፤ "ወታደር ብላ፣ ባላገር አብላ፤ ብዬ ያዘዝኩ እኔ ስለሆንኩ፣ ደመኛህ እኔ

ነኝ፣ እኔን ግደለኝ።" ብለው ገበሬው ነገሩት። ባለ ደሙ (ዘመዱ የሞተበት ሰው)፣ እኔ ንጉሥ መግደል አይቻለኝም አለ። ንጉሡም ብዙ ብር ሠጥተው ሰደዱት።

በሀይማኖታቸው፣ ያባቶቻቸውን ሀይማኖት የሚጠብቁ ቢሆኑም፣ በገዳም ሲማሩ(ቸንከር) ያስተዋሉትን በመገንዘብ፣ ቤተክርስቲያኗም ሆነ የመንግስት ሥርዐት ለውጥ ማድረግ እንደሚገባቸው ወስነዋል። ቁጥራቸው የላቀ ቄሶችና ደብተራዎች፣ የግዛታችውን ጠቅላላ መሬት አንድ ሶስተኛውን ይቆጣጠሩ ነበር። ይህ ለቤተክርስቲያን ሲሶ ወይም አንድ ሶስተኛ መወሰን አመጣጥ፣ በዛጉዌ ሥርወ መንግስትና በሰሎሞን ሥርወ መንግሥት መሀከል በመነኩሴው በተክለሀይማኖት አማካኝነት ከተደረገው ስምምነት ነው። ካህናቱ ይህንን መሬት ለገበሬዎች በኪራይ እያሳረሱ፣ የተንደላቀቀ ኑሮና፣ እልፎ አልፎም ስካርና የረከሰ ባህሪ ያሳዩ ነበር። ቴዎድሮስ፣ ከደብሮች አካባቢ የተወሰኑ መሬቶች በስተቀር፣ ሌላው ወደ መንግሥት እንዲመለስ አደረጉ። ይህ ውሳኔያቸው ከካህናቱና መነኮሳቱ የመረረ ጥላቻ ቢያመጣባቸውም፣ ቴዎድሮስ ለድሆች በሚያሳዩት ደግነት፣ ከሀይማኖት ጋር ጠብ እንደሌላቸው ምስክር ሆነ። ከዚህ ከተወረሰ መሬት የሚገኘው ገቢ ደግሞ ለወታደሮቻቸው ደሞዝና ለሌላው ለሀገሪቱ ዕድገት ለሚያስቡት ዕቅድ የሚውል ሆነ። ራሳቸው ግን፣ እንደ ተራ ሰው እንጂ ንጉሣዊ ያልሆነ ኑሮ ይኖሩ ነበር። ይህ አኗኗር፣ ከመጨረሻ ሚስታቸው ከእቴጌ ጥሩ ወርቅ ጋር የግጭት መንስኤ ነበር። እቴጌዋ፣ ንጉሡ እንደ ንጉሥ እንዲኖሩ ትመኝ ነበር።

ቴዎድሮስ፣ የተበተነ ሀገር ብቻ ሳይሆን፣ በራሷ በኦርቶዶክስ ሀይማኖት ውስጥ ከባድ የተከፋፈለ ወገን ነበር ያጋጠማቸው። ይህ ክፍፍል ደግሞ ከጠብ አልፎ ለውጊያና ለእርስ በርስ ግጭት የዳረገ ነበር። ክፍፍሉ የመጣው በክርስቶስ ባህሪ ትርጉም፣ በአንድ ወገን ፀጋ፣ በሌለው ወገን ቅባት እንዲሁም ካራ እየተባሉ በሚጠሩ በቤተክርስቲያኗ ሊቃውንቶች መሀከል ነው። ቴዎድሮስ በሀይላቸው የተበነውን ሀገር ሲያገኙ፣ አብረዋቸው የነበሩት፣ አቡነ ሰላማ ደግሞ ሀይማኖቱን አንድ ለማድረግ ጥረው ነበር። በዚህ በኩል ቴዎድሮስ የሞከሩት ሳይሳካ ቀርቶ፣ በኋላ አፄ ዮሐንስ (አራተኛ)፣ ሊቃውንቱን ቦሩ ሜዳ ላይ አከራክረው ነው አንድነት የተፈጠረው። ይህንን የነበረ፣ በትርጉም የተነሳ ክፍፍል፣ የአሁኑ ዘመን የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዮች አምብዛም አያውቁም። አሁን ያለቸው ቤተክርስቲያን በትርጉም ሳይሆን በሌላ መንገድ ተከፋፍላ ትታያለች። ቤተክርስቲያኗ፣ በጣልያን ወረራ ጊዜ ጉልህ የሆነ የሀገር ወዳድነት ስሜት ያንፀባረቀችበት ጊዜ ቢሆንም፣ በሌሎች ታሪኮች ግን የራሷን ጥቅም ለመጠበቅ ስትል ለዕድገት እንቅፋት እንደነበረች ግልፅ ነበር። የቤተክርስትያን መሪዎችን የመረረ ጥላቻ የተቀበለ መሪ እንደ ቴዎድሮስ ያለ የለም። በተገኘው አጋጣሚ ንጉሡን በአደባባይ ይዘልፉም ነበር። በዚህ አንድ የሚጠቀስ ነገር ቢኖር፣ ንጉሡ፣ ከደብረታቦር ተነስተው መቅደላ በመከራ በደረሱበት ጊዜ፤ ሁለት ካህናት፣ ንጉሡን፣ እርስዎ ሀይማኖትዎን ከደዋል፤ ፆሙን አላከበሩም፤ ወታደሮችዎም ሥጋ እንዲበሉ አድርገዋል፤ ብለው ሲኮንኗቸው፤ አፄ ቴዎድሮስ ግን፣ በተለመደው ስድባቸው፣ "አህዮች" በማለት፣ መቅደላ ላይ መልሼ ባያችሁ፣ በጅራፍ ነው



የሚያስገርፉችሁ በማለት፣ ሰዎቹ ከነህይወታቸው ከመቅደላ እንዲወጡ አድርገዋል። ዘመኑ ቴዎድሮስን በሀይማኖት ስማቸውን እንደሚያጠፉ፣ ንጉሡ ይህንንም እንደሚያውቁ፣ ራሳቸው ቴዎድሮስ ለናፒየር በፃፉት የመጨረሻ ደብዳቤያቸው ጽሰውታል።

ሌላው አዋጅ፣ ትዳር በአንድ ወንድና ሴት መሀል እንዲሆን እንጂ ብዙ ሴቶች ማግባትን የሚከለክል ነው። በርግጥ ይህ ህግ የነበረ ቢሆንም፣ ብዙ ሰዎች ህጉን የተላለፉ ስለነበር ህጉን የሚያስከበር አዋጅ ነው የወጣው። ከአዋጁ በተጨማሪ፣ አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸው፣ ለችግራቸው ሰዎች ገንዘብ እየሠጡም ያጋቡ ነበር።

ሌላው ተጨማሪ ህግ፣ በግዛታቸው ውስጥ የባሪያ ንግድ እንዲቆም ማድረጋቸው ነበር። በዚያን ጊዜ፣ እንደ ዱፈተን ገለጣ፣ የባሪያን ንግዱን የሚያካሂዱት ሞስሊሞች ሲሆኑ፣ በባሪያነት የሚጋዙት ደግሞ በደቡብ በኩል የሚገኙ ተወላጆች ነበሩ። ጎጃም ውስጥ ባሶ የሚባል የገበያ ቦታ ዋና መናሀሪያ ሲሆን፣ ከዚህ ተነስቶ በምፅዋ ሆነ በመተማ በኩል ንግዱ ወድ ውጭ ድረስ ይሄድ ነበር። ቴዎድሮስ፣ የራሱን ወገን ክርስቲያን የሆነን ዜጋ የሚሸጥ ከተገኘ የሞት ቅጣት ይፈረድበት ነበር። ሆኖም የተጠለፉ ክርስቲያኖች በግድ ወደ ሙስሊምነት እንዲቀየሩ ተደርገው በቱርክ ግዛቶች በሙሉ ይሸጡ ነበር። ሰዎቹም፣ አንድ ቀን ሁሉ ወደ ሀገራችን እንመለሳለን በማለት ለሚያምኗቸው ሰዎች ክርስቲያን እንደነበሩ ይናገሩ ነበር። አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸው ባሶ ገበያ ድረስ ሄደው፣ ለሽያጭ የቀረቡትን ባሮች ከወሰዱ በኋላ፣ በበጌምድር፣ ጉና የሚባል ቦታ በመውሰድ ነፃ ለቀው፣ "የወደድካትን ሥሪ" በማለት እርስ በራሳቸው ተመራርጠው እንዲጋቡ ፈቅደው አጋብተዋል።

ቴዎድሮስ በዘመነ መሳፍንት ያዩትን ግፍና በደል ለማስወገድ ነበር ከቋራ ጀምረው የተነሱት። ሌሎችም እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ አብረው የወደቁ ይህንን የቴዎድሮስን አላማ የሚደግፉ ሰዎች ነበሩ። እንደ ዱፍተን አገላለፕ፣ እንደ ቴዎድሮስ ያለ ሀገር ወዳድ ንጉሥ በዚያች ሀገር ተፈጥሮ አያውቅም። ቴዎድሮስ የጠፋውን የአባቶቼን ሀገር እመልሳለሁ በማለት የተለያዩ ግዛቶችን በጉልበት በማዋሀድ ኢትዮጵያን እንደገና መሰረቱ። አዲሲቱ ኢትዮጵያ ከቀድሞዋ ኢትዮጵያ በስፋት ያነሰች መሆኗን ጠንቅቀው ያውቃሉ። ቱርኮች የምፅዋን ወደብ እኤአ 1570 ጀምሮ ለብዙ አመታት ይቆጣጠሩ ነበር፤ ግብፆችም በምዕራብ ድንበር የታቻላቸውን ያህል መሬት እየወሰዱም ነበር። ለዚህም ይሆናል፣ ቴዎድሮስ ለራሻው ዛር ኒኮላስ የወዳጅነት ስሜት የነበራቸው። ከቱርኮች ጋራ በክሬሚያ ስለሚዋጋ። ለኒኮላስ፣ ሱልጣን አብረን እንውጋ በማለት ደብዳቤ ልከው እንደነበር ይነገራል። ያባቶቼን ሀገር አረከቡ የሚሏቸውን የውስጥ መሳፍንቶች እንበርከከው፣ ረዥሙ ዕቅዳቸው ቱርኮቹን ከግዛታቸው አስለቅቀው ኢየሩሳሌምን ነፃ ለማውጣት ነበር። እዚህ ላይ አንባቢ ነገሩን ወደ እስላምና ክርስቲያን እንዳይቀይር መጠንቀቅ አለበት። ቴዎድሮስ የሀገራቸው ጠላት ከሆነ፣ እስላም ሆነ ክርስቲያን አይለዩም። ገና በሽፍትነት ዘመናቸው፣ ኢድሪስ የተባለ ሻንቅላ ተወላጅ ወዳጃቸውና አጋራቸው እንደነበረ መታወስ አለበት። ከዚህ በተጨማሪ፣ ቴዎድሮስ፣ በሱዳን ለነፃነታቸው የሚታገሉ

በግብፅ ላይ የተነሱ አማፅያንን ይረዱ ነበር፤ የእመፅ መሪ የነበረው ወድ መከ ነምሬ፣ በቴዎድሮስ ግዛት ሥር መጠለል ብቻ ሳይሆን፣ በቴዎድሮስ ሰም ሱዳን እየዘለቀ ግብር ይሰበስብ ነበር:: ለዚህ ደግሞ ሌላ የሚጠቀስ ሁኔታ ቢኖር፣ ቴዎድሮስ በጣም ያስቸገራቸውና አልጨበጥ ያላቸውን አመፀኛ አመዴ በሽርን ሲያሳድዱ፣ አንድ ሙስሊም፣ ሰው ገድሎ ፊታቸው ይቀርባል:: ንጉሡም ሰውየውን፣ ምን ብለህ ገደልከው ብለው ይጠይቃሉ፤ ገዳዩ ሲመልስ፣ ወንድሜን ስለገደለ ነው ይላል:: ቴዎድሮስም፣ ወንድምህን እሱ እንደገደለው በምን አወቅህ ብለው ሲጠይቁት፣ ሰውዬው ሲመልስ፣ ካፊርና(ክርስቲያን) እስላም፣ ከነቢዩ ጀምሮ እስከ ግራኝ፣ ከግራኝ እስካሁን ደመኞች ነን ይላል:: ቴዎድሮስ ሰውየውን ከቀጡ በኋላ፣ "ከአመዴ በሽር ጋር የተጣላነው ባገር ነው ብዬ ነበር የውነት ደም ነን" ብለዋል:: ደመኞች ነን ማለት፣ አንዱ አንዱን ለመግደል ቀድሞ የወሰነ ወይም በሞት የሚፈላለግ ማለት ነው:: እንደሳቸው አባበል፣ ውጊያው የአገር ጉዳይ ነው የነበረው::

በሀገራቸው፣ ሌላ አይነት የክርስትና እምነት እንዲሰበክ እንዳልፈቀዱ ይታወቃል:: አይሁዳውያንን ወደ ክርስትና እምነት ለመቀየር ከአወሮፓ ተነስተው የመጡ ሚሰዮናውያን፣ ሰዎቹን ወደክርስትና እምነት ቢቀይሩም ወደ ኦርቶዶክስ ሀይማኖት እንጂ ወደ ሌላ እንዳይሆን ቴዎድሮስ አግደው ነበር:: በክርስትና ሀይማኖት ሰም፣ በተዋህዶና በካቶሊክ፣ እንዲሁም በራሷ በተዋህዶ ውስጥ የነበረው ክፍፍል ብዙ ብጥብጥ ያስከተለና ለህይወት ማለፍ ምክንያት እንደነበረ ንጉሡ ጠንቅቀው ያውቁ ነበር:: ንጉሡ ፀሎት አሰልሰው አያውቁም ነበር፤ ቤተክርስቲያን መድረስ ካልቻሉ፣ ከሰዎቻቸው ዞር ብለው ወደ ጫካም ቢሆን ገባ ብለው ይፀልዩ ነበር:: ይህን ሁኔታ ያስተዋለው ራሳም በመፅሐፉ ዘግቦታል::

ይህን ሁሉ ዕቅድ ያወጡት፣ ለድሃ ህዝብና፣ ለተበደለው፣ ለተማረረው መልስ የሰጡ ንጉስ በየቦታው አመፅና ሸፍትነት ሲጀመር በጣም መናደዳቸው የሚገርም አይሆንም:: ከዚህ በተጨማሪ የኢጋራቸው፣ የባለቤታቸው፣ እሮምዋ እቴጌ ተዋበች ሞትና፤ የወዳጆቻቸው የሊቀ መኳስ ዮሐንስ(ጆን ቤል) እንዲሁም የቆንስል ፕላውደን ሞት በጣም እንደቀየራቸው ይታወቃል:: ሊቀ መኳስ ዮሐንስ (ጆን ቤል)፣ ለአፄ ቴዎድሮስ የሼክስፔርን ሥራዎች ያነብላቸው እንደነበርና አሳቸውም የሼክስፔርን ፅሁፎች፣ "የዮሐንስ መፅሐፍ ቅዱስ ይሉ ነበር:: አፄ ቴዎድሮስ ለተዋበች የነበራቸው ፍቅር የተለየ እንደነበር በሁሉም ታሪክ ዘጋቢዎች ይጠቀሳል:: ቴዎድሮስና ተዋበች አንድ ላይ ሲሆኑ መፅሐፍ ቅዱስ አብረው ያነቡ ነበር:: እቴጌዋ ሲሞቱ፣ ቅኔ ይችላሉ የሚባሉት ቴዎድሮስ የገጠሙትን ማስታወስ፣ ንጉሡ ለባለቤታቸው የነበራቸውን ሰሜት ይገልፃል:: ግጥሙም፣ "እስኪ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሄድ፣ እቴጌ ተዋበች ሚሰት ናት ገረድ" የሚል ነበር:: እቴጌ ተዋበች ከሞቱ በኋላ፣ አንድ ጊዜ፣ በእርካብ ምክንያት እግራቸው ቆስሎ አልድን ሲል ያዩ ተከታዮቻቸው፣ "አይ፣ ምሽቱ ነበረች እንጂ ሀብቱም ነበረቱም፣ እሷ ከሌለችማ ምን ዋጋ አለው::" ሲሉ ተሰምተዋል:: እሳቸውን በጣም ያበሳጫቸው የሚመስለው ግን፣ ራሳቸው የተራ ሰው እየኖሩ ሲረዷቸውና ኑሯቸው እንዲሻሻል ቀን ከሌሊት የሚጥሩላቸው የሀገሬቱ ዜጎች፣ ንጉሡን በሚፃረር



ሥነገድ ሲሰለፉ በማየታቸው ነው:: ለዚህ ደግሞ ይህ የቴዎድሮስ አባባል ዋቢ መሆን ይችላል:: "እኔ ያሰብኩት" ይላሉ ቴዎድሮስ፣ "ፈጣሪ ያስነሳኝ ለህዝቡ በረከት እንድሆን ነበር፤ ነገር ግን፣ እንዳየሁት ከሆነ ተሳስቻለሁ፤ ለዚህ ነው መድፌ ላይ፣ "ቴዎድሮስ የርጉማኖች መቅሰፍት የሚል ፅሁፍ ያስቀረፅኩበት" (የመጨረሻው፣ ከሊ.ፑን መፅሀፍ የተወሰደ)

**ቀጥር 21**፤ በአመፅ ከተነሱ፣ የመጀመሪያው የነበረው፣ ራሳቸው ጎጃም ላይ የሾሟቸው፣ ተድላ ጓሉ መሸፈት ነበር:: ከዚያም ደግሞ ዘመቻ በወጡበት ጊዜ ከፍተቱን በመጠቀም፣ የወንድማቸው ልጅ፣ ጋረድ ከንፉ፣ በመሸፈት ጎንደርንና የሰሜን ክፍሉ መዝበርበዝ ጀመረ:: ይኸው የወንድማቸው ልጅ ነው እንግዲህ ለሁለቱ እንግሊዛውያን ወዳጆቻቸው፣ ለፕላውደንና ለጆን ቤል ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው::

የኦሮሞ አመፅ ከተነሳ፣ ቴዎድሮስን በጣም ያወካቸው አመዴ በሽር የሚባል ሰው ነው:: ሰውየው፣ ንጉሡ በዘመቱበት ቁጥር ስለሚሸሽ በእጃቸው ሊገባ አልቻለም:: በሱ ጦስ ብዙ ችግሮች ተፈጥረዋል፤ የብዙ ሰዎች ሕይወትም አልፏል:: በሱ ምክንያት ንጉሡ ወሎን ሰባት ጊዜ ነው የተመላለሱበት:: ቴዎድሮስ አገሩን አስገብረው ሲሄዱ ወይም ወደ ሸዋ ሲሻገሩ ከጀርባቸው በሚሸፍተው ሰው ላይ ከባድ ቅጣት ነበር የሚያደርሱት:: በተረጋጋ ጊዜ ትዛዝ ተላልፍው የገበሬ የቁም ከብት አርደው የበሉ የራሳቸውን ወታደሮች እንኳን ይቀጡም ይገሉም ነበር:: በአመዴ በሽር የተነሳ፣ የራሳቸው በቅርብ የሚተማመኑባቸው የመቅደላ አዛዥ የነበሩት ግራዝማች አለሜ ከድተው ነበር(በኋላ ደጃዝማች):: ይህም የሆነው ከአመዴ በሽር ጋር ተላልከሀል ተብለው ንጉሡ ይገድሉሃል ብሎ የራሳቸው ሎሌ ስለነገራቸው ነው:: በሸዋም ቢሆን፣ ቴዎድሮስ የሾሟቸው መርዕድ አዝማች ሀይሌን፣ ሰራህ ብዙ የሚባል ሰው የአመዴ በሽርን መልክተኛ በሚሰጥር ተቀብለህ አልብሰህ ሰደሃል ብሎ በቴዎድሮስ ፊት ከሰሳቸው:: መርድ አዝማቹ፣ መልክተኛው መጥቷል ግን አይሆንም ብዬ መልሼ ሰደድኩት ብለው አመኑ:: ቴዎድሮስም መርድ አዝማቹን አሰረው፣ ሰራህ ብዙን፣ ሸዋ ላይ ማንን ልሹምብት ብለው ቢጠይቁ፣ ሰራህ ብዙ፣ አቶ ዳርጌን ቢሾሙ ሸዋ ደስ ይለዋል ሰላሉ፣ የንጉሥ ሳህለ ሥላሴ ልጅ አቶ (አቤቶ) ዳርጌ ተሾሙ:: በሳምንተኛው ቀን ግን፣ ጃራ የሚባል ሰው፣ ራሱን ሰራህ ብዙን ከዳርጌ ጋር ውሥጥ ለውሥጥ ተማምሏል ገንዘብም ከፍሏል ብሎ ቴዎድሮስ ፊት ከሰሰው:: ነገሩ ሲጣራ ውነት ሆኖ ስለተገኘ፣ አቶ ዳርጌም ታሰሩ፣ ሰራህ ብዙም በንጉሡ ተወረፈ:: በተጨማሪም፣ የለገ ጎራና የወረ ኢሉ ገዥዎች ከአመዴ በሽር ጋር ተነጋግረሃል ተብለው እርስ በርስ ተካሰው ሁለቱም ቴዎድሮስ ፊት አመኑ:: ሁለቱም ሰላመኑ፣ ቴዎድሮስ ቅጣቱ ወደ እስር ብቻ እንዲቀየር አደረጉ:: እንግዲህ መቅደላ ላይ የተሰበሰቡ የአቢሲኒያ እስረኞች፣ በተለይ የባላባቶቹ አመጣጥ በአብዛኛው በዚህ ምክንያት ነው የነበረው:: እስረኞቹ፣ አውሮፓውያኑ እንደሚያስወሩት ሁሉም ከጥፋት ንፁህ የነበሩ ሰዎች አልነበሩም:: የተወሰኑ የራሳቸውን ሰዎች በፍራቻና በጥርጣሬ አስረዋል:: አቤቶ ዳርጌም መቅደላ ነበሩ:: ቴዎድሮስ ከእሰራት ይልቅ በሞት መቅጣት ይችሉም ነበር:: ዳርጌ የአፄ ምኒልክ አጎት ናቸው:: ቢያሰሯቸውም፣

ቴዎድሮስ፣ ዳርጌን፣ "ዳሩ" ብለው ይጠሯቸው ነበር። የመርድ አዝማች ማዕረግ ከተነሣ፣ የሸዋ ገዥዎች በሳህለ ሥላሴና በሀይለ መለኮት ጊዜ ራሳቸውን ንጉሥ እያሉ እንደሚጠሩ ግልፅ ነበር። ሆኖም አፄ ቴዎድሮስ፣ ሸዋን ካስገበሩ በኋላ ነው ንጉሥ የሚባል ማዕረግ እንዳይጠቀሙ በመከልከል የመርድ አዝማች ማዕረግ የተጀመረው።

አፄ ቴዎድሮስ ከኦሮሞዎች ጋራ ብዙ ጦርነቶች ቢያካሂዱም ኦሮሞና አማራ አንድ ለማድረግ አስበው የማሉበትን ታሪክ መጥቀስ ተገቢ ነው። ከዚህ ቀደም እንደተጠቀሰው፣ ንጉሡ በወሎ ከተለያዩ የኦሮሞ ባላባቶች ጋር ተዋግተዋል። በዘመቻቸው በአንዱ፣ ጊምባ የተባለ ቦታ ሲሄዱ ኦሮሞ አንድነት ሆኖ ከበባቸው። ንጉሥ ቴዎድሮስም በትንቢት ፈከሩ፣ እንዲህ ብለው፡ "ኦሮሞና አማራን ባንድ ሰደቃ(ማዕድ) ያላበላሁ እንደ ሆነ እኔ የክርስቶስ ባሪያ፣ የቅዱስ ዮሐንስ ለት። ክርስቲያን አትበሉኝ።" አሉ። በጳጉሜ፣ ኦሮሞ ሁሉ ከበበ፣ ጊምባ ላይ፤ ንጉሥ ቴዎድሮስም ከፊተኛው ሰልፍ ቁመው። ከኋለኛው ሰልፍ ብዙ ፈረሰኛ አዙረው ሰደዱበት ይሉና፣ ደብተራ ዘነብ ሲቀጥሉ፣ ከጦርነቱ በኋላ፣ የዘመን መለወጫ ዕለት፣ ኦሮሞ ሁሉ ከተት ብሎ ገባ (ለአፄ ቴዎድሮስ)። እንደ ንጉሡም ትንቢት ሆነ፤ ሠራዊታቸው ሁሉ ተደነቀ። ባንድ ሰደቃ አበሉት። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ፣ ቴዎድሮስ የሚወዷት ሴት፣ ወይዘሮ (አንዳንዶች አቴጌ ይሏታል) የተመኙ የየጁ ኦሮሞ ነበርች። እንግዲህ አቴጌ ተዋቡችንም ሳንዘነጋ ነው። ሀይሉ የሚባለው አንደኛው ልጃቸው የተወለደው ከሌላ የኦሮሞ ሴት ነበር።

**ቁጥር 22፤** አፄ ቴዎድሮስ በራሳቸው አነሳሽነት ባለሙያተኞች እንዲያመጣላቸው ደብዳቤ የላኩለት ሰው ሳሙኤል ጎባት ይባላል። አቡን ነበር። በደብዳቤያቸው፤ ቄሶች እንደማይፈልጉ ገልፀው፤ "እሳት የሚተፋ፣ ለርሻ የሚሆን ተሽከርካሪ መኖሩን ሰምቻለሁ"፤ በማለት ጥበበኞች እንደሚፈልጉ ገልጠውለታል። ሆኖም ሳሙኤል ጎባት ግን በጥበበኞች ፋንታ ኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰባኪ ሚሲዮናውያንን በመቀስቀስ፣ ወንጌላቸውን በኢትዮጵያ የሚሰብኩበት ጊዜ ደርሷል በማለት ሚሲዮናውያኑ ጥበበኛ መስለው እንዲገቡ በመምከር ወደ ኢትዮጵያ እንዲሚጡ አደርጓል። ንጉሡ የፈለጉትን አላገኙም።

**ቁጥር 23፤** እንግሊዛዊ ቆንስል ፕላውደን (በቴዎድሮስ አጠራር፣ ቡላዲን) የንጉሡ አማካሪ ነበር። ፕላውደን መጀመሪያ ከራስ አሊ ጋራ ስምምነት ፈርሞ ነበር። ፕላውደን፣ ከራስ አሊ ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት የእንግሊዝ ባንዴራ ጎንደር ላይ እንዲውለበለብ ሲጠይቅ፣ ቴዎድሮስ በቁጣ ገንፍለው፣ "ምን፣ እኔ እንደ ተራው ሎሌ አሊ መሰልኩህ እንደዚህ በድፍረት የምታናግረኝ፣ እንደ አሊ ያለ ከሀዲ አሽከርስ ከውጭ መንግስት ጋር ውል መግባት ይችላል?" በማለት ባንዴራው እንዳይውለበለብ ከልከለዋል።

**ቁጥር 24፤** በዘመኑ የነበሩ ባላባቶችና ህዝቡ ከቴዎድሮስ ምኞትና አሠራር ጋር የሚጣጣሙ አልነበሩም። ይህንንም ቴዎድሮስ ከራሳም ጋራ በተለዋወጡት አነጋገር፣ በእንደቢታቸው ይገለፃል። ንጉሰ ነገሥቱ እንዲህ ብለዋል። "በሰላም እንዲኖሩ



የማዘጋጁ፣ እንደሠለጠነው አለም ወደሥልጣኔ እንዲሄዱ ታገልኩ፤ በሥርአት እንዲኖሩ፣ ልጆቻቸው ተስፋ እንዲኖራቸው ምከርኩ። ነገር ግን ከፉ ናቸው።" ብለዋል። የራሳቸውን ሰዎች ነው። በተጨማሪ፣ ከመልከተኛው ከራሳም ጋራ ሲነጋገሩ፣ የሸፈቱ ሰዎችን ምን ሊድረጋቸው ብለው ሲጠይቁት፣ ራሳም የህንድን ምሳሌ በመጥቀስ፣ ንግሥቷ በመላው ህንድ ላመፁት በሙሉ ምህረት አድርጋለች በማለት ሲነግራቸው፣ ቴዎድሮስም ፈገግ በማለት መልሰው፣ "የአቢሲኒያ ሰዎች እንደሌሎች ሰዎች ናቸው ብለህ ታስባለህ? ከፉ ናቸው፣ ምክርም አይሰሙም። እኔ ትክክል እንደሆንኩ ለማሳየት፣ ለሁሉም ሸፍቶች የምህረት አዋጅ አሁን አስነግራለሁ። ግን ታያለህ፤ አንዱም እንኳን ቢሆን አዋጁን አይቀበሉም።" አሉ። ከዛ በኋላ አዋጁ ሲነገር እንዲሰማ አንደኛውን አስተርጓሚዬን እንድልክ ጠየቁኝ። አዋጁም ተነገረ፤ የኔ አስተርጓሚም ምስክር ነበር። ይላል ራሳም።

**ቁጥር 25፤** አፄ ቴዎድሮስ የህዝቡን ባህሪ በደንብ የተገነዘቡ መሆኑን የሚያስረዳ ከራሳም ጋር ያደረጉት ልውውጥ አለ። ራሳም በአስተርጓሚው በዳሰታ አማካኝነት አንዳንዴ በአረብኛ አንዳንዴም በትግርኛ፣ ንጉሡ የተለያዩ ርእሶችን አንስተው ስናወራ ይላል፡ ቴዎድሮስ ስለ ግብር አሠራር ጠየቁኝ ይላል። እሱም በሀገሩ እንዴት የገቢ ግብር እንደሚሰበሰብ ስነግራቸው፣ "ያገሬ ሰዎች በገንዘባቸው ነግደው ለኔ ግብር ከሚከፍሉ መሬት ውስጥ ቢቀብሩት ይመርጣሉ።" አሉ። ከዚያም፣ ፈረስና የወንድ አገልጋይ ያለው ሰው ግብር እንደሚከፍል ስነግራቸው፣ "ሚስተር ራሳም፣ ያገሬን ሰዎች አታውቃቸውም፤ ፈረሶቻቸውን፣ በቅሎቻቸውን ሌላም የቤት እንስሳ ላይ ቀረጥ ባደርግ፣ አንድም ሰው በፈረስም በበቅሎ አይሄድም፤ እያንዳንዱ ሰው ደግሞ የራሱ አገልጋይ ይሆን ነበር።" ብለዋል። በዚያን ጊዜ አፄ ቴዎድሮስ እንደዚህ አይነት ግብሮችን ህዝቡ ላይ ለመጣል ባይጨክኑም፣ ከሳቸው በኋላ እስከ ጣልያን ሁለተኛው ወረራ ድረስ፣ የበጌምድር ሰዎችና ሌሎችም ከመጠን በላይ የሆነ ግብር፣ በቤት፣ በከብትና በዶሮ ሳይቀር ይገብሩ ነበር።

**ቁጥር 26፤** አፄ ቴዎድሮስ በጋፋት የተሠሩትን ማቅለጫዎቹን ሲጎበኙ፣ ሄንሪ ዱፍተን በተቀት ያርዶች ከኋላቸው ይከተል ነበር። ማቅለጫዎችን ደግፎ ለመያዝ በቀርከሀ የተሠራ ሥራ ነበር። ያጋጠመውን ሲገልፅ እንዲህ ይላል። "አዳልጦኝ አንደኛው ቀርከሃ ላይ ስወድቅ፣ የቀርከሃው ሌላኛው ጫፍ ንጉሡን ጭንቅላታቸውን ከጀርባቸው በኩል ይመታቸዋል። ይህን ሁኔታ ከቴዎድሮስ ውጭ ሌላ ሰው ሳላስተዋለም ነበር። ቴዎድሮስም በዝምታ ዞር ብለው ላንዳፍታ አዩኝ። ሁኔታው እንዴት እንደተፈጠረ ንጉሡ የተረዱ ይመስለኛል። አመለካከታቸው ደግሞ የተለየና ርጋ የሆነ አጭር ዕይታ ነበር። እኔም ስተረጉመው ወዲያውኑ ይቅርታ እንደተደረገልኝ አድርጌ ነው። በጣም የከፋኝ ነገር ግን ሰዎች በብዛት ሲተራመሱ ስለነበር እጠገባቸው ቀርቤ ይቅርታ መጠየቅ ስላልቻልኩ ነበር፤ እሳቸው ግን ጉዳዩን በቅላላ ረስተውታል።" ይላል።

**ቁጥር 27፤** ቴዎድሮስ፣ ቱርኮችንም ሆነ አሽከሮቻቸውን ግብፆችን እየተዋጉ ነው ምዕራቡን የኢትዮጵያ ደንበር ያስጠበቁት:: ለቴዎድሮስ፣ ግብፅና ቱርክ ልዩነት አልነበረውም:: ቴዎድሮስ፣ በደብዳቤዎቻቸውም ቱርክ አንጂ ግብፅ የሚል ቃል አይጠቀሙም:: በዚያን ጊዜ በርግጥ ግብፅ ራሷ በቱርኮች ሥር ነበረች:: ለራሳም ሲነግሩት፤ በልጅነታቸው የምዕራቡን ግዛት ከቱርኮች ነፃ አውጠተው እስከ ሱዳን ድረስ እንዳባረሯቸው፣ "ፈሪዎች! በመድፋቸው ጀርባ ባይደበቁ ኖሮ ድል ሊደርጋቸው ነበር::" በማለት ይገልጣሉ:: ይህ ቦታ ደበርኪ ይባላል:: በሌላ ዘገባ፣ ቴዎድሮስ የመድፍን ጥቅም የተገነዘቡት በዚህ ጊዜ ነበር:: ሆኖም ሱዳንን የወረሩት ግብፆች፣ አመቺ ጊዜ እየጠበቁ፣ ምዕራባዊ የኢትዮጵያን ደንበር እየጣሱ ቦታዎችን ይዘዋል:: ይህም፣ ከቴዎድሮስ በፊት፣ ራሳቸው ቴዎድሮስ የተዋጉባቸው ታላቅ ወንድማቸው ደጃዝማች ከንፉ ዕድሜ ልካቸውን ይዋጉት የነበረው ከቱርክ ከሚላኩ ግብፆች ጋር ነበር:: ለዚህ ነው፣ "የከንፉ ጎራዴ ብረት የነበረ፣ እየቀላ ሄደ ቱርክ እየመሰለ" የተባለላቸው:: በዚህ ጀግንነታቸው፣ ደጃዝማች ከንፉ በግብፅ አገር ታዋቂ ነበሩ:: ሆኖም ከንፉ ሲሞቱ በሁለቱ ልጆቻቸው መሀከል ውጊያ ሲካሄድ፣ ግብፆች አጋጣሚውን ጠብቀው ሲሰፉ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ፣ ደጃዝማች ካሳ ከወይዘሮ መነን ከልጃቸው ከራስ አሊ ጋር በሚዋጉበት ጊዜ መተማ ድረስ ዘልቀው ቦታ ይዘው ነበር:: ነገር ግን፣ ደጃዝማች ካሳ፣ ራስ አሊን ድል ከመቱ በኋላ ተመልሰው፣ ግብፆችን ከመተማ አንዳስወጡ ተዘግቧል:: አፄ ቴዎድሮስ በምዕራቡ ደንበር፣ አይደለም መተማ፣ ቱከሪርም የኢትዮጵያ ነው የሚሉት:: በዚያን ጊዜ፣ ግብፅ የኢትዮጵያ ዋና የውጭ ጠላት ነበረች:: ይህም በተለይ ቱርኮቹ እየተዳከሙ፣ ግብፆቹ ራሳቸውን ባጠናከሩበት ጊዜ ነበር:: ከግብፆች ጋር የነበረው ጦርነት በቴዎድሮስ አላቆመም:: በአፄ ዮሐንስ ጊዜም፣ ራስ አሉላ አባ ነጋ ጎራዴያቸውን ያሰሉበት ታሪክ ነው::

**ቁጥር 28፤** ቆንስላው የተገደለው በቴዎድሮስ ወንድም ልጅ በጋረድ ከንፉ ሀይሉ ሰዎች ነበር:: ቴዎድሮስ በተሰማቸው መሪር ሀዘን የቆንስላውን ገዳዮች አይቀጡ ቅጣት ነው የቀጡት:: ይህም በጎንደር ደባርቅ በሚባል ቦታ ነበር:: "የተሰለፈውን በሙሉ ከቤት በስተቀር አንድ ሳይቀር..." ቀጣሁ የሚሉት አባባል አለ:: ሆኖም በዚህ ውጊያ ሌላው እንግሊዛዊ ወዳጃቸው፣ ሲቀ መኳስ ቤል፣ ቴዎድሮስን መትቶ ለመጣልና ጦርነቱን ለማሸነፍ የወሰነው፣ የወንድማቸው ልጅ፣ ጋረድ ከንፉ ወደ ቴዎድሮስ ሲገሰግስ አይቶ በሽጉጥ ተኩሶ ሲገድለው፣ የጋረድ ወንድም ጀን ቤልን ይገድላል:: ጆን ቤል፣ ንጉሡን ቴዎድሮስን ለመከላከል በሰውነቱ ሲከልል ነው የተገደለው:: ቴዎድሮስ ለፕላውደን ላደረጉት እንክብካቤ፣ ከንግሥት ቪክቶሪያ የሽጉጥ ስጦታ ተልኳላቸዋል:: ጋረድ ሲሞት፣ የቴዎድሮስን ዝምድና ለመጥቀስ የተገጠም ግጥም ይህ ነበር፣ "ጋረድ ሞተ ተቀበረ፤ ያንተ ወንድም ነውና እንጂራው ነበረ::"

**ቁጥር 29፤** አፄ ቴዎድሮስ በተፈጥሯቸው ፈጠራም የሚወዱ ብቻ ሳይሆን የሚሞክሩ ነበሩ:: ከአውሮፓውያኑ ጋር ሲወያዩ፣ የመንሳፈፍ ሁኔታን አንስተው፣ አንድ ነገር



ሁሉም ባለውና በሌለው ውሃ ላይ እኩል ይንሳፈፋል ወይ ብለው በመጠየቃቸው ኬሎች ተገርመዋል:: ይህንንም ጠይቀው፣ ጣና ሀይቅ ላይ፣ መንኮራኩር ያለበት ጀልባ አስገተው ለመቅዘፍ ሞክረው፣ ጀልባው ትንሽ እንደሄደ ሰጠመ:: እንደ ሀሳባቸው የሜካኒካል ሀይል ለማቋቋም ነበር:: ከዚያ በኋላ ይህን ሀሳብ ርግፍ አድርገው ትተውታል::

ገና በልጅነታቸው፣ ጣቁሳ በተባለ ቦታ፣ ከራስ አሊ ሰዎች ጋር ሲዋጉ ሲሰላለፉ፣ ደጃች ካሳ፣ እንጨት አስፈልፍለው፤ በላዩ ላይ ብረት ጠምጥመው፤ በውስጡ ባሩድ (የብረት አፋር) አስገብተው ካሸጉ በኋላ፣ እንደገናም ባሩድ በሸክላ በሸክላ እያደረጉ የጠላት ጦር የሚሰፍርበት ቦታ ከቀበሩ በኋላ፣ ከረጅም ቀርከሃ ጋር እያያዘው፣ የተከሰውን ወስጡን ባሩድ ሞልተው፣ ውስጥ ለውስጥ ምሽጋቸው ድረስ አስመጥተው ይጠባበቁ ነበር:: ጠላት ካምፕ ላይ ሲሰፍር ከምሽጋቸው ሳይወጡ ለመለኮስና ለማፈንዳት ነው:: ነገር ግን ከደጃች ካሳ ወገን አንድ ሰው ተይዞ ሲያሰፈራሩት ሚስጥሩን አወጣባቸው:: ሚስጥራቸው ስለወጣ በጣም ተናደው ከራስ አሊ ሰዎች ጋር እርቅ አደረጉ:: ሌላ መረጃ ካልመጣ በስተቀር፣ ደጃች ካሳ፣ የመጀመሪያውን የአቢሲኒያ ፈንጅ ነበር የሰሩት:: ይህን ታሪክ ደብተራ ዘነብ ሲዘግቡት፣ ራሳቸው ንጉሡ ይህንኑ አንስተው ለራሳም አጫውተውታል::

በሸፍትነታቸው ዘመን ደግሞ፣ ገባሮቻቸው ሻንቅሎቹ ማር ሲያመጡላቸው፣ "የማሩን ወለላ አቅልጠው ከጣሩ በኋላ፣ በፋጋ በፋጋ (ከቅል የተሠራ መጠጫ) አድርገው ምድር ቆፍረው እንዲቀዝቀዝ መሬቱ ውስጥ ቀበሩት:: ከዚያም በአዳራሽ ሰዉን ጠርተው፣ ለወታደርና ለሽማግሌ አንድ ፋጋ ለሁለት፣ ለልጅ ለልጁ ደግሞ አንድ ፋጋ ለሶስት ሰጡ:: ወታደሮችም በጠዝኑ ጊዜ በካሳ ጥበብ በጣም ተደነቁ::" ይላሉ ደብተራ ዘነብ:: ታዲያ ይህ ሁሉ ችሎታም ነበር መወደድና አድናቆትን ያጌጸመረላቸው::

አፄ ቴዎድሮስ፣ በዘመኑ ከሚገባው በላይ ብዙ ዕውቀትም ነበራቸው:: ቀልደኛም እንደሆኑ የታየበት አንድ ሁኔታ፣ በጋፋት፣ ራሳም ላይ ያደረጉት ነገር አለ:: ለራሳም ስለ ግሪክ ፈላስፋ ዲዮጀነስና(በአማርኛ ፅሁፍ፣ ዲዮጋን) ስለ ገንዳው አንስተው አጫወቱትና፣ መልሰውም ፈላስፋው፣ እብድ ነው ወይስ ራሱን ወዳድ ነው ብለህ ታስባለህ ብለው ጠየቁት:: ራሳም ሲቀጥልም፣ ንጉሡ እኔ ከማውቀው በላይ ስለ አውሮፓ ታሪክ አጫወቱኝና፣ የንግሥት ሳባና የንጉሥ ሰለሞን ትውልድ አለኝ ብለው ሲነግሩኝ፣ በዚህ ነገር ላይ እንዲያብራሩልኝ ስጠይቅ፣ ንጉሡ ግን በመቀጠል፣ እንዴት አንድ የአቢሲኒያ ልዕልት ታላቁ እስክንድርን እንደጎበኘቻውና በቆይታዋም ከእስክንድር ወንድ ልጅ እንደወለደቻና ልጁም ሲያድግ የእለምን ግማሹን እንደገዛ ነገሩኝ:: ከዛም፣ በአቢሲኒያ ታሪክ ታላቁ እስክንድር በክብር የሚታይ ሰው ነው፤ ምክንያቱም በህይወት እያለ መንግሥተ ሰማይ ደርሶ የተመለሰ ሰው ስለሆነ በማለት ግራ ሲጋባ አይተው ታሪኩን ለማረጋገጥ፣ ከንቲባ ሀይሉን ጠርተው ከመፅሐፉ እንዲያነቡልኝ አዘዙ:: ከንቲባ ሀይሉ ይህን መፅሐፍ (ዜና እስክንድር) እንደ መፅሐፍ ቅዱስ ነው የሚያምኑትና፣ በሳሙኤል አስተርጓሚነት ተነበበልኝ፣ ወደ ሰላሳ የሚሆኑ

ስዕሎችም ነበሩበት ይላል። ባጭሩ ከንግሥት ሄሌና የተወለደው ሕፃኑ አሌክሳንደር መንግሥተ ሰማይ ደርሶ እንደተመለሰ ነው የሚያስረዳው። ንጉሡም፣ ታሪኩን እንዴት እንዳገኙሁት ሲጠይቁኝ፣ እኔም ስመልስ፣ አሌክሳንደር ወደ ምድር መመለሱ ምኝ ነው፣ እኔ ብሆን አልመለሰም አልኩኝ። ይህ አባባል እንደተተረጎመላቸው፣ ንጉሡ ከተቀመጡበት ወንበር ሊፈነገሉ ትንሽ እስኪቀራቸው ድረስ በሳቅ ፈነዱ። ከዛም፣ "እኔ በእንደዚህ አይነቱ ተራ ነገር የማምን ይመስልሃል?" ብለው ጠየቁኝ። በዚህ ጉዳይ ከልብ የሚያምኑት ከንቲባ ሀይሉ ግን ደንግጠው ድምፅ አልባ ነበሩ። ከንቲባ ሀይሉ፣ ከዚህ በፊት የጎንደር ከተማ ከንቲባ ነበሩ፤ ሆኖም እነ ራስ አሊ የሚያደርጉትን ነገር በቅርብ ስለሚያዩና ክርስቲያንነታቸው የማስመሰያ መሆኑን ስለተረዱ፣ ሰዎችን በጣም ይጠሉ ነበር። ያለዕድል ሆኖ፣ አንዲት ከንጉሡ ቤት የተባረረች ሴት ሠራተኛን ከንጉሡ ፈቃድ ውጭ አስጠግተሃል ተብለው ተከሰው ከቴዎድሮስ ጋር ተጣልተው፣ ንጉሡ መቅደላ አስረዋቸው ነበር። ሌላ የሚጠቀስ ነገር ቢኖር፣ አፄ ቴዎድሮስ ጥንቆላና አስማት ስለማይወዱ፣ ከንቲባ ሀይሉ በዚህ ይታሙም ስለነበር ነው። መቅደላ ላይ፣ ቴዎድሮስ ራሳቸው ከፈቷቸው ሰዎች ከንቲባ ሀይሉ አንድ ነበሩ። ከንቲባ ሀይሉ፣ ቴዎድሮስን፣ ከአስራ አራት አመት በኃላ አትኖርም ብለው ፊት ለፊት ነግረዋቸው ነበር ይባላል። እንደተባለውም ንጉሡ በነገሡ በአስራ አራተኛው አመት ነው መቅደላ ላይ ራሳቸውን ያጠፉት።

**ቁጥር 30፣** አፄ ቴዎድሮስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመዝመት የነበራቸው ሀሳብ በወታደሮቻቸውም የታወቀ ነበር። ወታደሮቻቸው ካደረጓቸው ከታወቁ ሁለት ጉርምርታዎች አንዱ በዚሁ በኢየሩሳሌም የተነሳ ነበር። ንጉሡ ወደ ሸዋ በዘመቱ ጊዜ፣ ከደብረብረሃን ወደ እንኮበር ሲወርዱ ከባድ የጉም ጨለማ ነበር፤ እሳቸውም ራስ እንግዳን ለቀለብ ወደ ምስራቅ ወደ አውራምባ ሲልኳቸው፣ ከንጉሡ ጋር የቀረው ወታደር፣ እነዚህን አስቀድሞ የሰደደው፣ እኛን ኢየሩሳሌም ወስዶ ሊያስፈጀን ነው ብሎ አንጎራጎረ። ሁለት ወታደሮች አፋፍ ላይ ሆነው፣ ለዚህ ንጉሥ ውሀ የቀዳ፣ እንጨት የሰበረ፣ የተከተለውም ውጉዝ ይሁን በማለት ውግዘቱ ከአቡነ ሰላማ (በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ከፍተኛ የክህነት ሥልጣን) ከአቡነ ሰላማ የመጣ ነው በማለት ለፈፉ። አጨኔውና አቡኑ ግን የኛ ቃል አየደለም አሉ። ንጉሡ ተበሳጭተው የሙቱትና በጥይት የሳቱት ወታደር ነበር፤ ሆኖም በአቡኑ ሰላማና በአጨኔው ግልግል ቴዎድሮስ በረድ ቢሉም፣ በነጋታው፣ እነዚህ ሰዎች ግዝቱን ሲደግሙ ያዬ ሰው ሄዶ ሸምቆ ይዟቸው መጣ፤ ሲጣራ ሁለቱም ሰዎቹ ቅስና የሌላቸው ወታደሮች ሆነው ተገኙ። ቴዎድሮስም በዙሪያ ያሉትን፣ ንጉሥ ላይ ያሴረ ሰው ምን ይሁን ብለው ሲጠይቁ፣ ሌሎቹ ሞት ይገባቸዋል ብለው ፈረዱ። ከወታደሮች አርባ ሰምንቱ በቦታው ተገደሉ፣ ቁራ መስከ ይባላል። ሁለቱ ገዛቶች ግን ከዳሞት የመጡ ስለነበር፣ ጎጃም ተወስደው ተሰቀሉ። እንግዲህ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ነው የአብዛኞቹ ሰዎች ሞት የተፈጠረው። እንደ ስታንሊም አስተያየት፣ በማንኛውም በሠለጠነው አለም፣ አገርና ንጉሥን የሚከዳ ከፍተኛ ቅጣት ነበር የሚደርስበት ።



የማንጎራጎር ነገር ከተነሳ፣ እቴጌ ተዋበች ሲሞቱ፣ አፄ ቴዎድሮስ አስከሬኑን ይዤ ልሂድ ብለው ሲነሱ፣ ወታደሩ በውሃ ሲያሰበላን ነው ብሎ ስላንጎራጎረ፣ ቴዎድሮስ የባለቤታቸውን አስከሬን ለሁለት ወራት በየዘመቻው እየያዙ ሲንከራተቱ ከርመው ጣሸን ወስደው ቀበሯቸው። የአፄ ቴዎድሮስ እህት፣ ወይዘሮ ወለተ ወርቅ ይባላሉ። (አፄ ቴዎድሮስ ለፈረንሳዩ መሴ ሌዣን ድረዋቸው ነበር) ሲሞቱ፣ ንጉሡ ወደ መቅደላ በመጓዝ ላይ ስለነበሩ፣ አስከሬኑ እንዲሁ መንገድ ከርሞ በመጨረሻም መቅደላ ደርሶ ተቀብሯል። በዚያን ጊዜ፣ ኢትዮጵያውያን አስከሬን በሰም አድርጎ የመገነዝ ጥበቡ ነበራቸው፤ ስለዚህ ለብዙ ቀናት ሳይቀበር መቆየት ይችላል። ሌላኛዋ የአፄ ቴዎድሮ እሀት፣ ወይዘሮ የሴፋ፣ የትግራዩን ደጃማዝች ሰባጋዲስን አግብተው ነበር። ሌላ ከፍል እንደተጠቀሰው ፣ ደጃች ሰባጋዲስ ከራስ ማርዬ ጋር ሲዋጉ ተይዘው በአዛዥ አሸቴ ትዛዝ ተገድለዋል።

**ቁጥር 31፣** ስለ ቴዎድሮስ ጭካኔ አውሮፓውያን የሚያሰወሩትን ንጉሡ በደንብ ያውቁ ነበር። ለዚህም ምሳሌ፣ ራሳም እንዲህ ሲል የሚገልፀው ሁኔታ አለ። ንጉሡ፣ አንድ የሀያ አመት ወጣት ወንጀለኛ በሰንሰለት እንደታሰረ ወደኔ ላኩልኝ። ወጣቱ ለመዝረፍ ሲል ወላጅ እናቱን የገደለ ነበር። ወንጀለኛው ራሱ የሚናዘዘውን ነገር ራሴ ከአፉ እንድሰማና ንጉሡ ከምን አይነት ሰዎች ጋር እንደሚታገሉ እንድረዳ ነበር የላኩት። ቴዎድሮስም ሲፅፉ፣ "ይህን ሰው በህጉ መሠረት ብቀጣው፣ ላንተ ያስረከብኩህ አንዳንድ አውሮፓውያን ነብሰ ገዳይ ይሉኛል።" የሚል ነበር። ይህ እናቱን ገዳይ፣ በአቢሲኒያ ህግ መሠረት ቢቀጣ፣ ሰውነቱ ተቆራርጦ ለቀብርም አይበቃም ነበር። ነገር ግን፣ ንጉሡ በጥይት ተገድሎ ወዲያው እንዲቀበር አዘዙ። ራሳም ሲቀጥል፣ ቴዎድሮስ ምንም ጨካኝ ቢሆኑም፣ የሳቸው ፍርድ ከፍትህ ነገሥቱ ወይም ከአቢሲኒያ ህግ ቀለል ያለ ነበር ይላል። ምንም እንኳን ሰዎችን በብዛት ቢየጠቁም፣ በጭካኔ ከመጣ ግን፣ ቴዎድሮስ ያደረጉት፣ ደጃች ውቤና ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ካደረጉት ከግማሹም አይደርሰም። ከቴዎድሮስ በፊት፣ ለቀላል ጥፋት እንኳን ሰዎች አይናቸው ይጎለጎል፣ ምላሳቸውም ይቆረጥና እግራቸውም ይቆረጥ ነበር። ይህ ደግሞ በሰውነት ላይ ከሚደርሰው ሰቆቃ በተጨማሪ ነው። ደብተራ ዘነብ የሚጠቅሱት አንድ ጎጂ የተባለ ሰው፣ የሰዎችን አይን እስጎልጉሎ በእንቅብ አሰምልቶ፣ አንድ ሰው ብቻ አይኑ እንዲተርፍ ካደረገ በኋላ አይናቸው የተጎለጎሉትን ሰዎች እየመራ እንዲሄድ ያስደርግ ነበር ይላሉ። ራሳም፣ በዚሁ ጉዳይ ላይ ሲደመደም፣ በሀገሪቱ ዳር እስከ ዳር ቢዞሩ እንደዚህ አይነት አይንና ምላሰ የሚጎለጉል በቴዎድሮስ የተደረገ አንድም ቢሆን አይገኝም ይላል። በሌላ ዘገባ፣ በሸዋም ቢሆን ሰውነትን በመቆራረጥ ቅጣት ይፈፀም ነበር፤ ቴዎድሮስ ሸዋን ካስገበሩ በኋላ ግን ይህን አይነት ተግባር በአዋጅ አስቁመውታል።

**ቁጥር 32፣** ሎርድ ጆን ራሰል በዘመኑ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረና፣ በመሀሉም ከሥልጣን በመውረድ በተተካው ጠቅላይ ሚኒስትር በፓልመርስተን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ ተሹሞ ነበር። ፓልመርስተን ሲሞት ተመልሶ ጠቅላይ

ሚኒስትርነቱን ይዟል፡፡ የእንግሊዝ መንግሥት ባደረገው የአቋም ለውጥ ምክንያት፣ የግብፅ ቤተክርስቲያናት በኢየሩሳሌም የነበሩትን የኢትዮጵያን ገዳማት በጉልበት ወሰዱ፡፡ ይህ ዜናም የቴዎድሮስ ጆሮ ደረሰ፡፡ በፊት የነበረው የእንግሊዝ ቆንስል፣ ጀምስ ፊን ገዳማቱንና ኢትዮጵያውያኑን ከጥቃት ይጠብቅ ነበር፤ ሆኖም አሁን የተካው ኖወል ሙር ግን፣ ከላይ አለቆቹ ካልረዱኝ በስተቀር ምንም አቅም የለኝም ብሎ ነው የተወው፡፡ ከእንግሊዝ መንግሥት በኩል ምንም አይነት ርዳታ ወይም ጣልቃ ገብነት አልተደረገም፡፡ ይህ የሆነው፣ በዚያን ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት የሚፎካከረው ከሩስያ ጋር ስለነበር፣ የሩስያን መስፋፋት ለማስቆም ከሩስያ ጠላቶች፣ ከቱርኮች ጋር ማበሩን ፖሊሲ ስላደረገ ነው፡፡ ግብፅም ቢሆን የቱርክ ቅጥያ ማለት ስለነበር፣ በቴዎድሮስና በአቢሲኒያ ኪሳራ፣ እንግሊዞች ግብፆቹን አልተጫኑም፡፡ ይህ የእንግሊዝ ባህሪ፣ በአፄ ዮሐንስ ጊዜም ቢሆን፣ በወቅቱ ጉልበት ነበረው ለተባለው ለጣልያን መንግሥት በማድላት፣ እንግሊዞቹ ምፅዋ በጣልያኖች እጅ እንድትወድቅ ነው ያደረጉት፡፡ እንግሊዞቹ፣ ጣልያኖች ምፅዋን እንዲይዙ ጋብዘዋል የሚሉ ዘገባዎችም አሉ፡፡

***ቀጥር 33*፣** በዚህ ምክንያት በኢየሩሳሌም ገዳማት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ቤትየለሽ ሆነው ተሰደው እንደነበር፤ በስደታቸው ጊዜም የአርመን ቤተክርስቲያን መነኮሳት በቀለብ ኢትዮጵያውያንን ይረዱ ነበር፡፡ ሆኖም ለመሰደዳቸው ምክንያት ዋነኞዎቹ ራሳቸው አርመኖች ነበሩ፡፡ ቴዎድሮስን ለማባበል እነዚህ መነኮሳት ወደቦታቸው እንዲመለሱ፣ በብሪታንያና በአርመኖች መካከል ስምምነት ተደርጎ ነበር፡፡ ቴዎድሮስ ኢየሩሳሌም ድረስ የሚፎከሩበት አንዱ ምክንያትም ይህ ሊሆን ይችላል፡፡

***ቀጥር 34*፣** በጥቅምት 25 ለምሳሌ የባርካ ነዋሪዎች(በግብፅ ስር የሚተዳደሩ) በጎሰን በመውረር ክርስቲያኖችን በማጥቃት ብዙ ሴቶችና ወንዶች ከገደሉ በኋላ፣ 120 ሴትና ወንዶች ልጆችን በማጋዝ ለባርነት እንደዳረጓቸውና ከብቶቻቸውንም እንደነዱ ተዘግቧል፡፡ ይህ ደግሞ በተደጋጋሚ ይደረጉ ከነበሩ ወረራዎች አንዱ ነው፡፡ የግብፁ ገዥ ይህንን ነገር በቀላሉ ማስቆም ይችል ነበር፤ በተለይም የባሪያ ንግድ በዚያን ጊዜ እየተከለከለ ስለነበር ሰዎችን ለባርነት መጥለፉን ማስቆም ይችል ነበር፡፡

***ቀጥር 37*፣** የአፄ ናፖሊዮን ወይም የፈረንሳዮቹ ፍላጎት፣ አፄ ቴዎድሮስ በካቶሊክ እምነት ተከታዮች ላይ ጫና እንዳይፈጥሩ ነው፡፡ ካቶሊኮቹ በዚያን ጊዜ ከሰሜኑ ደጃዝማች ንጉሤ ጋር በመተባበር ይሸርቡ ነበር፡፡ ሆኖም ቴዎድሮስ ባልታሰበና ባልተጠበቀ ፍጥነት በመገስገስ ደጃች ንጉሤን ድል አድርገው የካቶሊኮችን ሴራ አከሽፈዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፈረንሳይ ጀሰዊቶች፣ ማህደረቃል የሚባል የኢድዋ ተወላጅ ኢትዮጵያዊን ያለፍላጎቱ የካቶሊክ ስራ እንዲሰራላቸው ንጉሱን ጠይቀው፣ የፈረንሳይ ንጉስ ለፖለቲካ ሥራ ስለፈለገው፣ ቅር እያለው ወደነሱ እንዲመደብ ወስኖ ነበር፡፡ ማህደረቃል፣ የፈረንሳይ ቄሶች የፈለጉትን ነገር መስራት ስላልወደደ፣ ግብፅ ሲደርስ ይጠፋና ከሌላ፣ ለፌቨር ከሚባል ፈረንሳዊ፣ ጋር ይሆናል፡፡ ሆኖም፣ ለፌቨር



ማህደረቃልን፣ ወሰጡን ሳያስነብበው አንድ ሰነድ ላይ እንዲፈርም ይጠይቀዋል፡፡ ኢትዮጵያዊው ግን አልፈርምም ካለ በኋላ፣ ከሌላ ሰው ጋር ሆኖ ሰነዱን ሲያነብ፣ ውሉ ላይ የተፃፈው ነገር፣ ማህደረ ቃል ወደ አገሩ አቢሲኒያ ሲመለስ፣ 500 የሚሆኑ አቢሲኒያኖችን መልምሎ ወደ በርበን እንዲሄዱ እንዲያደርግ ነበር፡፡ ማህደረቃል በመናደድና በመደናገጥ ለፈረንሳይ ቆንስል አመልክቶ ከለፌቨር ጋር የነበረው ግንኙነት እንዲቋረጥለት ተደርጓል፡፡ በኋላም ከነ ፍላድ ጋራ በመሆን ወደ አቢሲኒያ ተመልሶ በትውልደ ቦታው ኢድዋ ሆኖ ወንጌል ያስተምር ነበር፡፡ ከዛም አፄ ቴዎድሮስ ባስተርጓሚነት እንዲያገለግል ጠርተውት ለተወሰነ ጊዜ አብሯቸው ነበር፡፡ ማህደረቃል ወደ ትውልድ ቦታው የተመለሰው፣ አፄ ቴዎድሮስ ደጃማች ተድላ ጓሉን ካሸነፉ በኋላ ነው፡፡ ያን ጊዜም በቴዎድሮስ ስር ተሰልፈው ሲዋጉ የነበሩ የትግራይ ተወላጆች፣ ንጉሡ ካሁን በኋላ አልፈልጋችሁም ስላሉ ከማህደረቃል ጋር ወደ ትውልድ ቦታቸው ተመልሰዋል፡፡

መንዚንጀር ተባሮ ቢወጣም፣ በምፅዋ የፈረንሳይ ምክትል ቆንስል ሆኖ ይሰራ ነበር፡፡ በምፅዋ፣ ሁሉም ሰው በተለይም ቱርኮቹ፣ ለመጣ ለሄደው ሁሉ ቴዎድሮስ ክፉ ነው እያሉ ነበር የሚያወሩት፡፡ የሚገርመው ነገር፣ መንዚንጀር ግን፣ ራሳምን፣ የመሀመዳኑንን ወሬ አትስማ፤ አውሮፓውያኑ ቴዎድሮስን የሚገባቸውን ክብር ቢሰጧቸው ኖሮ ይህ ሁሉ አይፈጠርም ብሎታል፡፡ ንጉሡ በተፈጥሯቸው ክፉ አልነበሩም፡፡ ንጉሡ ለራሳም በፃፉት ደብዳቤም ይህንኑ የአውሮፓውያን ንቀትና ሴኮብ ይገልጣሉ፡፡

የአርቂቆው(አርጊጎ) ናይብም ቢሆን፣ ምንም እንኳን እንዴ በቴዎድሮስ ቢታሰርም፣ የንጉሡ ደጋፊ ነበር፡፡ ቴዎድሮስ በተፈጥሯቸው ደግና ሩህሩህ ሰው እንደሆኑ፣ ነገር ግን ሲወለዱ ጀምሮ ደም ከጠማቸው ሰዎች ጋር ስለሚታገሉ ነው ጨካኝ የሆኑት ብሏል፡፡ ሰውየው በመጨመርም፣ የአውሮፓውያኑ መታሰር የቴዎድሮስ ጥፋት አይደለም ነው የሚለው፡፡ በንጉሡ ግዛት ሲኖሩ እንደ ራሱ ዜጎች ነው የሚያያቸው፣ ታዲያ በግዛቱ እየኖሩ ለንጉሡ ጥላቻ የሚያሳዩ ከሆነ፣ እንደማንም ሰው መቀጣት አለባቸው ይላል፡፡ ናይቡ የታሠረው፣ በምፅዋው የቱርክ ገዢ ወደ ቴዎድሮስ ተልኮ፣ ቴዎድሮስ ግን ከጠበቀው በላይ እንዲዘገይ ሲያደርጉት፣ የምፅዋ ጊታዩ እንድዘገይ ፈቃድ አልሰጠኝም በማለቱ፣ ቴዎድሮስ ቡን ብለው እንዴት ቱርክ ጊታዩ ነው ትላለህ በማለት ነበር፡፡ ተደጋግሞ እንደሚታየው፣ ቴዎድሮስ ራሳቸው እንደወታደር በድንኳን እያደሩ፤ በባዶ እግራቸው እየሄዱ፤ ሥራም ለመስራት ብዙ ጊዜ በመሪነት ራሳቸው በጃቸው እየቆፈሩና እየተሸከሙ፤ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ቢኖሩም፣ የኢትዮጵያን ንጉሥ ነገሥትነታቸውን ዝቅ የሚያደርግ ወይም የሚያንጓጥጥ ሰው ከተገኘ ግን፣ ነጭ ሆነ የራሳቸው ዜጋ ከባድ ቅጣት ነበር የሚደርስበት፡፡ የሀገራቸው ሰዎች በውጭ ሰዎች ሲሰደቡ መስማት አይፈልጉም፡፡ ከባሻ ፈለቀ(ስፒዲ) ጋር ትልቁ የጥላቻ መንስኤ፣ የአቢሲኒያን ሰዎች አህያ ናቸው ማለቱን ስለሰሙ ነበር፡፡ እንደ ፕላውደን ዘገባ ቴዎድሮስ በሥልጣናቸው በጣም ይቀናሉ፡፡

***ቁጥር 38፤*** *ሚሲዮናዊው ስተርን፣ ከኢትዮጵያ ለመውጣት አሽከሮቹን አስከትሎ ሲሄድ ወገራ ላይ ከአፄ ቴዎድሮስ ካምፕ ይደርሳል። ሰላምታ ለመስጠት ጎራ ሲል ንጉሡ ወዴት እንደሚሄድ ጠየቁትና አብረው ያሉትን አሽከሮቹን ወዴት እየሄዱ ነው በማለት ሲመለከቱ፣ አንደኛው አሽከር ቤተሰቦቼን ላይ ነው ብሎ ሲመልስ ቴዎድሮስ እንዴት በድፍረት ይናገራል ብለው አሽከሮቹ እንዲደበደቡ ትዛዝ ይሰጣሉ። ይህንን ያየው ስተርን ጣቱን በጥርሱ ይነክሳል፤ ይህ ደግሞ በዘመኑ የመበቀል ምልክት ነበር፤ ይህን ያዩ ቴዎድሮስ እሱንም እንዲገረፍ ትዛዝ ሰጡ። ሰውየውም ታስሮ ተመለሰ። በጣም ከሚጠሏቸው ሰዎች አንዱ ስተርን ነበር። ቴዎድሮስ አቶ ኮከብ ነበር የሚሉት። ስተርን ማለት ስታር ነው። ስተርን በአንድ መፅሐፉ ቴዎድሮስን "የአራዊቶች ንጉሥ" በማለት መዝለፉን ደርሰውበታል። ራሳምን ሲነግሩት እኔን እንዲህ ብሎ የሰደበኝ ሰው፣ ቁመቱ ይችን ነው የምታክል በማለት እጃቸውን ከምድሩ አራት ጫማ የሚሆን ከፍ አድርገው ለራሳም ነግረውታል። በአስተርጓሚያቸው በአቶ ሳሙኤል ውትወታ፣ እጃቸውን ለአመል ያህል ትንሽ ከፍ እንዳደረጉ ተዘግቧል።*

***ቁጥር 40፤*** *አፄ ቴዎድሮስ ምኞታቸው፣ የአባቴን አገር በጉልበት ይዘዋል የሚሏቸውን ቱርኮችን ከምፅዋ ለማስለቀቅ ነበር። ለዚህም የአውሮፓውያኑን እርዳታ ይፈልጉ ነበር። ሆኖም እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ከቱርክ ጋር የተባበሩበት ጊዜ ነበር። ስለቱም ባንድነት በክሬሚያ፣ ሩሲያን ሲቃወሙ፣ አፄ ቴዎድሮስ ግራ እንደገባቸው ይጠቀሳል። ይህ ጦርነት፣ ቴዎድሮስ በጣም የሚከታተሉት ጉዳይ ነበር። የመጣው ሰው ሁሉ ስለ ክሬሚያ ጦርነት ይጠየቅ ነበር። ከሆርመዝ ራሳም ጋር ሲወያዩ፣ ቴዎድሮስ፣ ስለ አሜሪካ እርስ በርስ ጦርነት፣ በብሪታኒያና በአሻንቲዎች ስለነበረው ውጊያ አውርተው፣ በክሪሚያ ጦርነት የተሸነፈውን፣ የሩሲያን ዛር፣ ኒኮላስን "እንግሊዞቹ አልገደሉትም ወይ?" ብለው ጠይቀዋል። ቴዎድሮስ በዚያን ጊዜ በሄሚያ የሚባል አገር ስለነበረው አምባገነን ጨካኝ ገዥ በደንብ ያውቁ ነበር።*

***ቁጥር 42፤*** *ስለ አፄ ቴዎድሮስ ደግነት የውጭ ፀሀፊዎች የዘገቡትን መመልከት አስፈላጊም ይሆናል። ከነዚህ አንዱ ፕላውደን ሲሆን፣ ዱፈተን፣ ራሳም፣ ቫልድማየርም ቢሆን በተለያዩ ጊዜያት ያዩትን የሰውየውን ደግነት አስፈረዋል። ከጠዋቱ፣ ቴዎድሮስ፣ ወታደሮቻቸውንና የጦር መሳሪያዎችን እንጂ ለሌላው ንብረት ደንታ የነበራቸው አይመስልም። ከሚገባው በላይ ለጋሥ ነበሩ፣ የግብጋባነት ባህሪ አይታይባቸውም ነበር። ቴዎድሮስ፣ አውሮፓውያኑን መልሰው ሲያስሩ የተወረሰውን ብር በሳቸው በኩል ምንም ሳያጎድሉ እንዳለ መመለሳቸው ተዘግቧል። ቫልደማየር ሲገልፅ፣ ንጉሡ በመንገዳቸው የታረዘች ድሃ ሴት አግኝተው፣ ከፈረሳቸው ወርደው የለበሱትን የራሳቸውን ሸማ አውልቀው ሴትዮዋን ሲያለብሱ አይቷል። ወላጅ አልባ የነበሩ ህፃናትን ሰብስበው ከእራሳቸው ካዝና በሚወጣ ገንዘብ ያስተዳድሯቸው እንደነበር ይታወቃል። በውጊያ ላይ ከተማረኩ ሰዎች ስለ መድሃኔ አለም ተብሎ በምህረት የሚለቀቁ ቢበዙ ነው እንጂ አያንሱም ነበር። በርግጥ በሞት የሚቀጡ አሉ፣ በመጀመሪያው አካባቢ፣ በዘመኑ የነበረው ፍትሀ ነገሥት ተከፍቶ ነው ፍርድ*



*የሚሰጠው። ከተሸነፉ በኋላ፣ ደጃዝማች ብሩ ጎሹን ምህረት አድርገው በከብር በሠንጠፍ አስቀምጠው፣ አንተ ብትሆን እኔን የያዘከኝ ምን ታደርገኝ ነበር ብለው ቢጠይቁት፣ አገልዎ ነበር ብሎ መመለሱ የሚዘነጋ አይደለም። በዚያን ጊዜ፣ ሳይበቀሉ፣ እግዚአብሔር በጠላቶቼ እጅ አይጥለኝም ነበር ያሉት።*

*ስለ ደጃች ብሩ ጎሹ በጥቂቱ፣ ብሩ ጎሹ የደጃዝማች ጎሹ ዘውዴ ልጅ ነው። ከአባቱ ጋር ተዋግቶ ጎጃምን ጠቅለል አድርጎ ይዞ ነበር። ያደገው በራስ አሊ ቤተ መንግሥትም ስለነበር ኩራተኛና ትቢተኛ ነው ይባላል። እንደ ቴዎድሮስ ሁሉ ሊላዋን የራስ አሊን ልጅ የውብዳርን በማግባት አማችም ነበር። ያም ሆኖ አፄ ቴዎድሮስ በአባቱ በደጃች ጎሹ ቤት ስለኖሩ በአክብሮት ነበር የሚይዙት። ተንኮሉ ስላስቸገራቸው፣ ዕድሜዬ ይፍታህ ብለው መቅደላ ልከውት፣ ቴዎድሮስ ሲሞቱ ነው ከመቅደላ የተለቀቀው። የተማረኩ ሰዎችን ምህረት በማድረግ፣ እንደጠላት ሳይሆን እንደ ወዳጅና ጓደኛ ያያሉ ብሎ ፕላውደን ለዘገበው መረጃ እንደዚህ አይነት ብዙ ምሳሌዎች አሉ።*

***ቁጥር 43፤*** *የወታደራዊ ማዕረግ ተዋረዱን የጀመሩት ቴዎድሮስ ናቸው። ሻምበል፣ ባሻ፣ የመቶ አለቃ ወዘተርፈ። ለንጉሣዊ በአላት፣ ራሶችና ሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣኖች፣ ከሀር የተሠራ ሸሚዝ ይለብሱ ነበር። የንጉሡ ወታደሮች የሚለብሱት ቀይ ሸሚዝ ቢጤም ነበር። በመቅደላ በአሮጌ ውጊያ ጊዜ የታየ ነበር። ናፒየር፣ በአሮጌ ቁልቁል ለውጊያ የወረዱት የአቢሲኒያ ተዋጊዎች በለበሱት ቀይ ልብስ ምክንያት፣ በርቀት ላየ ሰው የእንግሊዝ ሠራዊት ይመስላሉ ብሏል።*

***ቁጥር 44፤*** *አፄ ቴዎድሮስ ለሌሎች አውሮፓውያን ሲናገሩ፣ ባሻ ፈለቀ ተመልሶ ምፅዋ ሲደርስ ኢትዮጵያውያንን "እህያ" ብሎ ተሳድቧል ሲሉ ምሬታቸውን ገልፀዋል። የከፋው ደግሞ፣ አህያ ናቸው ብሎ የነገረው ለቱርኮቹ ነበር። በአፄ ቴዎድሮስ በኩል፣ አውሮፓውያኑን በሚገባ አስተናግደውና አስደስተው አያለ፣ በጀርባቸው ሲያቤሩ ማየቱን በጣም ነው የጠሉት። "ራሴ ላይ አድርጌያችሁ ብዞር እንኳን ሰሜን ከማንደፍ አትመለሱም" ይሉ ነበር።*

***ቁጥር 48፤*** *አቶ ሳሙኤል የአፄ ቴዎድሮስ አስተርጓሚ ነበረ። ከካሜሮን ጋር ስለሚሠራ ካሜሮንን ረድቶ ይሆናል። በንጉሡ ትዛዝ ከራሳም ጋር ይሰራ ነበር። ንጉሡ፣ ምንም ያህል ራሳምን ቢወዱት፣ ቢያከብሩትና የራሳቸው ሰዎች እንዲያከብሩት ቢያስደርጉም አያምኑትም ነበር። በአንድ ጉዳይ፣ አቶ ሳሙኤል፣ ንጉሡን የራሳምን ሀሳብ እንዲቀበሉ ሲወተውት፣ "አቶ ሳሙኤል፣ ራስህን እንደ ባሪያ ለእንግሊዞቹ ሸጥክ ወይ? አህያ ነህ፣ ብቻ ምላስህን ሰብስብ..." ብለውታል። ከዚያ በኋላ የአቶ ሳሙኤል ታማኝነት ቀንሶ በምትኩ ደስታ ተመደበ። ንጉሡ ራሳቸው ለራሳም፣ አንተ ሳሙኤልን አግኝተሀል ለኔ ደግሞ ደስታ ልጄ ነው ብለው በተዘዋዋሪ ነግረውታል። ሆኖም ደስታም ቢሆን፣ ያውም ለጎንደር በሳት መቃጠል ምክንያት የሆነው ሰው (የጎንደር ሸፍቶች ዘርፈውት ራቁቱን መጥቶ፣ ቴዎድሮስ ከራሳቸው*

ካዝና አልብሰውት ነበር) መልሶ ንጉሡን ከደቶ የራሳም ረዳት ነው የሆነው:: ንጉሡ እያወቁም ሆነ ሳያውቁ፣ ራሳም ውስጥ ውስጡን በገንዘብም በታማኝነትም ሰውን አስከድቷል::

**ቁጥር 49፤** ለዚህ መዘግየት ምክንያት፣ ራሳም ከአፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤ አለማግኘት ነው:: ከንጉሡ የተላኩ ደብዳቤዎች ቢደርሱትም ማህተም ስላልነበራቸው ራሳም ማረጋገጥ አልቻለም ነበር:: አፄ ቴዎድሮስ የሚመልሱት ደብዳቤ ከሙሉ ልባቸው ካልሆነ ወይም ንቀት ካለባቸው ማህተም አያደርጉበትም ነበር:: በዚያን ጊዜ፣ አፄ ቴዎድሮስ፣ ራሳቸው ፈቃድ ያልሠጡት ማንኛውም አውሮፓዊ ወደ ግዛታቸው እንዳይገባ አግደው ስለነበር፣ ያለ ፈቃድ ወደ ጎንደር መሄድም አይችልም ነበር:: ሌሎች ምክንያቶች ደግሞ፣ በዚያን ጊዜ በየቦታው ሽፍታ ስለበረከተ፣ ራሳም ወደ ንጉሡ መሄድ ይከብደው ነበር:: ከጎንደር የመጣ ነጋዴ፣ ወልደስላሴ ገበዜ፣ እንደሚለው ከሆነ፣ ቴዎድሮስ፣ ፕላውደን ላይ የደረሰውን ሁኔታም አልረሱትም::

**ቁጥር 50፤** ራሳም የሚለው፣ የካሜሮንን የመፈታት ወሬ የነገረው መሀመድ ሉሌይ የሚባል ሰው ነው:: መሀመድ ደግሞ፣ የአርቁቆው (አርጊጎ) ናይብ ነው ይህን ውሸት እንድነግር የመከረኝ ይላል:: ራሳም፣ መሀመድን፣ የማጭበርበር ሥራ ሰርቶብኛል ብሎ ለቴዎድሮስ ቢከስም፣ አፄ ቴዎድሮስ ጉዳዩን በደንብ ያውቁ ስለነበር፣ መሀመድ ቢዋሽም ለበጎ ብሎ ያደረገው ስለሆነ በማለት አልቀጡትም::

**ቁጥር 52፤** ቴዎድሮስ ራሳምን በጣም ይወዱት ነበር፤ "አንተ ጥሩ ሰው ነህ፤ አለቆችህ ግን ጥሩ ሰዎች አይደሉም" ብለው ነግረውታል:: የተቻላቸውን ሁሉ ያደረጉለት ሰው ቢኖር ራሳም ነው:: የሚተኛበትን ክፍል ራሳቸው ጠርገው አቧራውን በእጃቸው አፍሰው፤ ምንጣፍ አንጥፈውለታል:: ያም ቢሆን ራሳም በነበረው ብልጠት የቴዎድሮስን ባህሪ በደንብ ስለሚያውቅ፣ በአክብሮት የሚገባቸውን ማዕረግ በመሥጠት እንጂ እንደነካሜሮንና ስተርን ተዳፍሯቸው አያውቅም:: ራሳም ንጉሡን በክብር ማናገር እንዳለበት፣ አስረኛው ካሜሮንን ጨምሮ ብዙ ሰዎች መክረውታል:: ቴዎድሮስ በሌላ ቀን ከራሳም ጋራ ሲጫወቱ፣ ወደኋላ በመሄድ፣ የአብርሃምና የይስሐቅ ልጅ ማነው ብለው ጠይቀውት፣ እርሱም የጥያቄው አመጣጥ ስለገባው፣ ትውልዱን እስከ ንጉሥ ሰለሞን ካደረሰ በኋላ፣ ራሳቸው ቴዎድሮስ ከሰለሞን ሀረግ እላቸው ብሎ ተናገረ:: ቴዎድሮስም ሲመልሱ፣ "ያውሮፓ ሰዎች ይህንን አምነው ከተቀበሉ፣ ለበደሉኝ ሁሉ ይቅርታ አደርግላቸዋለሁ" ብለዋል:: ሌሎቹም እንዳሉት፣ ንጉሡ የፈለጉት አውሮፓውያኑ በአክብሮት እንዲያዩዋቸው ነበር::

ቴዎድሮስ ራሳቸው በአደባባይ ካደረጉት ንግግር መረዳት የሚቻለው፣ አውሮፓውያኑ የመንግሥት ተወካዮች ከሆኑ የሚገባው ክብር ይሠጣቸው ነበር፣ ሌሎቹ ግን ከአቢሲኒያውያን አይለዩም:: በንግግራቸው እንዲህ ብለው ነበር:: "መቅደላ ከመስደዴ በፊት፣ ሚስተር ራሳም ወዳጄ ነበር፤ ምንም እንዲታሰር ባደርግም አሁንም ወዳጄ ነው፤ በዚህ ምክንያት አከብረዋለሁ እወደዋለሁ፤ በህይወት እስካለሁ ድረስ ጥሩ ነገር አደርግለታለሁ፤ ምንም እንኳን በእንግሊዝ ያሉ የሱ



የባላዮች ቢሳለቁብኝና በድህነቴ ቢንቁኝም:: ነገር ግን፣ ሜሰር፣ ስተርን፣ ሮዘንታልና ካሜሩንን ከራሴ ከአቢሲኒያ ሰዎች የበለጠ ክብር አልሰጥም::"

ቴዎድሮስ የሚሳለቁባቸውን የውጭ ሰዎችን አስተሳሰብ የመረመሩበት አንድ ሁኔታ፣ በሳቸውና በራሳም መካከል በተደረገ የንግግር ልውውጥ መረዳት ይቻላል:: ይኸውም፣ አንድ ቀን ከራሳም ጋር ሲጫወቱ፣ "ያገርህ ሰዎች ሲመጡ በጥቁርነቴ እንደማይጠሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ፤ እኔ የማምነው፣ ፈጣሪ ሁላችንም እኩል አድርጎ እንደፈጠረን ነው::" ብለዋል::

**ቁጥር 53፤** አፄ ቴዎድሮስ ራሳምን በክብር ከማስተናገዳቸው በተጨማሪ፣ የሰለሞን አርማና መስቀል ያለበት ኒሻን አንደኛ ደረጃ ሸልመውታል:: የአፄ ቴዎድሮስ ኒሻን ሶስት ደረጃዎች ነበሩት፤ አንደኛ ደረጃው ሙሉ በሙሉ ከወርቅ የተሠራ፣ ሁለተኛ ደረጃው፣ መስቀሉ ወርቅ ሆኖ አርማው በብር የተሠራ፣ ሶስተኛ ደረጃው ደግሞ ሙሉ በሙሉ ከብር የተሠራ ነበር:: አንደኛ ደረጃውን ያገኙት፡ ራስ መሸሻ (የንጉሡ የመጀመሪያ ልጅ)፣ ራስ እንግዳና ራሱ ራሳም ነበሩ:: ሁለተኛ ደረጃውን ያገኙት ደግሞ የባለጠመንጃዎቹ ጦር አዛዥ የሆኑት ራስ ጠጋ፣ ሉተናንት ፕሪዶና ዶክተር ብላንክ ነበሩ፤ ሶስተኛ ደረጃው ግን አልተወሰነም ነበር:: ይህን ኒሻን የሚሰራው ባለሙያተኛ፣ የቴዎድሮስ ባለሟል ዛንደር የሚባል ሰው ነበር::

**ቁጥር 54፤** መድፍና የጦር መሳሪያዎችን በጣም በመውደዳቸው፣ የውጭ ስጦታ፣ መሳሪያ ካልሆነ ብዙም ግድ አይሰጣቸውም ነበር:: ራሳም ያመጣላቸውን ሀር በሙሉ ከፍተው ሳያዩ ለቤቶቹ አሳልፈው ነው የሠጡት:: የጦር መሳሪያዎች ግን "ፍቅረ ካሳ" ይባሉ ነበር:: የፈረንሳዩ ዜጋ ለዣን፣ ለቴዎድሮስ የሀር ጨርቅ አምጥቶ፣ ባገሬ ይህን የመሰለ ጨርቅ የሚሰሩ ስላሉ የንግድ ልውውጥ እንዲጀመር በማለት ንጉሡን ይጠይቃል፤ በዚህ የተበሳጩት አፄ ቴዎድሮስ ያሉት ነገር፣ "እነዚህ ሰዎች ምን አድርጊያቸው ነው እንደ ሉቅ ሸቃጭ የሚመለከቱኝ?" በማለት ብስጭታቸውን ገልፀዋል:: ለዣንም ቢሆን፣ በዚህ ቢምሩትም በኋላ ባሳየው ንቀት፣ "የታባቱና፣ የዞሉኝ" በማለት አስረው አስናብተውታል:: ይህ ሰው ምፅዋ ሲደርሱ፣ ንጉሡን የሚዘልፍ ፅሁፍ በመላኩ ቴዎድሮስ ሲናደዱ፣ ሌሎች አውሮፓውያንም ባደረገው ነገር ነቅፈውታል::

**ቁጥር 56፤** ለዚህ ፍራቻ ደግሞ በቂ ምክንያት ነበር፤ በ1842 በአፍጋኒስታን የነበረ የእንግሊዞች ሠራዊት ከከተማው ከካቡል ሲሸሽ ከወታደሮቹ ጋር ቁጥሩ ወደ 16ሺ ሰው ይጠጋ ነበር፤ ነገር ግን በተራራ ማለፊያ ጠብቀው ያገኟቸው የአፍጋን ተወላጆች፣ ከአንድ ሰው በስተቀር ሁሉንም እንደጨረሷቸው ይታወቃል:: የተረፈው ሰው ዶክተር ነበር:: እንደሚባለው ከሆነ ለወሬ ነጋሪነት ነው ያተረፉት:: የብሪታንያ ሰዎች ይህን ታሪክ ጠንቅቀው ያውቁ ነበር::

**ቁጥር 58፤** በዘመኑ የአፄ ቴዎድሮስን ጦር ከጎዱት ነገሮች አንዱ ኮሌራ ነበር፣ "ነፍጠኛ ፈንግል" ተብሎ ይጠራም ነበር:: ወታደር ብቻ ሳይሆን የቴዎድሮስ ሹማምንቶችም

*ሀይወታቸው አልፏል። ከሚታወቁት አንዱ፣ ኢጋሬሪ ኀለም ነበር። ወረርሽኙን መቋቋም የቻሉት ጦራቸውን በየቦታው ከፋፍሎ በማስፈር ነበር።*

***ቁጥር 59፤*** *እዚህ ላይ የታሠሩ አውሮፓውያን ቤተሰቦችን እወክላለሁ በማለት በራሱ አነሳሽነት የመጣ ዶክተር ቤክ የሚባል ሰው ነበር። የመጣበት ጊዜም፣ ቴዎድሮስ እስረኞቹን ለመፍታት ቃል በሠጡበት ጊዜ ሲሆን፣ የሰውየው ተልኮ በተቃራኒ፣ ቴዎድሮስ በአውሮፓውያን ላይ የነበራቸውን ጥርጣሬ አባብሶታል። የዶክተር ቤክን ጣልቃ ገብነት እነራሳምም አልወደዱትም ነበር። ሰውየው ወደ ትግራይ ዘልቆ ለንጉሡ መልክት ሲልክ፣ ያለኔ ፈቃድ ማን ሀገሬ ውስጥ ግባ አለህ በማለት ወደ ምፅዋ እንዲመለስ አድረገውታል። የሰውየውን ባህሪ በትክክል የሚያውቀው አቶ ሳሙኤል ሲናገር፣ ዶክተር ቤክ አንግዳ የሆነ ባህሪ አለው፤ ቢመጣ ኖሮ፣ ቴዎድሮስ በሁለተኛው ቀን እስር ቤት ያስገቡት ነበር ብሏል።*

***ቁጥር 60፤*** *አቢሲኒያ ብሉ ቡክ፣ የእንግሊዝ መንግሥት ስለ አቢሲኒያ ማንኛውንም ዘገባ ጥናት ወይም ታሪክ እየሰበሰበ የሚያስቀምጥበት ፋይል ነው። ይህ ፋይል የደብዳቤዎች ቅጅ ሳይቀር ይሰበሰብበታል። በዚያን ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት ስለ አቢሲኒያ ሁኔታ ጠንቅቆ ማወቁ የመቅደላን ዘመቻ የተሳካ እንዲሆን አድርጎለታል። የሚገርመው ነገር፣ እንግሊዛውያን ብቻ ሳይሆን ሌሎች አውሮፓውያን የሚዘግቡትም ይሰበሰባል። በመቅደላ ዘመቻ፣ ፈረንሳዊው መንዚንጀር ከናፒየር ጦር ጋር ዘምቶ፣ ዋግ ሹም ጎበዜን ማግባባት የቻለው እሱ ነበር። አውሮፓውያውያ እርስ በርስ የሚፎካከሩ ቢመስልም በእንደዚህ አይነቱ ጊዜ ግን ሲተባበሩ ነው የሚታየው።*

# ምዕራፍ ሁለት

## አነስሊ ወሽመጥ - ኮሎኔል መርዌዘር

አነስሊ የባህር ወሽመጥ የተፈጠረው፣ ዲሲ[61] በሚባል ከአቢሲኒያ ድንበር ጋር በትይዩነት ለሀያ ማይሎች በተዘረጋ ደሴት ነው። በመሀሉ የሚገኘው ይህ ወሽመጥ ከአንድ እስከ አምስት ማይሎች የሚሆን የጎን ስፋት አለው።

ለዚህ አይነቱ ሥራ ከኮሎኔል መርዌዘር[62] የበለጠ ምርጫ ሊኖር አይችልም። ኮሎኔሉ፣ በህንድ በፈረሰኛ መኮንንነት ሲያገለግል የነበረና አሁን ደግሞ በኤደን ተቀማጭ የፖለቲካ ሠራተኛ ነው። ይህ ሰው፣ ቀድሞ ከሆርመዝ ጂ ራሳም ጋር በነበረው ትውውቅም ሲሆን ይችላል የለውየውን መታሰር ሲሰማ ለማስለቀቅ ተነሣሣ። ለእስረኞቹ የሚሆን ገንዘብ ላከ፤ አቢሲኒያውያንን በጉቦ በመደለል ወደ መቅደላና ደብረ ታቦር መልከት መላክ ጀመረ። በሎንደን ለነበሩ ዋና ጋዜጦች የጋዜጣ አንቀፅ መፃፍ ጀመረ፤ በፅሁፉም፣ ታላቋ ብሪታኒያ በህንድ ሊደርስባት ከሚችለው ውርደት ራሷን ማዳን አለባት አለ፤ ይህ የእንግሊዝ መልክተኞች በመቅደላ በእስር መያዛቸው፣ በመሀመዳኑና በሂንዱስታን ለዎች ከተሰማ፣ በምስራቅ በሚገኘው የንግስቲቷ ግዛቶች አለም አቀፍ አመፅ ሊነሳ ይችላል።

መርዌዘር፣ አይነተኛ የሆነ መኮንን፤ በምስራቅ በኩል በተደረጉ የተለያዩ ጦርነቶች፣ ጎበዝ፣ ስልት አዋቂ፣ ደፋርና ፈጣንነቱን ያስመሰከረ ሰው በመሆኑ፣ አቢሲኒያ ደንበር ላይ ለሚሰፍረው ለመጀመሪያው ጦር አዛዥ እንዲሆን ተመረጠ። ከዚህም ጋር የሀገሪቷን ተወላጆች በመጠየቅ ወደፊት ይከሰታሉ የሚባሉ ችግሮችን እንዲመረምርና ወደ መሀል አገሪቱ መግቢያ መንገድ እንዲፈልግ ነበር። ወጣትና ሙሉ ጉልበት ያለው ሰው በመሆኑ ለማረፊያ የሚሆነውን ቦታ ፈልጎ ሲያገኝ ጊዜም አልወሰደበትም። በዚህ፣ በእጁ ባደረገው መስፈሪያ ቦታም የቅዱስ ጊዮርጊስ ምስል ያለበት መስቀል በራሱ እጅ ለመጀመሪያ ጊዜ ተከለ።

[61] ደሴቱን ደጃች ንጉሴ ለፈረንሳዮች በሥጦታ (በምዕራፍ ሁለት ማስታወሻዎች)

[62] ኮሎኔል መርዌዘር፣ ቴዎድሮስ የጠየቋቸውን (በምዕራፍ ሁለት ማስታወሻዎች)